
# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር 9ኛ ዓመት ቁጥር 1 መጋቢት/ሚያዝያ 1993 ዓ.ም



በገረዓልታ ተራሮች አናት ላይ የምትገኘው
የቆርቆር ደብረ ማርያም ጥንታዊ ገዳም



እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ!

# ከአንባብያን

## እንንቃ

መቼም በቅድስት ቤተ ክርቲያናችን ሰላም እንዳይኖር በጐቹ በፍቅር እንዳይኖሩ የቅድስናን ሥራ እንዳይሠሩ የሚያደርጉ በየጊዜው ዘዴያቸውን እየቀየሩ የሚመጡ ተኩላዎች እንዳሉ ግልጽ ነው። ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ለዕረፍት ወደ ጉራጌ ዞን እዣ አካባቢ ሄድኩኝ። በዓለ አስተርእዮን በአጥቢያችን በደማቅ ሁኔታ እያከበርን እያለ እነዚሁ ተኩላዎች ዓይናቸውን አፍጥጠው ቤተክርስተያናችን ቅጥር ግቢ ድረስ በመግባት የቅሰጣ ሥራቸውን መሥራት ጀመሩ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት በምእመናን ትጋት ይህ እኩይ ተግባራቸው ተጋለጠ። ሊያዙ ሲሉም አመለጡ። በዚሁ አካባቢ ሥራዎቻቸው በተደጋጋሚ እንደሚታዩ ሰምቼአለሁ። «አንተ የምትተኛ ንቃ፣ ከሙታንም ተነሣ።» ኤፌ.5÷14። እንደ ተባለ ምእምናን በያለበንበት ነቅተን ቤተክርስቲያናችንን ልንጠብቅ ይገባል።

ስለሺ ምራኒ
ጅማ ዩኒቨርስቲ

## እንድረስላቸው

ምንም እንኳን ከባሕር ማዶ በሚጐርፍላቸው ገንዘብ ተዋሕዶአዊት ቤተክርስቲያናችንን ለመሸርሸር ቢኳትኑም፣ ለጣያት አንሰግድም በማለታቸው ወደ እቶን እንዲወረወሩ የተደረጉትን ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጐን ፀጉራቸው እንኳን በወላፈኑ ሳይነካ ከእሳት ያወጣቸው፤ሳኦልን ከአልጋው አውርዶ ዳዊትን ከትቢያ አንሥቶ በትረ መንግሥት ለመጨበጥ የረዳው አምላክ ዛሬም ከእኛ ጋር ነውና አንሰጋም። የሆነው ሆኖ በገጠር በተለይም በጠረፍ ያሉ አብያተክርስቲያናት በብዛት አስታዋሽ አጥተው በአሳባቢ ሁኔታ ላይ ናቸውና ምእመናን እና ስታውሳቸው። በዚያ ያሉትም ወገኖቻችን ናቸውና።

*ዓለማየሁ ደረሰ ዲምቱ*


**የምሥራች**

**የማኅበረ ቅዱሳን**
**ቁጥር ፩**
**ያሬዳዊ የመዝሙር**
**ካሴት በቅርብ ቀን**
**በሥርጭት ላይ**
ይውላል።


# ሥዕል ወይስ ምስል?

*ከኃ/ገብርኤል ዘሐና*

ሰብል ሲያዘረዝረ ጠላት ይበዛበታል የሚለውን የቄሱን ቃል እያሰላሰልኩ ከሩቅ ጉዞዬ እየተመለስኩ ነው። ደብረ ብረሃን ከተማ ደርሻለሁ። መሐል ከተማ ያለውን የቅድስት ሥላሴን ቤተክርስቲያን ልሳለም ጎራ አልኩ። ገና ከቅጥሩ ስገባ ብዙ ገንዘብ ፈስሶበት የተሠራውን ምስል አየሁ። የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና፣ሥነ ስቅለት የሚያሳይ መሆኑ ነው። መንገደኛነቴን ዘንግቼው ቆሜ እመለከተው ጀመር። ከኋላዬ አንድ የኔቢጤ መጥቶ ጋሼ ይሄ እኮ በየጊዜው ልብስ ይቀየርለታል፤ መጋረጃ ይጋረድለታል። በተለይ በበዓል ወቅት የሚያማምር ልብስ ይጎናጸፋል አለኝ። ቃል አልተነፈስኩም። ምስልና ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መች ይሆን የተዋወቁት? ጠያቂው አእምሮዬ ጠየቀ። ከግቢው ወጥቼ መንገዴን ቀጠልኩ።

አዲስ አበባ ብዙ ያዘረዘሩ ሰብሎች በፀረ ሰብል ተባዮችና እንስሳት እየተበላባት ያለች ሀገር ናት። ጓደኛዬ ነው ይህን የነገረኝ። ፈራሁ የፈሪዎቹም የጀግኖቹም መሸሸጊያ ወደሆነችው ቤተክርስቲያን ሮጥሁ። የመጀመሪያውን ቀን አራት ኪሎ ካቴድራል ቅድስት ሥላሴ፣ሁለተኛውን ቀን ታዕካ ነገሥት ባኣታ ለማርያም ሄድሁ። በሦስተኛው ቀን መቼስ አንዴ መንገደኛ ሆኛለሁ፤ ስዞር ነው የዋልኩት። አራት ኪሎ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ፣ምስካዬ ኀዙናን መድኃኔዓለም፣ሽሮሜዳ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ፣አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል የሄድኩባቸው ናቸው። ሁሉም ደስ ይላል። እንደየዐቅማቸው ተልዕኮአቸውን ለመወጣት ደፋ ቀና ይላሉ። አንዳንድ ያየኋቸው ምእመናን ድርጊት ግን ውጤን ረበሸው። አሳዘኑኝ። በግቢው ውስጥ ከቆሙት ምስሎች ሥር ተደፍቶ ይጸልያሉ። ከመቅደሱ ገብቶ ከጽላቱ ፊት ተደፍቶ መጸለዩስ ሊቀር ነው? አልኩኝ።

እነዚያ ደብረ ብርሃን ያየሁአቸው ዓይነት ምስሎች በአንዳንድ የአዲስ አበባ አድባራት እና ገዳማት ተገጥግጠው መሠራት ጀምረዋል። የ4 ወንጌላውያን ፣የመላእክት፣የእመቤታችን ምስል በጀሶ፣በተለያዩ ማዕድናት ተቀርጸዋል። አሁንም አእምሮዬ ምስልና ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መች ይሆን የተዋወቀት? ብሎ ጠየቀኝ።

ቀኑን ሁሉ ስዞር ውዬ ደክሞኛል። የጊዜ ንዋሙን ጸሎት አድርሼ ልተኛ ስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ያኔ ልጅ ሳለሁ የሃይማኖት አባቴ ስለ ሥዕልና ስለ ምስል የነገሩኝ ነገር ታወሰኝ። «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከምትጠቀምባቸው ንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ሥዕል ነው። ሥዕል በተለያዩ ቀለማት በወረቀት፣በጨርቅ፣በብራና በግድግዳ ላይ የሚሳል ነው። ሥዕል ለመንፈሳዊ አገልግሎት መዋል የጀመረው በፈቃደ እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን ሲሆን በመጀመሪያ የተሳለውም ሥዕለ ኪሩብ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ዘጸ 37÷7 ። ቤተክርስቲያናችን ከጀሶ፣ከስሚንቶ፣ከእንጨት የሚሠሩ ምስሎችና ቅርፆችን አትቀበልም።»


**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ መሆን ከፈለጉ**

| | ሐመር መጽሔት | | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 ዕትም | የ12 ዕትም | የ6 ዕትም | የ12 ዕትም |
| ለአዲስ አበባ | 18.70 | 37.40 | 10.00 | 20.00 |
| ለክፍለ ዐገር | 19.20 | 38.40 | 10.50 | 21.00 |
| ለውጭ ሀገር | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 9 ዶላር | 18 ዶላር |

አድራሻዎንና የከፈሉበትን ማስረጃ ለዲ.መስፍን ተ/ዮሐንስ ንግድ ባንክ 4 ኪሎ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 75282 አዲስ አበባ ከፍለው በመ.ሣ.ቁ 80078 ይላኩልን።

[illegible] ገ/መድኅን:: [illegible] 23-25

ቅዱሳን ስለሥራቸው ክብርና ዝና ተናግረው አያውቁም:: ሌሎች ቅዱሳንና እግዚአብሔር ግን ይመሰክሩላቸዋል:: ሩት ስለሥራስዋ «እኔ እንግዳ ነኝ» ነበር ያለችው::

/በረከተ ወንጌል /

ቅዱስ ሚካኤል ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚከራከር መልአክ ነው:: ዲያብሎስ የሙሴን መቃብር ለእሥራኤል አሳይቶ አምልኮተ ባዕድ እንዲፈጽሙ ለማስተማር በተነሣ ጊዜ የተከራከረውና እስራኤላውያንን የጠበቃቸው እርሱ ነው::

/ትምህርተ ሃይማኖት/

እኔ አሜሪካ ከሄድኩ ገና አምስት ዓመቴ ነው:: ያገሬ ሰዎች ግን 100 ዓመት ሆኗቸዋል:: ብዙዎችም ሙሉ በሙሉ ከአገሩ ሕዝብ ጋር ተዋሕደዋል:: አሜሪካውያን ሆነዋል:: አሜሪካዊ ያልሆኑም ቢሆኑ የመጨረሻ ሕልማቸው አሜሪካዊነት ሆኗል:: የዚህም ሰበቡ «አሜሪካ የኔ ናት» የሚል አንድ ዘር ወይም ጎሳ ባለመኖሩ ነው::

/ቃለ መጠይቅ/

ዛሬ ዛሬ ከየትኛው ገዳም እንደመጡ የማይታወቁ በርካታ መነኮሳትና መነኮሳይያት በዓታቸውን ትተው በየከተማው ሲዟዟሩ ይታያሉ:: የቀደሙት አባቶች የደነገጉልን ሕግ «ማንም በዓቱን ለቆ በመንደርና በከተማ ሲወጣና ሲወርድ ቢገኝ ተመክሮ አልሰማ ካለ ከማኅበሩ ይለይ» እያለ በማይታወቅ የግል ጉዳያቸው ከተማ ገብተው ከቀናት አልፎ ወራት ሲያስቆጥሩ የገዳማቸው አስተዳደር በደንቡ መሠረት እርምጃ ሲወስድባቸው አይታይም::

/ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ/


ዋና አዘጋጅ - ግርማ ወ/ሩፋኤል
ም/ዋና አዘጋጅ- መርሻ አለኸኝ



ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

E -mail-EOC-M-KIDUSAN@ telecom.net.et.



ሐመር
9ኛ ዓመት ቁጥር 1
የካቲት / መጋቢት 1993 ዓ.ም


# ይዘት


የማኅበሩ መልእክት

- ቤተክርስቲያንን የምናገለግለው በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው ....................2

ደብዳቤዎች ............................................ 4

በረከተ ወንጌል
- ሩት ..................................................6

ትምህርተ ሃይማኖት
- ጸሎተ ሃይማኖት ................................ 9
- መላእክት ........................................12

ምዕራፍ..................................................15

ቃለ መጠይቅ
- ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊነትን ላላየውና ላልቀመሰው.............................................16

ኪነጥበብ
- በባቢሎን ወንዞች አጠገብ ........................ 17

እናስተዋውቃችሁ
- ደብረ ማርያም ቆርቆር ዘገርዓልታ..............19
- አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ ..........................21

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- ብቸኝነት ..............................................23

ዓምደ ወራዙት
- የወጣቱ አስተዋጽኦ ለቤተክርስቲያን.......... 26

ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ
- ◆ ገዳማዊ ሕይወት.................................. 29



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

# የማኅበሩ መልእክት

## ቤተክርስቲያንን የምናገለግለው በቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት–በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው

በአሜሪካ አገር ከምትገኝ አንዲት ትንሽ ግዛት ውስጥ ኦርቶዶክሳውያን መሆናቸውን በገለፁ ግለሰቦች የተሠራጨ እና «ኢትዮጵያ ከሚገኘው እና ማኅበረ ቅዱሳን በመባል ከሚታወቀው መንፈሳዊ ማኅበር ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክስቲያንን ለማቋቋም» ዝግጅት ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ በራሪ ወረቀት በቅርቡ ከጽ/ቤታችን ደርሦ ነበር። በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ ግዛቶች የሚገኙ አባቶች፣የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናንም ስለዚሁ ወረቀት ፍሬ ሐሳብ ጉዳይ ሲጠይቁን፤ «ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ ዓይነት ተግባር ላይ መሣተፍ የጀመረውስ ከመቼ ጀምሮ ነው?» ሲሉን ሰነበቱ። በዚሁ አስታከው የማኅበሩን አጠቃላይ አገልግሎት ማሽመድመድ የሚፈልጉ ግለሰቦችና አካሎችም የየራሳቸውን አስተያየት ለመስጠት ሲሽቀዳደሙ ከረሙ። ከዚህ በፊት ቢናገሩት ቢናገሩት ሰሚ ያላገኙበትን ነገር ሁሉ ለማለት ሞከሩ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ያሠራጨው አካል ባለቤትነት ላልተጠቀሰበት፣ ቤተክርስቲያንን ማቋቋም ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ላልተቀመጠበት ለዚህ ወረቀት መልስ መስጠት ባይሆንም የበራሪ ወረቀቱ አዘጋጆችም ሆኑ ሌሎች ግለሰቦች ስለማኅበሩ ዓላማና አሠራር ተጨማሪ መረጃ ያገኙ ዘንድ ይህንን መልእክት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በርግጥ በበራሪ ወረቀቱ ላይ ከሠፈሩት ነጥቦች መካከል ማኅበሩን በትክክል የሚመለከቱት በኢትዮጵያ መገኘቱን እንዲሁም መንፈሳዊ ማኅበር መሆኑን የሚጠቅሱት ሁለት ነጥቦች ብቻ ናቸው። ከዚህ በተረፈ የወረቀቱ አዘጋጆች ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ካላቸው ቅንዓትና በአካባቢያቸው ሕንፃ ቤተክርስቲያን ያለመኖሩን በመመልከት ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከመፈለግም ይሁን ከሌላ ዓላማ የተነሣ ማኅበሩን የጠቀሱበት መንገድ ከማኅበሩ ዓላማ ጋር ያልተገናዘበ ነው። ይህም የማኅበሩን አሠራር ካለመረዳት ወይም ሆን ተብሎ ለማስጠላት ከማሰብ የተፈጸመ ድርጊት ሊሆን ይችላል። በዚህም ይሁን በዚያ ግን ድርጊቱ ማኅበረ ቅዱሳንን የሚመለከት አይደለም። የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት የሚፈጸመው «በቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት በቤተክርስቲያን ውስጥ» ነውና።

ከመዋቅሩ ለመረዳት እንደሚቻለው ማኅበረ ቅዱሳን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ሥር ተዋቅሮ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚፈጽም ማኅበር ነው። አባላቱም የሰንበት ት/ቤት ወይም የሰበካ ጉባኤ አባልነት ያላቸው፤ በሰንበት ት/ቤቶች፣በሰበካ ጉባኤያት እንዲሁም ቤተክርስቲያን በምታዛቸው ማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎቶች የመሣተፍ እና ለቤተክርስቲያን አባቶች የመታዘዝ ግዴታ ያለባቸው ናቸው። በዚህ መሠረትም «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ሳይለወጥ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ይችል ዘንድ የዘመኑን ትውልድ አስተባብሮ ትምህርተ ሃይማኖት ለሁሉም እንዲዳረስ» ያደርጋል። «በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ወጣቶችን በማኅበሩ ሥር በማደራጀትም «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት እንዲማሩና የአባቶች ተተኪ እንዲሆኑ» እንዲሁም በሥራ ምክንያት ከአንዱ አጥቢያ ወደሌላው አጥቢያ የሚዘዋወረውን ይህንን ትውልድ በሄደበት ተከታትሎ በሰንበት ት/ቤትና በሰበካ ጉባኤ እንዲታቀፍና በገንዘቡ፣በዕውቀቱ እንዲሁም በጉልበቱ እንዲያገለግል ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ከዚህም ባሻገር «የሚመለከታቸውን የቤተክርስቲያኒቱን አካላት በማስፈቀድና በማነጋገር ትምህርተ ወንጌልን በተለያዩ ዘዴዎች /በመጽሔቶች፣ በጋዜጦች፣በበራሪ ጽሑፎች፣በካሴቶችና በመሳሰሉት/ እንዲስፋፋ» የሚያደርግ ማኅበር ነው። ይህንንም የሚያደርገው በጠቅላይ ቤተክህነት ደረጃ በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ፤ በአኀጉረ ስብከት ደረጃም ከሀ/ስብከቶችና ከወረዳ ቤተክህነት ጽ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ነው። ከዚህ የወጣ ከዚህ የተለየ የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት የለም።

በዚህም መሠረት ከ60 በላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያንን በማደራጀት

እምነታቸውን፣ሥርዓታቸውን፣ትውፊታቸውንና ታሪካቸውን እንዲያውቁ በማድረግ ላይ ይገኛል። ተመርቀው የወጡትም እናት ቤተክርስቲያናቸውን በገንዘባቸው፣በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው ያገለግላሉ። ምእመናን ስለቤተክርስቲያናቸው ትምህርት ጠንቅቀው ይረዱ ዘንድም በሐመር መጽሔት፣በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣና በበራሪ ወረቀቶች አማካኝነት ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው።

ገዳማትንና አድባራትን በተመለከተም የተጎዱት ይረዱ እና የደከሙት ይበረቱ ፣በቋሚነትም ራሣቸውን ይችሉ ዘንድ ፕሮጀክቶችን በማስቀረጽም በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ይረዳል። ይህ ሁሉ አገልግሎት የሚፈጸመው ግን በቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው።

አንድ ዋና የሚለማመድ ሰው ወይም ሥራው ከውኃ ጋር የተገናኘ ባሕረኛ ሁሉን ነገር በባሕር ላይ እንደሚሠራ ሁሉ መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚሹ ሁሉም በቤተክርስቲያን ጥላ ሥር መሰባሰብ እንዳለባቸው ማኅበሩ ያምናል። ከዚህ ውጪ በየመንደሩ፣በየጓዳውና በየግል ፍላጎት ከቤተክርስቲያን ታዛ በመራቅ የሚሠራ ሥራ የለም።

በሌላም በኩል የቤተክርስቲያንን ሥራ ከቤተክርስቲያን ርቀን መሥራት እንደሌለብን ሁሉ የቤተክርስቲያን ያልሆነውን ተግባር በቤተክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ልንፈጽም አይገባንም። የቤተክርስቲያን ዓውደ ምሕረት አዳባባይነቱ ለቤተክርስቲያን ትምህርት፣ለወንጌል ቃል እንጂ ለምድራዊ አስተሳሰብ ወይም ለግለሰቦች ፍላጎት ማስተናገጃነት አይደለምና። በዚህ ረገድም ማኅበረ ቅዱሳን አቋሙን በግልጽ አስቀምጧል። «በማንኛውም የቤተክርስቲያን አስተዳደርም ሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም ጣልቃ ገብነት» እንደማይኖረው በመግለጽ። ወጣቱን የምናስተባብረውም ይህንን የምሕረት አገልግሎት ለመፈጸም፣የምሥራቹን ቃል ለማድረስ፣ የቤተክርስቲያንን እምነት፣ሥርዓትና ትውፊት ለመጠበቅ ብቻ ነው። በዚህ ዐቢይ ሐሳብ መመሪያነት ነው አገልግሎታችንን የፈጸምነውና የምንፈጽመው። ይህንንም ምእመናን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ከዚህ የተነሣም አመኔታቸው ከፍ ያለ ሆኗል። በመጽሔትና በጋዜጣ የምናወጣቸውን፣በአንደበታችን የምንናገራቸውን የሚቀበሉትም ለዚህ ነው። ይህንን ያደረገውን አምላካችንን ዘወትር እናመሰግነዋለን።

ይሁን እንጂ ይህንን መልካም ስምና ተግባር ለግል ጥቅማቸው ለማዋል የፈለጉ ሰዎች የሉም ማለት አይቻልም። የማኅበሩ አባላት ሳይሆኑ «የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ነን»፣ሳይላኩ «ከማኅበሩ ተልከናል» ፣ ወይም ከማኅበሩ አባላት መካከል «ታዋቂዎች ናቸው» ብለው የሚያስቧቸውን ስም በመያዝ «አውቀዋለሁ፣ጓደኛዬ ነው » ወዘተ በማለት ያጭበረብሩና የሚያጭበረብሩ ሰዎች ነበሩ። ለአብነትም በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1 ላይ ያወጣነውን ግለሰብ መመልከት ይቻላል።

ብዙ ጊዜ የነዚህ አጭበርባሪዎች ሰለባ የሚሆኑት ደግሞ የማኅበሩን አጠቃላይ አሠራር ያልተረዱ ሰዎች መሆናቸውን ተገንዝበናል። ለምሳሌ በአሜሪካ በተሠራጨው ወረቀት ግራ የተጋቡት ሰዎች በዚህ ወገን ሊታዩ ይችላሉ። በእጃቸው ስለገባው ወረቀት በአሜሪካ የሚገኘውን የማኅበሩን የግንኙነት ጣቢያ ወይም አዲስ አበባ ያለውን ዋናውን ማዕከል ጠይቆ ከመረዳት ይልቅ ሌሎች ያሉትን ተቀብለዋልና። የማኅበረ ቅዱሳን አቋም፣ዓላማ፣አሠራርና አካሄድ የሚገለጸው በሥራው፣በሕጋዊው የማኅበሩ የመዋቅር ሠንሠለት መሠረት ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ የሚባለውም ሆነ የሚነገረው ነገር ማኅበረ ቅዱሳንን አይመለከትም። የማኅበረ ቅዱሳን ዓላማ የቅድስት ቤተክርስቲያን ዓላማ፣መመሪያው የቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ፣የመጨረሻ ግቡም ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ናት። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረውም ማኅበርተኞነታችን በወንጌልና ስለወንጌል በመሆኑ» ስለ ወንጌል ሁሉን እናደርጋለን።» 1ቆሮ.19÷23። «እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ÷ፍቅር ያለበት ነገር ሁሉ፣መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ» ገንዘብ ለማድረግ እንጥራለን። ፊልጵ.4÷8–9። ከአባቶቻችን የተማርነውንና የተቀበልነውን÷የሰማነውን ያየነውንም እናደርጋለን። ይህ ሁሉ የሚገኘው በቤተክርስቲያን ውስጥ÷ቤተክርስቲያንን ስናገለግል÷ በቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ስንመራ በመሆኑም ሁልጊዜ አጥብቀን እንከታተለዋለን። የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር÷በቤተክርስቲያናችን ኖረን÷በሕጓ ተመላልሰን÷ የመንግሥቱ ወራሾች ለመሆን ይርዳን። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ደብዳቤዎች

## ሚዛኖችን በርቱ በሉልኝ

በሚዛን ተፈሪ ከተማ መናፍቃን የበዙበት ሆኖ ሳለ ሌት ተቀን ቢሠሩ በማይታክቱት የሀገረ ስብከቱ የሥራ ኃላፊዎችና መምህራን አማካኝነት ሴራቸው እየከሸፈ ነው:: ለወደፊቱም በዚሁ እንዲቀጥሉ አደራ እያልኩ ሌሎች አኅጉረ ስብከትም ከዚህ ትምህርት እንዲወስዱ መልእክቴን አስተላልፉልኝ::

*አባቴነህ ለማ*
*ሚዛን ተፈሪ*

## ወጣቶቹ በርቱ

ይህንን ደብዳቤ የምጽፍላችሁ በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 በቀረበው የማኅበራችሁ መልእክት መናፍቃን «የተልእኮአችን ማዕከላት» ከሚሏቸውና ጥንትም ግራኝ መሐመድን የመሰለ ፀረ ቤተክርስቲያን ለተነሣባት ለሐረር ከተማ ነው:: ይሁን እንጂ ዛሬም በዚች ከተማ እነሱ እንዳሉት የመናፍቃን እንቅስቃሴ ጐልቶ እየታየ ወጣቱ ኦርቶዶክሳዊ ሲንቀሳቀስ አይታይም:: ለምን ይሆን? ወደድንም ጠላንም የነገዋ ቤተክርስቲያን ተረካቢዎች እኛ እስከሆን ድረስ ከአባቶቻችን ጐን በመሆን እንትጋ::

*ኃይለ ሚካኤል*
*መቀሌ ዩኒቨርስቲ*

## ...ሴሎችንም

ለአሥራ አምስት ተከታታይ ቀናት በአጥቢያችን በጆሮአችን የሰማነውን ትምህርት በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 በዐይናችን ስናየው የበለጠ ገባን:: ይኸውም በባስልዮስ ዘቂሳርያ የወጣው «ሩት» የተሰኘው ጽሑፍ ነው:: የአባታችንን ስም ብቻ ሳይሆን ግብሩንም የወረሰው ወንድማችን አሁንም እኔና መሰሎቼ በዐይናችን ከማንበብ በቀር ታሪክ ከምሥጢር ጠንቅቀን የማናውቃቸውን ሌሎች የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት /መጽሐፈ ዮዲት፣ መጽሐፈ አስቴር ወዘተ/ እንዲተነትንልን አደራችን ይድረሰው::

*ወ/ጊዮርጊስ ታደሠ*
*አ/አ*

## ሥላሴን የጠራ

በሲድኒ ኦሎምፒክ ድልን ያቀዳጁን አትሌቶቻችን በንግግራቸው ሁሉ «እግዚአብሔር÷ እግዚአብሔር» እያሉ ይጠሩት የነበረው እግዚአብሔር ለካ «ዓለም» ሁሉ የሚለው «እግዚአብሔር» ሳይሆን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምትጠራውን ሥላሴን ኖሯል:: መጽሐፉስ እንዲህ ብሎ የለ? *«ቅሩብ እግዚአብሔር ለኵሉ ሎሙ እለ ይጼውዕዎ – ወለኵሎሙ እለ ይጼውዕዎ በጽድቅ»* መዝ.144÷18:: አሁ ንም የሥላሴን ስም ከመጥራት አት ታክቱ በሉልኝ::

*ዶ/ር ዘርፉ መልአኩ*
*በደለ*

## ትጉህ ኖላዊ

«ወጣትነት ለቤተክርስቲያን አገልግሎት መቀደስ» በሚል ርዕስ በአባታችን በሊቀ ካህናት ኃ/ሥላሴ ዓለማየሁ እየቀረበ ያለው ትምህርት ምን ያህል ትውልዱን እየታደገ እንደሆነ ለመግለጽ ቃላትም አንደበትም የለኝም:: በእውነት አባታችንን ቤተክርስቲያን የሰጠችዎን ኃላፊነት በሚገባ እየተወጡ ነውና አሁንም ይበርቱልን በሉልኝ:: ይህ ነው ኖላዊነት::

*መ/ር ብርሃኑ ታደሰ*
*ጋዘር /ደ.ኦሞ/*

## የነብርን ጅራት

የአምላክን አደራ በመያዝ በጐች ምእመናንን ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ ምን ያህል በተጠንቀቅ እንደቆማችሁ ካለፈው የመጽሔታችሁ መልእክት ተረድቻለሁ:: አሁንም በእነርሱ አድሮ «እነዚህ ሰዎች አስቸገሩኝ» ያለው ሰይጣን በመሆኑ የነብርን ጅራት ከያዙ... ነውና በእመ ብርሃን ጸሎትና ምልጃ በቅዱሳን ሁሉ እየታገዛችሁ ትጉ እላለሁ::

*ኃ/ጊዮርጊስ*
*ከሚዛን ተፈሪ*

## አመስግኑልኝ

በአሶሳ ዞን በኩርሙክ /ኩታ ወረቄ/ ከተማ በ1991 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ የተጀመረው የምዕራብ ፀሐይ ብሥራተ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ግንባታው ተጠናቅቆ ታኅሣሥ 22/1993 ዓ.ም. አባቶቻችንና የአሶሳ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት መዘምራን እንዲሁም የአካባቢው ምእመናን በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተመርቆ ታቦተ ሕጉ በቦታው ከብሯል:: አባቶቻችንንና መዘምራኑን በምእመናን ስም አመስግኑልኝ::

*ቤካ ገ/ሚካኤል*
*ኩርሙክ*

## አርአያነት ያለው

«ይህ ሁሉ አድማና ግርግር ለወንጌል ስብከት ወይስ ለወንጀል መስፋፋት» በሚል በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 የተጻፈው የማኅበሩ መልእክት መናፍቃን እንዴት ባለ ሁኔታ የበግ ለምዳቸውን ለብሰው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳሉ አሳይቶናል:: በተጨማሪም በቅድስት ቤተክርስቲያን ታዛ ስር ተጠልለው የመናፍቃንን እኩይ ዓላማ የሚያሳኩትን ግለሰቦችና ቡድኖች በማጋለጥ ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን እየሠራ ያለውን መልካም ሥራ እንድናይ አድርጐናል:: ይህም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጥላ ስር ያለነውን ሁሉ የሚያስደስት በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባውና አርአያነት ያለው ተግባር ነው:: ለሥራችሁ መሳካትም ልዑል እግዚአብሔር ኃይል ና ብርታቱን ይስጣችሁ::

*ሙሉጌታ ኃ/ሚካኤል*
*ከቀጨኔ ደ/ሰ/መ ቤ.ክ*

## ልንኮራባቸው ይገባል

በሐመር መጽሔት ታትመው የሚወጡት ጽሑፎችና ሥዕሎች እውቀት የምንገበይባቸውና የመንፈስ ርካታ የምናገኝባቸው ናቸው:: ቤተክርስቲያናችን ለዘመናት ተንከባክባና ጠብቃ ያቆየቻቸው የታሪካችን መገለጫና የማንነታ

ችን ማረጋገጫ ስለሆኑ ልንኮራባቸው ይገባል:: ለምሳሌ ባለፈው የጥምቀት በዓል በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 መጽሔት የፊት ሽፋን ላይ የወጣው ፎቶ ግራፍ በጐንደር የሚገኘው ግንብ እጅግ ውብና ማራኪ በመሆኑ ለጥምቀት በዓሉ አከባበር ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል::

*እስጢፋኖስ*
*/አ.አ/*

## መናፍቃንን ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው

በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 እትም የማኅበሩ መልእክት ላይ «ይህ ሁሉ አድማና ግርግር ለወንጌል ስብከት ወይስ ለወንጀል መስፋፋት» በሚል ርዕስ ያወጣችሁት ጽሑፍ ምን ያህል የመናፍቃንን እንቅስቃሴ በንቃት እየተከታተላችሁ መሆኑን ያስገነዘበኝና ያሰደ ሰተኝ መሆኑን ታውቃላችሁ? ይህም ከጊዜ በኋላ መናፍቃንን ተስፋ የሚያ ስቆርጥ በመሆኑ በርቱ እላለሁ:: ምእ መናንም የአፋቸውን ልዝብነት አይተው እንዳይታለሉ ድብቅ ሴራቸውን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ አጉልታችሁ ማሳየታችሁ ይበል የሚያሰኝ ነውና ቀጥሉበት::

*መ/ር እሱባለው መላኩ*
*መ፥ ደ/ሰ/ቅ/ሚካኤል ሰ/ት/ቤት*

## እኛም እንደ አባቶቻችን እንሁን

ሐመሮች በ8ኛ ዓመት ቁ ጥር 5 ላይ «እናንተም ደግ ገደላችሁ እርሳቸውም ደግ ሞቱ» በሚል ርዕስ ስለ አቡነ ሚካኤል ዘጐሬ ተጋድሎ ያቀረባችሁት ጽሑፍ የሚያስመሰግን ነው:: ቤተክርስቲያናችን ሃይማኖታቸውን ከ መልካም ምግባር ጋር አስተባ ብረው የያዙ አባቶች መፍለቂያ ናት:: እኛም እንደ አባቶቻችን እንሁን፣ አሠረ ፍኖታቸውንም እንከተል::

*መስፍን ደሴ*
*ወላይታ ሶዶ*

## ምግቧ በደቃቁ ሆነ

ብዙ የሕይወት ስንቅ ይዛ በየሁለት ወሩ የምትደርሰኝ መጽሔታችሁን እወዳታለሁ:: ነገር ግን አሁን አሁን ሰይጣን ነው መሰለኝ ለእኔና በእሷ መካከል ችግር እየተፈጠረ ነው:: ይኸውም በውስጥ የምትሰንቃቸው ምግቦች በእጅጉ የደቀቁና የተጠጋጉ በመሆናቸው ብዙም ባይሆን ዕድሜ ያዝ ባደረገው ዓይኔ እንደልቡ ልመገባቸው አልቻልኩም:: እባካችሁ የምትችሉ ቢሆን እንደእኔ ሌሎች ዓይናቸው ደከም ያሉ ሰዎችም ሊቸገሩ ይችላሉና የፊደል መጠኑን ጨመር አድርጉልን::

*አቶ ላየ ከራሉ*
*ሞጆ*


__ከአዘጋጁ__

አቶ ላየን እናመሰግናለን:: እርስዎ ያሉትን ችግር ሳንረዳ ቀርተን አይደለም:: ነገር ግን መጽሔቷ ወደ እናንተ የምትመጣው በሁለት ወር አንዴ ስለሆነ ከስንቁ ጨመር አድርጋ እንድትደርሳችሁ በሚል ነው:: ጥያቄዎን በሚቀጥሉት እትሞቻችን ጀምሮ በተግባር እንመልሳለን::

## አዎ የአባ ጦር ይሰበቅ

ባለፈው እትም -የአባ እንየው ጦር ይሰበቅ? በማለት በደብዳቤዎች ዓምድ የመከራችሁን ምክር ደርሶናል:: አባ እንየው የሰይጣንን ተልእኮ ይዘው በቤተክርስቲያናችን ላይ የዘመቱ መናፍቃንን ለመመከት የሚወጡት የሚወርዱት በስተርጅና ነውና ሌሎች በፅኑ ታግሎ የሚጥለው ሮጦ የሚያሸንፈው ወጣቱም የአባታችንን ጦር ይስበቅ እላለሁ::

*ጠናበል ለማ*
*አ/አ*



የእናንተ ለእኔ ጽሑፎች ዋጋ አለመስጠት ከቅርጫታችሁ ሰፊነትና አይምሬነት የተነሣ ይህንን የማልፈልገውን ውሳኔ እንድወስን አድርጎኛል ለእናንተ የተለያዩ መጣጥፎችን በመላክ ጊዜዬን ከማጠፋ ወደሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎች መዞር ይበልጥብኛል:: ጊዜ ወርቅ ነውና::

*ፍሬ ሠናይ ፀጋዬ*
*ጐሐ ጽዮን*

__ከአዘጋጁ__

አንባቢያችን ወደሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎችም መዞርዎ ጥሩ ነው:: ለእኛ ጀርባዎትን ሳይሰጡ ማለት ነው:: ችላ አላችሁኝ ላሉት ግን እኛ እንደዚያ አናደርግም:: የእኛ ዝግጅት እኮ ለእርስዎና ለመሰል ኦርቶዶክሳውያን ነው:: ይበሉ ለዚህ አባባላችን መልስ በመስጠት በመካከላችን ዕርቅ እንዲሰፍን ያድርጉ::

## ድንቅ ዝግጅት

ትናንት አረማውያን ያደረሱትን የንዋየ ቅድሳት ውድመት በተለያየ መንገድ እየደገሙ ያሉ አጽራረ ቤተክርስቲያን እየተስፋፉ ያሉበት ዘመን ነው:: ታዲያ እናንተም ይህንን ተገንዝባችሁ ለንዋያተ ቅድሳት መጠበቅ በቀጥታ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ክፍሎች በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 እትም ጠይቃችሁ በችግሩ ዙሪያ እንዲናገሩ ስላደረጋችኋቸው አመስግናችኋለሁ፡ ድንቅ ዝግጅት:: ነገር ግን አንድ ክፍል ቀርቷችኋል:: ለመሆኑ በጉዳዩ ምእመናን ምን ይላሉ ?

*ሐና*
*ከድሬዳዋ*

## ከሰው ጋር አገናኛችሁኝ

በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 «ብቸኝነት» የሚለው ጽሑፍ ከሰው አገናኝቶኛል:: ቀጣዩን ደግሞ በጉጉት እየጠበኩ ነው:: በእውነቱ የችግሩ ተጠቂ በመሆኔ ስፈልገው ያገኘሁት ጽሑፍ በመሆኑ ጠቅሞኛል እግዚአብሔር ይስጥልኝ::

*መታሰቢያ*
*አ/አ*

## አንቶቼን አመስግኑልኝ

ከደራርቱና ከጌጤ ጋር ያደረጋችሁትን ቃለ ምልልስ አነበብኩት:: በእውነት በተሰማሩበት ሙያ ስኬትን እየተጐናጸፉ በእግዚአብሔር ቤት መኖራቸው ለብዙዎቻችን አርአያ የሚሆን ነውና አመስግኑልኝ::

*ፋጹም ገ/እግዚአብሔር*
*መቀሌ*

## አሷንም አየኋት

ብዙ ጊዜ ሐመርን ከምናፍቅባቸው ዓምዶች አንዱ እናስተዋውቃችሁ ነው:: እስከአሁን በዚህ ተወዳጅ ዓምድ አማካኝነት ከርካታ ቅዱሳት መካናት ጋር ተዋውቄያለሁ:: ባለፈው የ5ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትም ደግሞ ስለመኖሯም ሰምቼ የማላውቀውን የአጤ ዋሻ ማርያምን ቤተክርስቲያን በዓይነ ኅሊናዬ አይቼአታለሁ:: ይህንን በረከት እንዳገኝ ያደረገኝ ዲ.ስሎሞን ወንድሙን እግዚአብሔር ይስጥልኝ በሉልኝ::

*ዲ. መታፈሪያ ዓለሙ*
*ምዕራብ ወለጋ*

# ሩት

*ባለፈው እትም በዚህ ርዕስ ሥር ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት አንዱ ስለሆነው መጽሐፈ ሩት ያደረግነውን ትንታኔ የመጀመሪያ ምዕራፍ አይተናል። በዚህ ምዕራፍ የመጽሐፉ ዋና ባለታሪክ ስለሆነችው ሩት ከአማቷ ኑኃሚን ጋር ስላደረገችው የእምነት፣የተስፋና የፍቅር ጉዞ የመጀመሪያ ክፍል ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ ካቆምንበት እንቀጥላለን። መልካም ንባብ*

ባስልዮስ ዘቂሳርያ

## ምዕራፍ 2

የኑኃሚን ቤት ባዶ ነው። የሚያርስ ባል የላትም። ስለዚህ አንድ ነገር መደረግ ነበረበት።

ሩት የባልዋ ዘመድ ወደሚሆነው ወደ ቦኤዝ እርሻ ተሰማራች። ቦኤዝ የመድኃኔዓለም ምሳሌ ነው። ቦኤዝ ማለት «ብርታት፣መስማማት፣ኃያል፣ባዕለጸጋ» ነው። ጌታችንም «ድንቅ፣መካር፣ኃያል» ተብሏል። /ኢሳ.9÷6/። ቦኤዝ በእርሻው ሠራተኞች አሠማርቷል። ጌታችንም ምእምናንን እርሻ በተባለች ዓለም አሠማርቷልና። ቦኤዝ የመድኃኔዓለም ምሳሌ ነው። በእርሻው በቤተክርስቲያን ምእመናንን ተቀብሎ ያሠማራ ብርቱና ኃያል ባዕለጸጋ አምላክ ነውና። ሩት ሁሉን ትታ መጣች። ሁሉ ካለው አምላክ እርሻ ውስጥ ተሠማራች። የራስዋን ተወች። የእግዚአብሔርን ፍለጋ ተሠማራች።

የተሠማራችበት ሥራ አድካሚ አስልቺና አስቸጋሪ ነበር፤ ቃርሚያ። መቃረም ማለት ገበሬዎች ሲያጭዱ ያለፉትን የእህል ቅሪት መልቀም ነው። በኦሪት ሕግ «ቃርሚያ ለመጻተኛና ለድኻ አደግ ለመበለትም ይሁን።» /ዘዳ.24÷19–22/ ተብሎ ስለታዘዘ ገበሬዎች ቃርሚያውን ይተውት ነበር። ከላይ ፀሐይ ከታች ዋዕይ አለ። ወደ ቤተልሔም ስትገባ ሁሉ በእጇ ሁሉ በደጅዋ ተመቻችቶ አልጠበቃትም፤ ድካም፣ ትግል ነው የጠበቃት። ነገር ግን ያለ ምሬትና መሰልቸት ተወጣችው። የአጫጆች አዛዥ እንኳን «ከማለዳ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ቆይታለች። ጥቂት ጊዜ እንኳን አላረፈችም» ሲል ነበር የመሰከረላት። ሩት 2÷7።

አንዳንድ ሰዎች ወደ መንፈሳዊ ኑሮ ሲመጡ በአንድ ቀን የሚለወጡ፣ ፈተና ከአሁን በኋላ የማይነካቸው፣ ሁሉም ነገር ባሰቡት መልክ የሚቃናላቸው፣ መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ የሚሆን ይመስላቸዋል። ሌሎች ደግሞ ስለተመለሱ ስላመኑ ብቻ በጸሎት፣ በጾም፣በማስቀደስ፣ራስን በመግዛት...መጋደል የቀረላቸው መስሎ ይሰማቸዋል።

እውነቱ ግን ይህ አይደለም። የእስራኤል ዘነፍስ ምሳሌ የሆኑት እሥራኤል ዘሥጋ ወደ ከነዓን የገቡት በተጋድሎ ነው። በዘመነ ዕዝራና ነህምያ እሥራኤል ከፋርስ የተመለሱት በተጋድሎ ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልጋል።» በማለት ያስተማረው። የሐዋ.14÷22።

ወደ እግዚአብሔር መጣን ማለት ወደ ቤተክርስቲያን ቀረብን ማለት፣ መማርና ማስቀደስ፣መጾምና መጸለይ ጀመርን ማለት፣ ዓለምን ድል አድርገን አክሊልን ለመቀበል ተዘጋጀን ማለት አይደለም። ተጋድሎ ጀመርን ማለት ነው እንጂ። ዓለምን ለማሸነፍ ኃይል ያስፈልጋል። ያ ኃይል ደግሞ የሚገኘው በድካም ነው። «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና።» 2ቆሮ.12÷10።

ያለ ዕረፍት ተጋች። ከጠዋት እስከማታ ያለ ዕረፍት እንትጋ፥ የምንሻውን ለማግኘት ራሳችንንም ዓለምንም ድል ለመንሣት ያለ ዕረፍት እንትጋ። ጥቂት ድል አገኘን ብለን እንዝናና ወይም ደግሞ ጥቂት ሠራን ብለን እንሰልች። የዕረፍት ጊዜ እስኪሰጠን ድረስ እንጋደል። ቅዱሳን አበው እግዚአብሔር ዕረፍት እስኪሰጣቸው ሳያርፉ ሳይሰለቹ ደከሙ፤ ኃይልና ጸጋ በድካም እንደሚገኝ ዐውቀዋልና።

ቦኤዝ ምስክርነቱን ከአጫጆች አዛዥ ተቀበለ። እግዚአብሔር ስለኛ የቅዱሳንን ምስክርነት ይሰማል። የጠባቂ መልአክን ምሥክርነት ያዳምጣል። ሩት ወደ ሥራዋ ስትሠማራ ቃርሚያ ለመልቀም እንጂ ስለ እራስዋ ለማንም አልተናገረችም። ማንነቷን ሥራዋ መሰከረላት። በአጠገብዋ ያልነበረው ቦኤዝ እንኳን «ባልሽ ከሞተ በኋላ አባትሽንና እናትሽን የተወለድሽበትንም ምድር ትተሽ ቀድሞ ወደ ማታውቂው ሕዝብ እንደመጣሽ፣ ለአማትሽም ያደረግሺውን ነገር ሁሉ ፈጽሞ ሰምቻለሁ።» ነበር ያላት ሩት. 2÷11። ከፍሬዋ ታወቀች። ሥራዋ መሰከረላት ብርሃንዋ በሰዎች ፊት በራ። እርስዋ አልተናገረችም፤ አዛዡና ቦኤዝ መሠከሩላት።

ቅዱሳን ስለራሳቸው ክብርና ዝና ተናግረው አያውቁም። ሌሎች ቅዱሳንና እግዚአብሔር ግን ይመሰክሩላቸዋል። ሩት ስለራስዋ «እኔ እንግዳ ነኝ» ነበር ያለችው። ሩት2÷10። ከባርያዎችህ እንደ አንዱ ልታደርገኝ ፈቀድክ» ብላ ነበር የተደሰተችው። ባለሟልህ ለምን አላደረግኸኝም ብላ ቅር አልተሰኘችም። መጥምቀ መለኰት ቅዱስ ዮሐንስ ስለራሱ ሲናገር በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ፣የእግሩን ጠፍር ልፈታ የማይቻለኝ፤ እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ይገባል» ነበር ያለው /ዮሐ.1÷23-28፤3÷30/ መድኀኔዓለም ጌታችን ግን ስለ ዮሐንስ መሠከረለት «እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበር» ሲል ዮሐ.5÷35።

ሩት የእምነት የተስፋና የፍቅር ሰው ብቻ አይደለችም። እነዚህን የያዘ ሰው የሚያገኛቸው ታዛዥነትና ትኅትና ነበሯት። በማታወቀው ሀገር ለአማትዋ ታዝዛ ቃርሚያ ለመልቀም ተሠማራች። የምታገኘውን እያንዳንዱን ጸጋ በትኅትና ከስግደት ጋር ትቀበለው ነበር። በግምባርዋም ስገደችለት– «እኔንስ ለመቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስ አገኘሁ?» ነበር ያለችው። /ሩት 2÷10/ ይገባኛል አላለችም፣ አይበቃኝምም አላለችም። ላገኘችው ነገር ሁሉ በትኅትና ታመሰግን ነበር።

ከዓለም ስንመለስ ነፍሳችን ተጠምታ ነው የምትመጣው። ርካታን ትሻለች። ስለዚህም «እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ዘወትር አይጠማም» ዮሐ. 4÷14 ይለናልና ነፍሳችን ትረካ ዘንድ፣ ከዛለችበት የሞት አፋፍ ትመለስ ዘንድ የሕይወት ውኃ ቃለ እግዚአብሔር የዘወትር መጠጧ መሆን አለበት። «ጐበዛዝቱ ከቀዱት ውኃ ጠጭ።» ሩት 2÷10

ገበሬዎች ዘሩ። አጫጆች አጨዱ። ሩት ደግሞ ሰበሰበች። አልዘራችም ፣አላጨደችም ነገር ግን ሰበሰበች። ጐበዛዝቱ ቀዱ ÷ ሩት ደግሞ ጠጣች። ወንዝ አልወረደች፣ አልቀዳችም ነገር ግን ጠጣች። ወንጌል እንዲህ ይላል «አንዱ ይዘራል÷ አንዱም ያጭዳል...እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ። ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ።» ዮሐ.4÷38።

ጐበዛዝቱ አበው እጅግ ደከሙ። የእምነት እርሻ አርሰው የጥበብና የጸጋ መከር አፈሩ። ዛሬ እኛ በድካማቸው ገብተን የጻፏቸውን መጻሕፍት እናነባለን፣ በሠሩት ቤተክርስቲያን እናስቀድሳለን። ባዘጋጁት ጸሎት እንጸልያለን። ባገኙት ቃል ኪዳን ምሕረት እናገኛለን። እነርሱ ደከሙ እኛም በድካማቸው ገባን። በአባቶች ድካም ብንገባም የአባቶችን ሀብት ብንቀበልም ለመዳን የሰው ድርሻ አለውና ለሚዘንበው ዝናብ አርሰን፣ለሚወጣው ፀሐይ ውጭ ወጥተን፣ለሚሰጠው ሕክምና ካርድ አውጥተን መጠበቅ ግን አለብን። ሩት ያልደከመችበትን ብትቃርምም ወደ እርሻው መሄድ መልቀምና መሰብሰብ ግን ነበረባት።

ምንም እንኳን ለተጋድሎና ለድካም ብንጠራ ድካማችን ግን ታናሽ ነው። ዘርተው ያበቀሉትን ከመቃረም ቀድተው ያስቀመጡትን ከመጠጣት ያለፈ አይደለም። ነገር ግን ይህ አድክሞን የቀረን ስንቶቻችን ነን?

ትጉኂ ሩት በምሳ ሰዓት ደግሞ ሌላውንና ታላቁን ስጦታ አገኘችው። «ወደ ዚህ ቅረቢ ምሳ ብይ እንጀራሽንም በሆምጣጤ አጥቅሽ አላት» ተባለች። ሩት. 2÷14።

ከጌታዋ ማዕድ ትበላ ዘንድ ተፈቀደላት። «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ። ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደርሱ እገባለሁ÷ከርሱም ጋር እራት እበላለሁ። እርሱም ከኔ ጋር ይበላል።» ራእይ.3÷20።

የእግዚአብሔር የአባታችን ማዕድ ሥጋውና ደሙ ነው:: የእግዚአብሔር የጌታችን ማዕድ ጸጋው በረከቱ ነው:: ይህ የማዕከላዊነት ደረጃ ነው:: የእግዚአብሔርን ማዕድ የምንበላበት የጸጋና የበረከት ተሳታፊ የምንሆንበት ለኛ ብቻ አይደለም:: በልታም ጠግባ አተረፈችም /ለአማትዋ/ ለተራበችው አማትዋ፣ ለደከመችው አማትዋ አተረፈች::

ወደ እግዚአብሔር ማዕድ ስንቀርብ እናተርፋለን:: ለኛ ብቻ አይደለም ለሌሎችም:: ቅዱሳን ተመግበው አትርፈውልናል:: መጻሕፍቶቻቸውን፣ቃልኪዳኖቻቸውን፣ የኑሮ መንገዳቸውንና፣ ጸሎታቸውን ቅዱሳን መካኖቻቸውን አትርፈውልናል:: ለኛ ለደከምነው ለተራብነው:: እኛም ይህ ይጠበቅብናል:: ለልጆቻችን፣ ለዘመዶቻችን፣ ለወገኖቻችን፣ ለጓደኞቻችን ለተማሪዎቻችን ማትረፍ:: ባል ለሚስት÷ ሚስት ÷ለባል ማትረፍ::

በዚህ ደረጃ ማዕዱን ብቻ አይደለም የምናገኘው:: «ቦኤዝም ጐበዛዝቱን– በነዶው መካከል ትቃርም÷ እናንተ አታሳ ፍሩአት ደግሞ ከነዶው አስቀርታችሁ ተዉላት:: እርስዋም ትቃርም» ሩት.2÷16:: በመጀመሪያ እንድትቃርም ብቻ ነበር የተ ፈቀደላት:: አሁን ግን እንዲያፈሱላትም ተፈቀዶለት:: ከበፊት ይልቅ አሁን ድካምዋ ቀነሰ» ጸጋው በዛላት:: ወገኖች ወደ እግዚአብሔር በቀረብን ቁጥር ጸጋው እየበዛልን ይሄዳል:: ክርስትና አንድ ቦታ ገብቶ ተቀምጦ መቅረት አይደለም:: የዕለት ተዕለት ጉዞ የዕለት ተዕለት ተጋድሎ ነው:: ከኃይል ወደ ኃይል፣ ከጸጋ ወደ ጸጋ፣ ከክብር ወደ ክብር መሸጋገር ነው:: እንዲህ ከተጓዝን ድካማችን እየተቀነሰ ቸርነቱ እየበዛልን ይሄዳል::

ለዚህ ነው በቅዱሳን ታሪክ መካከል አናብስት ሲታዘዙላቸው፣አዕዋፍ ምግባቸውን ሲያመጡላቸው፣ ምንጮች ከዐለት ሲፈልቁላቸው የምናየው:: ነገር ግን ጸሎት፣ጾምና ተጋድሎ አልቀረላቸውም::

ድካም ተቀንሶላታል /ግን አልቀረላትም/ ቸርነት በዝቶላታል:: ስለዚህ ብዙ ቃረመች:: «አማትዋም የቃረመችውን አየች::» ሩት.2÷18:: የክርስትና ጉዞ ትልቁ ነገር መቃረሙ ብቻ አይደለም:: የትነው የቃረምነው የሚል ነው? ለዚህ ነው ኑኃሚን «ዛሬ ወዴት ቃረምሽ?» ስትል የጠየቀቻት:: አያሌ ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን እየተማሩ መሆኑን፣ እያ ስተማሩ መሆኑን፣ እየጸለዩ መሆኑን፣ እያገለገሉ መሆኑን፣ ገንዘባቸውን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ይናገራሉ:: መልካም:: ግን የት?

በየትኛው እርሻ? ታላቁ ባስልዮስ በደረሰው ውዳሴ አምላክ በተሰኘው ጸሎት ነፍሱን እንዲህ ይላታል:: «በማናቸው እርሻ ሊያውሉሽ ተቃጠሩሽ፣ በማናቸው ማዕረግ ተቃጠሩሽ፣ በባለ ሠላሳ ነው? በባለ ስድሳ ነው? በባለ መቶነው? /ውዳሴ አምላክ ዘዘወትር/

በማሳዎች ውስጥ ለቃርሚያ ተሰማርተን ይሆናል:: ነገር ግን ከቦኤዝ እርሻ ውጭ እንዳንገኝ አደራ:: ነቀዝ የበላው ትል የቆረጠመው እህል እንዳንቃርም አደራ:: ዲያብሎስ አስመስሎ በዘራው ማሳ ውስጥ በማወቅም ይሁን በየዋህነት ገብተን ዋጋ አልባ ድካም እንዳንደክም አደራ::

ወላጆች ልጆቻቸውን፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን፣ካህናት ምእመናንን ወዴት ቃረማችሁ? ብለው መጠየቅ አለባቸው:: አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው የትም ት/ቤት ቢማሩ ግድ የላቸውም:: ብቻ አንዳንድ የማይፈልጓቸው ጠባዮች እስካላሳዩ ድረስ:: ግን ምን እንደቃረሙ አያረጋግጡም::

እህሉ ብቻ ሳይሆን እርሻው ወሳኝ ነው:: ትክክለኛውን ቃርሚያ ለመቃረማቸው ምስክሩ በትክክለኛው እርሻ ላይ ተሠማርተው መዋላቸው ነውና:: ያለበለዚያ ከእሾህ ወይን፣ከኩርንችት በለስ አይለቀምም:: ማቴ.7÷16::

ኑኃሚንም ለሩት የመከረቻት ይኼንኑ ነው:: «ልጄ ሆይ ከገረዶቹ ጋር ብትወጭ በሌላም እርሻ ባያገኙሽ መልካም ነው::» ሩት.2÷22:: ቅዱሳን መላእክት ወደ አምላካችን ሊወስዱን ሲመጡ በሌላ እርሻ እንዳያገኙን አምላክ ሆይ ጠብቀን::

ኑኃሚን በወለደቻቸው ልጆች ያላገኘችውን ዕረፍት እግዚአብሔር በሰጣት «ልጅ» አገኘችው:: የእግዚአብሔር ስጦታ ከሁሉም በላይ ነውና:: አብርሃም እንደ ሥጋ በወለደው እስማኤል ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው ይስሐቅ በረከትን አገኘ:: በሰው ጥበብና ሥጋዊ ጥረት መንፈሳዊ በረከት አይገኝም:: የሚገኘው ድካምና መባዘን ብቻ ነው:: ወደ እግዚአብሔር ስንመለስ ግን ያጣነውን ነገር ከእርሱ እናገኘዋለን:: ያም ፍጹምና በቂ ነው::

## ምዕራፍ 3

«ልጄ ሆይ መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍትን አልፈልግሽምና::» ሩት3÷1 በቤተክርስቲያን መከር የተሠማራን ሁሉ መልካም ይሆንልን ዘንድ ዕረፍትን እንፈልግ:: ደከመን ፣ ሰለቸን፣ታከተን፣በቃን አንበል:: ያለበለዚያ ጊዜውን ጠብቆ እግዚአብሔር የሚሰጠንን በረከት እናጣዋለን:: እስቲ ሩትን እንከተላት:: ቢሰለቻት ቢታክታት ኖሮ ታጣው የነበረውን ታላቅ ጸጋ እንመልከት::

«ቦኤዝ በአውድማው ገብሱን በመንሽ ስለሚበትን ታጠቢ፣ ተቀቢ፣ ልብስሽን ልበሽ፣ በሌሊት ዕንቅልፍ ሲወስደው ገልጠሽ በእግሩ ሥር ተኚ» ይህ የኑኃሚን ትዕዛዝ ነው::

ቅን ታዛዥዋ ሩት «የተናገርሽኝን ሁሉ አደርጋለሁ» አለች ሩት.2÷2–5:: እስካሁን ድረስ በተሰጣት ትዕዛዝ ስትከራከር ወይም ስታንጐራጉር አልተሰማችም:: ተቀብላ ከመፈጸም በቀር መታዘዝ ከመሥዋዕት እንደሚበልጥ ተረድታለች:: ተስፋ ያደረገችው አምላክ የታመነ መሆኑን አምናለች:: /1ሳሙ.15÷22፣ዕብራ.11÷11/::

«ሩትም በቀስታ መጣች፣ እግሩንም ገልጣ ተኛች::» ሩት3÷7 ይህ ታላቁ የክርስትና ደረጃ ነው:: እግሩን ገልጣ ማየቷ ውስጠ ምሥጢሩን የማየትዋ ምሳሌ ነው:: ዕንቅልፍ የሞት ምሳሌ ነው:: በሞት እንደምትመስለው ተናገረች:: ቅዱስ ጳውሎስ ለሮማውያን በላከው መልእክቱ «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?» ሮሜ.8÷3–4 በማለት ያስተማረንም ይኸንን ነው::

ክርስትና ማለት ከሰቃዮች ወገን ርቆ ከተሰቃዩ ወገን መቆም ነው:: እኛ የእግዚአብሔር ዘመዶች ወገኖቹ ነን:: /የሐዋ.17÷28/:: በሞቱ እንመስለው ዘንድ ይገባናልና:: ምክንያቱም አብረነው ከሞትን አብረን እንቀበራለን:: አብረን ከተቀበርን አብረን እንነሣለን:: ሞቱን በሚመስል ሞት ከርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከርሱ ጋር እንተባበራለን:: ሮሜ.6÷5::

ጌታችን በእኩለ ሌሊት እንደተነሣ ለኛም የማይገኘውን ተስፋ የምናደርገውን የመጨረሻው ጸጋ እንደሰጠን÷ ቦኤዝም በመንፈቀ ሌሊት ተነሣ:: ሦስት ነገሮችንም ለሩት ሰጣት::

- *ቡራኬ* – ልጄ ሆይ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ::

- *ቃል ኪዳን* – ያልሽውን ሁሉ አደርግልሻለሁ::

- *እህል* – ስድስት መሥፈሪያ ገብስ ሠፈረላት::

ይህ የፍጹምነት ደረጃ ነው:: ይህ ደረጃ ምሥጢር ይታይበታል:: ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ፣ሕዝቅኤልና ዳንኤል ከብሉይ፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ጳውሎስ ከሐዲስ ለዚህ ምሥጢር በቅተዋል:: ሰማይ ተከፍቶ ሰው ሊያየው የማይችለውን ታላቅ ምሥጢር አይተዋል::

/ኢሳ.6÷1–5፣ ሕዝ.1÷1–28፣ ዳን.7÷9–11፣ የሐዋ7÷56፣ራእይ 4÷1–11፣ 2ቆሮ.12÷1–10/

በቅዱሳን አባቶቻችን ታሪክም ሰማይ ተከፍቶ ምድር ተዘርግቶ ሰው ሊያየው የማይችለውን ድንቅ ምሥጢር ማየታቸው ተጽፏል:: እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከ24ቱ ካህናተ ሰማይ ጋር ሃያ አምስተኛ ሆነው አመስግነዋል::

ይህ ደረጃ ቡራኬ ይገኝበታል:: ይህ ቡራኬ የበጐ ሥራ ምሥክር ነው:: ቦኤዝ ስለሩት «ባለጠጋም ድሃም ብለሽ ጐበዛዝትን አልተከተልሽም» ሲል ጽናትዋንና ለሥጋዋ ምቾትና ፍላጐት ያለመንበርከኳን፣ «በሀገሬ ያሉ ሕዝብ ሁሉ ምግባረ መልካም ሴት መሆንሽን ዐውቀዋል» ሲል ብርሃንዋ በሰው ሁሉ ፊት መብራቱን መስክሮላታል:: ራስዋ አልተናገረችም ቦኤዝ እንጂ:: የቅዱሳንንም ሥራ እግዚአብሔር ይመሰክርላቸዋል:: በተአምራት፣

በጽሎተ፣ በቀዱሳን መካናተ እግዚአብሔር ጽድቃ ቸውን ይመሰክራል:: ለኛም እንዲሁ:: ለሩት እንደተነገረ «ከፊተኛው ይልቅ በመጨረሻው ጊዜ ቸርነት አድርገሻል» ሩት. 3÷10:: እንደተባለች በመልካም ጀምረን በክፉ፣ በጽድቅ ጀምረን በኃጢአት፣ በድ ንግልና ጀምረን በዝሙት፣ በእምነት ጀምረን በክህደት፣በአገልግሎት ጀምረን በንዝህ ላልንት ካልፈጸምን ከፊተኛው ይልቅ እያበዛን በመጨረሻ የምንሠራው ከበለጠ ይመሰክርልናል:: የአባታችን በረከቱም ይሰጠናል::

ይህ ደረጃ ቃል ኪዳን ይገኝበታል:: «ያልሽውን ሁሉ ነገር አደርግልሻለሁ» ምንኛ ደስ ይላል:: ተግታለች፣ ታዝዛለች፣ጸንታለች ደክማለች እና ያልሽውን ሁሉ አደርግልሻለሁ ተባለች» ጸንተን ብንገኝ ፣በመልካም እርሻ ውስጥ ብንገኝ በሥራችን ቢመሠክርልን ያልነው ሁሉ ይደረጋል:: ቅዱሳን ያሉት ሁሉ ተደር ጐላቸዋል:: የለመኑትን ሁሉ አግኝተዋል:: የጠየቁት ሁሉ ተመልሶላቸዋል:: በየመጽሐፈ ገድላቸው መጨረሻ «ኃጥአንን ማር ልኝ» ሲሉ ለጠየቁት ጥያቄ «እምርላች ኋለሁ» የሚል ምላሽ አግኝተዋል::

«እኔ ዋርሳ እሆንሻለሁ» ነበር ያላት ቦኤዝ:: በሥጋ መንገድ እንደ እኅቷ ብትጓዝ ኑሮ ባል አታጣም ነበር:: ያ ባል ግን በረከት አያመጣላትም:: በኋላ የምናየውን ጸጋ አያስገኝላትም:: ሥጋዊ ፍሬ እንጂ መንፈሳዊ ፍሬ አታፈራበትም:: አሁን ግን እንደ መንፈሳዊ ፈቃድ በመታዘዝ ተጓዘች:: ስለዚህም እግዚአብሔር የሚበልጠውን ሊሰጣት ቃል ገባላት::

ቸርነት በወጣኒነቷ ትቃርም ነበር:: በማዕከላዊነቷ ከሚያጭዱት እያፈሰሱላት ድካም ተቀንሶላት ነበር:: አሁንስ? አሁንማ የለበሽውን ኩታ አምጥተሽ ያዥው አላት:: በያዘችው ጊዜ ስድስት መሥፈሪያ ገብስ ሰፈረላት:: ያለድካም ያለቃርሚያ ከዚህ በፊት ቀኑን ሙሉ ስትቃርም ውላ የምታገኘው «አንድ የኢፍ መሥፈሪያ» ነበር ሩት.3÷17:: አሁን ግን ስድስት መሥፈሪያ ስድስት ጊዜ እጥፍ:: ስለ ሥራዋ የተከፈላት አይደለም ስለቸርነቱ::

የእግዚአብሔር ቸርነት ከሰው ሥራ ይበልጣል:: እኛ በመውጣትና በመውረድ ከምናተርፈው የበለጠ የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታው ይበልጣል:: ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመጨረሻ ያገኙት ስድስት ክንፍ ያገኙት ቃልኪዳን ከመጀመሪያ የድማካቸው ፍሬ በእጅጉ ይበልጣል:: ይህ የፍጹምነት ደረጃ ነው::

በክርስትና ኑሮ ለጸኑ እስከ መጨረሻው ለተጋደሉ፣በድካማቸው ከሰበሰቡት ስድስት ጊዜ እጥፍ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሚሰጣቸው ጊዜ አለ:: ያ ግን በአንድ ቀን በአንድ ጀምበር አይገኝም::

እሥራኤል ያላገኙትን በረከት ነው ሩት ያገኘችው:: በትጋት በጽናት፣ በመሻትና፣ በመታዘዝ:: ተስፋ ያደረገችው አምላክ አላሳፈራትም:: ሁሉ ንም ነገር ግን በአንድ ጊዜ አልሰ ጣትም:: የነሣት ነገር ግን የለም:: እግዚአብሔር የታመነ በመሆኑም የሚ ነሣን ነገር አይኖርም:: ሁሉንም ግን በአንድ ጊዜ አይሰጠንም::

ኑኃሚን ምን ነበር ያለቻት? «ልጄ ሆይ ሰውየው ይህንን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍምና ፍጻሜው እስኪታወቅ ዝም በይ::» ሩት 3÷18:: አቤት ትኅትና አቤት ትዕግሥት:: «ዝምበይ ለምን ፍጻሜው እስኪታወቅ–የአባቶቻችንም ክብራቸው የተገለጸው ገድላቸው የተጻፈው ገዳማቸው የተከበረው ተአምራታቸው የታወጀው በመጨረሻ ነው:: እንዲያውም ካረፉ በኋላ ፍጻሜው ሲታወቅ:: ፍጻሜው ሳይታወቅ ምንም አንናገር የምንናገርበት የራሱ ጊዜ አለውና:: ሐዋርያት ዝም በሉ ለማንም አትናገሩ የተባሉበት ጊዜ ነበር:: ሂዱና ለአሕዛብ ሁሉ ንገሩ የተባሉበት ጊዜ እስኪደርስ:: የዝምታ ጊዜ አለ:: የመግለጥ ጊዜ አለ::

## ምዕራፍ 4

በኦሪት ዘዳግም 25÷5 «ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ፤ ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ... ከእርስዋ የሚወለደው በኩር ልጅ በሞተው ወንድሙ ስም ይጠራ::» በተባለው መሠረት ቦኤዝ ለአቤሜሌክ ከርሱ ይልቅ የሚቀርበውን ወንድም ፈለገና:: «የወንድማችንን የቦኤዝን እርሻ ዋጀው» ሲል ጠየቀው:: እርሱም እሺ እዋጀዋለሁ አለ:: ቦኤዚም ርስቱን የምትዋጅ ከሆነ ሚስቱን ሩትንም ማግባት አለብህ አለው:: በዚህ ጊዜ ግን «መቤዠት አልችልምና መቤዠቱን አንተ ውሰድ» አለው:: ሩት4÷1–6::

መሬቱን ፈለገው ሩትን ግን አልፈለጋትም:: ዓለም እንደዚህ ነው የኛ የሆነውን እንጂ እኛን አትፈልገንም:: ውበታችንን፣ ገንዘባችንን፣ ጉልበታችንን፣ዕውቀታችንን ትጠቀምበታለች:: ከዚያ በኋላ እንደ አረጀ ቁና ትወረውረናለች:: የኛ ስለሆነው እንጅ ስለኛ ግድ የላትምና:: ስለኛ የሚጨነቀው የኛ ቦኤዝ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

ቦኤዝ ግን እንዲህ አለ «ለአቤልሜሌክና ለኬሌዎን ለመሐሎንም የነበረውን ሁሉ ከኑኃሚን እጅ እንደገዛሁ እናንተ ዛሬ ምስክሮች ናችሁ:: ደግሞም የሟቹ ስም ከወንድሞቹ መካከል ከሀገሩም እንዳይጠፋ የሟቹን ስም በርስቱ ላይ እንዳስነሣ የመሐሎንን ሚስት ሞዓባዊቱን ሩትን ሚስት ትሆ ነኝ ዘንድ ወሰድሁአት:: እናንተ ዛሬም ምስክሮች ናችሁ አላቸው::» ሩት. 4÷10::

ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል ብላ መጣች:: «ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ» ዘዳ.23÷3:: የተባለው ሕግ አላ ገዳትም:: ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ገባች:: ሕግና እምነት፣ ተስፋና ፍቅር አሸ ነፈው:: ሩት ሞዓባዊነቷ በዘር እንጅ በም ግባር አልነበረም:: በዘር ሞዓባዊት ብት ሆንም በምግባር ከእስራኤል በልጣ ተገ ኝታለች::

ክርስቲያን የሚያሰኘን ሃይማኖ ታችንና ምግባራችን እንጂ ከክርስቲያን ቤተሰብ መወለዳችን ብቻ አይደለም:: እንደ ሩት ከሩቅ የሚመጡ ወገኖች አሉ:: የክርስትና እምነት ካልተሰበከበት፣ቅዳሴ ካልተቀደሰበት፣አድባራት ገዳማት ከሌሉበት ጉባኤና ትምህርት ካልሰፋበት ማኅበረሰብ፣ አካባቢ፣ሀገር የሚመጡ አሉ:: ከእኛ ቀድመው የጸጋው ባለቤቶች የመን ግሥቱ ወራሾች የሚ ሆኑ::

«ብዙዎች ከምዕራብና ከምሥራቅ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ:: የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወዳለው ጨለማ ይጣላሉ::» ማቴ.8÷11::

ሽማግሌዎቹ ሩትን ምን ብለው ነበር የመረቋት:: «እግዚአብሔር ይህችን ወደ ቤትህ የምትገባውን ሴት የእሥራኤልን ቤት እንደሠሩ እንደሁለቱ እንደ ራሔልና ልያ ያድርጋት» ሩት4÷11:: ራሔልና ልያ የአሥራሁለቱ የእሥራኤል ነገድ እናቶች ናቸው:: በእምነት የመጣችው ሞዓባዊት የእሥራኤል መሠረት ከሆኑ እናቶች ጋር ተጠራች:: እግዚአብሔር ከለመነችው ተስፋም ካደረገችው በላይ እንደሰጣት ተመልከቱ::

«አንተም በኤፍራታ ባለጠጋ ሁን ስምህም በቤተልሔም ይጠራ» የዳዊት ከተማ ናት ቤተልሔም:: የዳዊት ጥንተ አያት ነው ቦኤዝ:: የጌታችን የልደት ከተማ ናት ቤተልሔም:: የጌታችን ጥንተ አያት ነው ቦኤዝ:: በኤፍራታ ተጠራ::

«ቤትህም እግዚአብሔር ከዚህች ቆንጆ ከሚሰጥህ ዘር ትዕማር ለይሁዳ እንደ ወለደችው እንደ ፋሬስ ቤት ይሁን::»

ትዕማርም የተናቀች ሴት ነበረች:: እግዚአብሔር ግን አከበራት የጌታችን የዘር ሐረግ የተጠራበትን ፋሬስንም ወለደች /ዘፍ.38/ ሩትም እንዲሁ ከተናቀው ዘር ከሞዓብ መጥታ በጌታችን የዘር ሐረግ የተጠቀሰች ታላቅ ሴት ሆነች::

ኑኃሚን ምን ብላ ነበር:: «ተስፋ አለኝ ብል ዛሬ ሌሊትስ እንኳ ባል ባገባ ወንዶች ልጆችም ብወልድ:: እነርሱ እስኪያድጉ ድረስ ትቆያላችሁን?» ሩት 1÷13:: ኑኃሚን ተስፋ ቆርጣ ነበር:: በመጀመሪያም ወደ ሞዓብ የተጓዘችው በረሃብ ምክንያት ቤቷ ባዶ ቀርቶ ዘር እንዳታጣ ነበር:: ነገር ግን አልቀረ ላትም:: ሞዓብ ከሞት አላዳናትም:: ብቻ ዋን ከመቅረት አላዳናትም:: በገዛ ጥበቧ ያደረገችው ሁሉ ከከንቱነትና ተስፋ ከመቁረጥ በቀር ያተረፈላት ነገር አልነበረም::
በሥራ ፍለጋ፣ሚስት /ባል ለማግኘት፣ ልጅ ለመውለድ፣ሥልጣን ለመ ያዝ ሀብት ለማፍራት ታዋቂ ለመሆን ሲሉ የዚህን ዓለም መንገድ የሚመርጡ አሉ:: ነገር ግን አያገኙትም:: ምናልባት 10 ዓመት ሲያለፋቸው በሚ ያገኙዋት ጥቂት ነገር ተስፋ በማድረግ ይደክሙ ይሆናል በመጨረሻ ግን ውጤቱን ያውቁታል:: የፈሩት ይደርሳል÷ የጠሉት ይወርሳል:: አስቀድመው ጽድቅን ቢፈልጉ ግን የቀረው ሁሉ በተጨ መረላቸው ነበር:: ማቴ. 6÷33::

/ወደ ገጽ 14 ዞሯል/

# ጸሎተ ሃይማኖት

ባለፈው እትማችን በዚህ ርእስ «ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከእርሱ ጋር የነበረ »እና «የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ» በሚሉት ርእሶች ዙሪያ ሰፋ ያለ ትምህርት ማቅረባችን ይታወሳል:: ዛሬ ደግሞ «ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፤» «የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፤» «በባሕርይው ከአብ ጋር የተካከለ» በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ መጠነኛ ትንታኔ እናቀርባለን:: በተከታታይ እያቀረብነው ስላለው ስለዚህ ጽሑፍ ያላችሁን አስተያየት እንድትሰጡንም እናሳስባለን::

## «ብርሃን ዘእምብርሃን፤ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን»

«እግዚአብሔር ብርሃን ነው::» 1ዮሐ.1÷5:: እግዚአብሔር ብርሃን ነው ስንል የሚታየውን ብርሃን ማለታችን ሳይሆን ከዚህ በላይ የሆነ በመንፈሳዊ ዐይን ብቻ የሚታይ ብርሃን ማለት ነው::

ይህ ብርሃን ልዩ በመሆኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤» ሲል ገልጦታል። 1ጢሞ.6÷16:: የእግዚአብሔር ብርሃንነት የባሕርይ ገንዘቡ ስለሆነ በምድር ላይ የሚያበሩት ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ሳይፈጠሩ /ዘፍ. 1÷14–19/ ከዚያም በፊት ብርሃን ይሁን ከማለት አስቀድሞ /ዘፍ. 1÷3–5/ እርሱ በብርሃንነቱ ነበረ:: ለዚህም ነው «እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም» የተባለው 1ዮሐ.1÷5::

በጸሎተ ሃይማኖት ቀጥለን የምናገኘው «ብርሃን ዘእም ብርሃን አምላክ ዘእም አምላክ ዘበአማን÷ዘተወልደ ወኢኮ ዘተገብረ፤ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ» የሚለውን ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን ነው:: ትርጓሜውም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፤ በባሕርይው /በመለኮቱ/ ከአብ ጋር የተካከለ ማለት ነው:: እነዚህ አባባሎች የሚያመለክቱት ወልድ በባሕርይ፣በሕልውና በምንም በምን ከአባቱ የማያንስ ወይም የማይበልጥ ፍጹም ትክ ክልነት ያለው መሆኑን ነው::

በዚህም አንቀጽ ውስጥ

1. ከብርሃን የተገኘ ብርሃን
2. ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ
3. የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ
4. በባሕርይው ከአብ ጋር የተካከለ ነጥቦችን በአጭሩ እንመለከታለን::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ:: የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም::» ሲል እንደተናገረ እርሱ የዓለም ብርሃን ነው:: ዮሐ.8÷12፣ 9÷5:: መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስም «ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን» በማለት ስለጌታችን ተናግሯል:: ዮሐ. 1÷9::

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችን ብርሃንነት የባሕርይው /ከማንም ያልተቀበለው ገንዘቡ/ መሆኑን ሲያስረዳ እውነተኛ ብርሃን ብሎታል:: ታዲያ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ማለት ለምን አስፈለገ ሊባል ይችላል? ብርሃንነት ገንዘቡ ሲሆን ሳለ ከአብ የተወለደ መሆኑን ለመግለጥ ነው:: ጌታችን ከአብ ተወለደ በማለታችን ብርሃንነቱ የሚያንስ አይደለም:: ይህም ከአንዱ የጧፍ መብራት ሌላውን እንደ ማቀጣጠል ያለ ነው:: ሁለቱም የተቀጣጠሉት መብራቶች ያላቸው ብርሃንም ሆነ ጠባይ አንድ ዓይነት እንደሆነ ሁሉ ከአብ የተወለደው ወልድም እንደ መብራቱ መቀዳደም ሳይኖር በባሕርይው ÷ በሕልውናው አንድ መሆኑን ይገልጣል::

ከአንድ የጧፍ መብራት ሌላውን እንደማቀጣጠል ነው ሲባል እንደ መብራቶች በመካከላቸው መቀዳደም ይኖራል ማለት ሳይሆን ከአንዱ መብራት የተቀጣጠለው ሌላኛው መብራት በባሕርይው በጠባዩ ከመጀመሪያው በምንም የማይለይ መሆኑን ለማስረዳት ነው:: ብርሃንነቱ አንድ ነው:: የአንዱ ከሌላው አያንስም፣አይበልጥም:: ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ስንልም ባሕርይው የማይለወጥ፣የማይከፈል፣የማይለይ ነው ማለታችን ነው::

አባ ሕርያቆስ «ሠለስቱ ስም አሐዱ እግዚአብሔር፤ አኮ ከመ አብርሃም ዘይልሕቅ እምይስሐቅ፣ወይስሐቅ ዘይልሕቅ እምያዕቆብ አኮ ከማሁ ለመለኮት ኢይልሕቅ አብ እምወልዱ÷ወወልድኒ ኢይልሕቅ እመንፈስ ቅዱስ:: በስም ሦስት በእግዚአብሔርነት አንድ ይባላሉ:: አብርሃም ከይስሐቅ እንደሚበልጥ /እንደሚቀድም/ ይስሐቅም ከያዕቆብ እንደሚቀድም /እንደሚበልጥ/ ለመለኮት እንደዚህ አይደለም:: አብርሃም ከይስሐቅ እንደሚቀድም /እንደሚበልጥ/ አብ ከልጁ የሚበልጥ የሚቀድም አይደለም፤ ይስሐቅ ከያዕቆብ እንደሚቀድም እንደሚበልጥ ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ የሚበልጥ /የሚቀድም/ አይደለም» ሲል ሕልውናቸውን ገልጦታል:: /ቅዳሴ ማርያም/::

በማቴዎስ ወንጌል ቅዱሳን ሐዋርያትም «የዓለም ብርሃን ናችሁ» ተብለዋል:: ማቴ.5÷14:: የእነርሱ ብርሃን ነት ግን ከጌታችን ብርሃንነት ይለያል:: የጌታችን ብርሃንነት የባሕርይው ሲሆን የቅዱሳን ግን የጸጋ /ከጌታችን የተቀ በሉት/ ነው:: ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ «እውነተኛው ብርሃን» ያለው ይህንንም በፀሐይና በጨረቃ ልንመስለው እንች ላለን:: ፀሐይ ብርሃን የምታመነጨው ከራሷ ሲሆን ጨረቃ ግን የራሷ ብርሃን ስለ ሌላት ከፀሐይ ተቀብላ ታበራለች:: ጨረቃ ያለ ፀሐይ ብርሃን መሆን አትችልም:: ቅዱሳንም ብርሃን የተባሉት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ጸጋ እና በረከት ተሳታፊዎች በመሆናቸው ከእርሱ በተቀበሉት ብርሃን ነው:: ያለ ክርስቶስ በራሳቸው ብርሃን ሊሆኑ አይችሉም::

ወንጌላዊው ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ /መጥምቁ ዮሐንስ/ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ:: ስለብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ÷ እርሱ /መጥምቁ/ ብርሃን አልነበረም» ብሎ የጌታን ብርሃንነት መስክሯል:: ዮሐ.1÷7:: ዮሐንስ ጌታን ብርሃን ማለቱ መለኮታዊነቱን ያስረዳል::

በዓለም ላይ ተንሰራፍቶ የነበረውን የመረረ የጨለማ ሕይወት በብርሃንነቱ ስለገላለጠ፤ ኃይለ እግዚአብሔር ርቆት ለነበረው በዲያብሎስ ቀንበር ለተጠመደው የሰው ልጅ ወልድ ዋሕድ መልካሙን የምሥራች በመስጠቱ ብርሃን ይባላል:: ስለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ «በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላ ቸው፤» በማለት ተናግሯል:: ኢሳ.9÷2:: ጨለማ በሆነች በሲኦል ተጣለው የነበሩት አዳምና ልጆቹ በእርሱ ብርሃንነት ወደ ገነት ገብተዋልና::

በጨለማ የሚኖር ይፈራል፤ ይደነግጣል፣ መንገድ ይጠፋበታል፣የሚረግጠውን አያውቅም፣ ዕንቅፋት ያገኘዋል፣አውሬም ሊበላው ይችላል ወዘተ:: ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣቱ ግን ፍርሃት ራቀ:: «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው የሚያስፈራኝ ማን ነው?» እንዳለ:: መዝ. 26÷1:: ወደ ገነት እንዳንገባ ዕንቅፋት ሆኖብን የነበረው ዲያብሎስን በመስቀሉ አስወገደልን:: ቆላ.2÷14:: ቅዱስ ዳዊት «ብርሃንህንና እውነትህን ላክ» ሲል የተ ናገረው ስለ ወልድ ነው::

በዓለም ያለው የጨለማ ሕይወት የተገለጠው በእርሱ ነውና:: በትንሣኤው ብርሃን ሞትን ድል አድርጐ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል የትንሣኤ ሙታንን ተስፋ አበራልን:: «አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኵራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል:: ...ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ» እንዲል:: 1ቆሮ.15÷20–22::

ሌላው ብርሃን ይለወጣል፣ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የማይለወጥ ብርሃን ነው:: ስለዚህ እውነተኛ ብርሃን ይባላል:: «ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች» እንዲል:: ሚል.4÷2:: «የጽድቅ» ማለት የእውነት ማለት ነው:: ይህም የተነገረው ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ዲያብሎስ አገዛዝ ላጸናበት በጨለማ ሕይወት ለታሠረው የወጣ እውነተኛ ፀሐይ ነውና:: ስለዚህም አባ ሕርያቆስ «አብ ፀሐይ ነው÷ወልድም ፀሐይ ነው መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ ነው» ሲል ተናግሯል:: /ቅዳሴ ማርያም/::

በጸሎተ ሃይማኖታችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከእውነተኛ ብርሃን /ከአብ/ የተገኘ እውነተኛ ብርሃን እንለዋለን:: የተገኘ ማለት ምንን ያመለክታል? «ተወለደ» ለማለት «ተገኘ» ተባለ:: ከሰው የሚወለድ ሰው ነው፣ ከአዕዋፍ የሚገኙ አዕዋፍ ናቸው:: የተወለደው ወላጁን ያህላል፣ ይመስላል:: የአባቱን ባሕርይና አካል ይዞ ይወለዳል:: ወልድ ከአብ ተገኘ /ተወለደ/ ማለትም አባቱን ያህላል አባቱን ይመስላል ማለት ነው:: ነገር ግን አባት ከልጁ እንደሚቀድም፣በአብና በወልድ መካከል መቅደም መቀዳደም የለም::

የመለኮትን ረቂቅ ልደት ከሰው /ከፍጥረት ልደት/ ጋር ማነጻጸር ወይም ማመሳሰል በርግጥ አይቻልም:: ነገር ግን በሰው አቅም በሰው ቋንቋ ለመግለጥ ያህል ብቻነው:: የወልድ ከአብ መገኘት ከፀሐይ እንደሚወጣ ብርሃን ነው:: ፀሐይ ሦስት አካላት አሏት:: ክበብ፣ ብርሃን /ጮራ/ እና ሙቀት:: ከክበቧ ብርሃንዋ /ጮራዋ/ ይፈነጠቃል፣ሙቀቷ ይወጣል :: ጮራዋ፣ /ብርሃኗ/ ከክበቧ ክበቧ ከብርሃኗ ቀድሞ ተገኝቷል ማለት አይደለም:: በመካከላቸው መቅደም መቀዳደም የለም:: እንደዚህ ሁሉ በብርሃን የተመሰለ ወልድ በክበቧ ከተመሰለ አብ ተገኘ እንላለን:: ነገር ግን ምሳሌ ዘየሐጽጽ ነው:: ስለዚህ ተገኘ ማለት ተወለደ ማለት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል::

## 2. አምላክ ዘእም አምላክ ዘበአማን፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ

አባቱ ሌላ የተወለደው ሌላ እንዳይባል ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ተባለ:: በሌላም በኵል ከትልቁ አምላክ የተገኘ ትንሹ አምላክ የሚል እንዳይኖር እንዲህ አድርገው ሠለሥቱ ምዕት አስቀምጠውልናል:: ወይም ከአምላክ የተገኘ ሌላ ፍጥረት አልተባለም:: ባሕርይው፣ሕልውናው፣ሥልጣኑ ከአባቱ ጋር አንድ እንደሆነ ለማጠየቅ ከእውነተኛ አም ላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ እንላለን:: በዚህም ዝቅ የማለት ወይም የመብለጥ ነገር በመካከል አለመኖሩን እንረዳለን::

እውነተኛ አምላክ ማለትም የጸጋ አማልክት ከሚባሉት ቅዱሳን የተለየ መሆኑን ለማስረዳት ነው:: ለምሳሌ:– እግዚአብሔር ሙሴን «በፈርዖን ላይ አምላክ አድርጌሃለሁ» ብሎታል:: ዘጸ.7÷1:: በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ሙሴ «አምላክ» ተብሏል:: ይህንን ጸጋ የተቀበለው ከእግዚአብሔር እንጂ የባሕርዩው አይደለም:: ለዚያውም ራሱን በእግዚአብሔር ፊት በትኅትና ያቀረበ ቅዱስ ሰው! «ጌታ ሆይ እኔ አፌ ኰልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ፣ትናንት ከትናንት ወዲያ ባሪያህንም÷ ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈትብ ሰው አይደለሁም» እንዲል:: ዘጸ.4÷10::

እግዚአብሔር ለሙሴ የጸጋ አምላክነትን ክብር የሰጠው ይሁን እንጂ የሙሴ አምላክነት /ገዥነት/ በፈርዖን ላይ ብቻ ስለሆነ «በፈርዖን ላይ አምላክ አድርጌሃለሁ» ብሎታል:: ዘጸ. 7÷1:: እግዚአብሔር ሙሴን «አምላክ አድርጌሃለሁ» ሲለው በፈጣሪነት ደረጃ ሳይሆን በገዥነቱ ነው:: «መለከ» ማለት ገዛ ማለት ሲሆን አምላክ ማለት ገዢ ማለት ነውና::

በመዝሙረ ዳዊትም «እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር መካከል ቆመ÷ በአማልክትም መካከል ይፈርዳል» ተብሏል:: መዝ.81÷1:: በዚያው የመጽሐፍ ክፍል «እኔ ግን አማልክት ናችሁ÷ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ ነገር ግን እንደሰው ትሞታላችሁ» የሚል ተጽፏል:: መዝ.81÷6–7:: በእነዚህ የመጻሕፍት ክፍሎች ላይ አማልክት የተባሉ እግዚአብሔር በጸጋ ያከበራቸው ቅዱሳን ናቸው:: ለዚህም ነው ቅዱስ ዳዊት «እንደ ሰው ትሞታላችሁ» ያላቸው:: ጌታችንስ ሞቶ የለም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል:: *በእርግጥ ጌታችን ሞተ* ሲባል በገዛ ፈቃዱ እና ሥልጣኑ ቅድስት ነፍሱን ከክብርት ሥጋው ለይቶ እንጂ እንደ ፍጥረታዊ ሰው ተገድዶ የሞተ አይደለም:: ዮሐ.10÷17–18:: ቢሞትም ደግሞ በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጐ የተነሣ በመሆኑ እንደዚህ ባለ ንጽጽር የምናስተያየው እና የምናወዳድረው አይደለም:: ሰይጣንም አምላክ የተባለበት ሁኔታ አለ:: «የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» ተብሎ እንደተነገረ:: 2ቆሮ.4÷4:: የሰይጣን አምላክነት እርሱ የማያስታቸው ሰዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የእርሱ ፈቃድ ፈጻሚዎችና ተገዢዎች በመሆናቸው የተሰጠው ስያሜ ነው:: ከዚህም ባሻገር ጣዖታት በሚያምኑባቸው ሰዎች አምላክ ስለሚባሉ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ በዚያው ስም ይጠራቸዋል:: ዘጸ.32÷1፣ ዘዳ.4÷28:: ይሁን እንጂ አምላክነት የላቸውም::

እግዚአብሔር አምላክ ነው ሲባል ግን ከዚህ ሁሉ የተለየ ነው:: የሚታየውን እና የማይታየውን ፍጥረት እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ፣ የፈጠረ፣ሁሉን በሥልጣኑ መግዛት ማስተዳደር የሚችል ከእርሱ በላይ የሆነ ማንም የለምና:: በዚህም የተነሣ የአማልክት አምላክ /የቅዱሳን አምላክ ማለት ነው ይባላል:: የአማልክት አምላክ የሚለው ሐረግ እውነተኛ አምላክ ከሚለው ጋር እኩል ገላጭ ነው::

ስለሆነም በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ እየተባለ ተጠርቷል:: ለምሳሌ የሚከተሉትን ይመልከቱ::

- «የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ተናገረ» መዝ.49÷1::
- «እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም÷ በፍርድ የማያዳላ÷መማለጃም የማይቀበል ነው::» ዘዳ.10÷17::

ወልድ የባሕርይ አምላክ ነውና የአማልክት አምላክ ከሚለው በተጨማሪ ኃያል አምላክ ይባላል:: ለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ «ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር÷ኃያል አምላክ÷የዘላለም አባት÷የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ያለውን መመል ከት ይቻላል:: ኢሳ.9÷6::

ነቢዩ ኢሳይያስ ጌታችንን «አለቅነት በጫን ቃው ላይ ይሆናል» ያለው ገዢነቱ ወይም አምላክነቱ የራሱ የባሕርይ ገንዘቡ መሆኑን ሲያጠይቅ ነው:: ቀጥሎም «ኃያል አም ላክ» ብሎታል:: ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃያል አምላክ ማን ነው? ከዚህ የምንረዳው ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ የኃያላን ኃያል፣ የጌቶች ጌታ፣ የአማልክት አምላክ መሆኑን ነው::

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ያስረዳናል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «... ከእርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ÷እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው» እንዳለ:: ሮሜ.9÷5::

ቅዱስ ዮሐንስም «...እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን÷እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ዘበአማን /እውነተኛ አምላክ/ መሆኑን በሚገባ ተናግሯል:: 1ዮሐ.5÷20::

## 3. ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ፤ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ

ከላይ ተገኘ ብሎ እዚህ ላይ የተወለደ ያለውን ለማብራራት ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ተወለደ ስንል መቀዳደም የሌለበት ልደት መሆኑን ቀደም ብለን ገልጠናል:: አብ ባለበት ዘመን ሁሉ ወልድ አልተለየም:: ለዚህም ነው ራሱ ወልድ «ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ» ሲል የተና ገረው:: ኢሳ.48÷16:: በዚህ የመጽሐፍ ክፍል «ከሆነበት» የሚለው ኃይለ ቃል የሚያመለክተው ኑባሬውን ነው:: አብ ካለ ወልድም መንፈስ ቅዱስም መኖራቸው የግድ ነውና::

እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ነበረ በዚህ ዘመን አልነበረም የማይባል አምላክ እንደሆነ ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው የአንድነት ሦስትነት ኑባሬ «ከሆነበት» በሚለው ተገልጧል:: ወልድ በኖረበት ዘመን ሲገ ልጽ ነቢዩ «ከሆነበት» ብሏል:: ይህ ኑባሬ ደግሞ መወለድን እንጂ መፈጠርን አያመለክትም::

ቅዱስ ዮሐንስ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ÷ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ያለው ቃል የተባለ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ተዋሕዶ ከአብ ጋር የነበረውን ኑባሬ ያመለክታል:: ዮሐ.1÷1:: ግን በመወለድ እንጂ በመፈጠር አይደለም:: በመፈጠር ቢሆን ኖሮ «በመጀመሪያ» የምትለው ቃል ባላስፈለገች ነበር:: በመጀመሪያ ከተባለ የትኛዋ መጀመሪያ ሊባል ይችላል?

ይህች መጀመሪያ በሰው የጊዜ አቆጣጠር የሚደረስባት ሳትሆን ሁል ጊዜ መጀመሪያ እንደሆነች የምትቀር ናት:: ለእግዚአብሔር ለሕልውናው መጀመሪያ የለውምና:: ሰው እንደማያውቃት እንደማይደርስባት ለማመልከት «መጀመሪያ» በማለት ቅዱስ ዮሐንስ ገልጧታል:: በዚያች መጀመሪያ ሁሉ ወልድ ከአብ ጋር በአንድነቱ በሦስትነቱ ያለ ነውና «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ::»አለ::

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ሲል የተጠቀሰችው መጀመሪያ የተለካች የተወሰነች ናትና ወደኋላ ብንመለስ በእግዚአብሔር ፈቃድ ልንደርስባት እንችላለን:: ዘፍ. 1÷1:: ቃለ አብ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ጋር ያለውን ኑባሬ ለመግለጥ በቅዱስ ዮሐንስ የተነገረችው መጀመሪያ ግን በራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊያውቃት አይችልም:: ይህንን ስንመለከት አብ ከወልድ ቀድሞ የኖረበት ዘመን እንደሌለ እንረዳለን:: አብ ከወልድ ካልቀደመ ደግሞ አልፈጠረውም::

በነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ «ከሆነበት» የተባለችው የጊዜ አመልካች ቃል በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል «በመጀመሪያ» የተባለችው የጊዜ አመልካች ቃል ጋር ፍጹም አንድነት አላት:: ስለዚህ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ከተባለ በአንድነት በሦስትነት ነበረ ማለት እንጂ ተፈጠረ ማለትን በጭራሽ አያመጣም:: ለምን? ቢሉ አብ /አባት/ ካለ ያለ ልጅ አባት ተብሎ ሊጠራ አይችልምና የግድ የልጁን ሕልውና ያሳያልና:: ወልድም /ልጅም/ ካለ በግድ የአባቱን መኖር ያመለክታልና::

አንድ ሰው ልጅ ቢወልድ ልጁ የአባቱን ባሕርይ ይዞ ይወለዳል:: በሥነ ተፈጥሮ አባቱን ይመስለዋል:: አባት ስለ ወለደ ግን ፈጠረ አይባልም:: ከእሱም አካል ከዘሩ ከፍሎ አስገኝቷል እንጂ አል ፈጠረውም:: የወልድም ከአብ መወለድ ምንም እንኳ ከዚህ በጣም ደካማ ከሆነ ነገር ጋር የማይነፃፀር ቢሆን ከአብ ባሕርይ አብን አኽሎ ፣አብን መስሎ መወለዱን እንናገራለን:: በዚህ የመወለድ ግብሩ ደግሞ መቅደም መቀ ዳደም የለበትም::

«እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» ሲል ጌታችን የተናገረው ቃል ወልድ ያለ አብ÷አብም ያለ ወልድ የኖሩበት ዘመን እንዳልነበረ ወደ ፊትም እንደማይኖር ያስረዳል:: ዮሐ. 14÷11:: ነገር ግን ከፀሐይ ክበቡ የሚፈነጠቅ ብርሃን ከክበቧ ሳይለይ ወደ እኛ እንደ ሚመጣ ወልድም ከአባቱ ጋር ካለው ሕልውና ሳይለይ በተለየ አካሉ ወደ እኛ መጥቷልና «ከአብ ወጥቼ /ተወልጄ/ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤» ብሏል:: ዮሐ. 16÷28:: ምንም እንኳን አዳምንና ልጆቹን ለማዳን የፈጠረውን ሥጋ ቢዋሐድም ከአባቱ አንድነት አልተለየምና «አብ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም:: በማለት ተናግሯል:: ዮሐ. 16÷32:: በዚህ ሁኔታ ወልድ ከአብ ጋር ያለውን አንድነት አስረዳን እንጂ ተፈጠረ አልተባለም::

ርዕሰ መናፍቃን አርዮስና መሰሎቹ አብ ወለደው የሚለውን ፈጠረው እያሉ አሳስተው ይተረጉሙ ስለነበረ እንዲህ ማለት የመጨረሻ ክህደት መሆ ኑን ለመግለጥ ሠለሥቱ ምዕት «ዘተ ወልደ ወኢ ዘተገብረ» በማለት በአጭርና በግልጥ ቋንቋ ተናገሩ:: / ለበለጠ ማብራሪያ ሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 4 እና 5ን ይመልከቱ:: */ይቀጥላል/*

## *ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊነትን...*

*ከገጽ 17 የዞረ*

ብቻ አይደሉም:: የአምስቱም አብያተ ክርስቲያናት ይመጣሉ:: በደስታ ይሳተፋሉ:: በጣም ጥሩ ውጤት ነው:: ወደ ፊትም ይቀጥላል:: ምእመናኑም በጣም በመደሰታቸው የሚቀጥለው የጋራ ቅዳሴ የሚከናወንበትን ጊዜ እየጠየቁን ነው::

<u>ሐመር</u>:-*ከቅዳሴውና ወጣቶችን ከመሰብሰቡ ሌላ የምትነጋገሩበት አጀንዳ አላችሁ?*

<u>አቡነ ኤፍሬም</u>: - አለን እንጂ:: ለአንዳንድ ችግሮች መልስ ለመስጠት ስላሉብን የጋራ ኃላፊነቶች፣ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ስላለን ተሣትፎ ወዘተ እንነጋገራለን:: በእውነት በጥሩ መስመር ላይ ነው ያለነው:: ለምሳሌ በቅርቡ አንድ ትልቅ የጸሎት መርሐ ግብር እናዘጋጃለን:: በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ኦርቶዶክሳውያን ዲፕሎማቶች እና ለመሣተፍ ፈቃደኛ ለሆኑ ሁሉ የጸሎት መርሐ ግብር አዘጋጅተናል:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሚሠሯቸው ሥራዎች መሳካት ነው ጸሎት የምናደርገው::

<u>ሐመር</u> : -*ብፁዕ አባታችን*

*/ወደ ገጽ 19 ዞሯል/*

## ደብረ ማርያም...

/ከገጽ 21 የዞረ/

ማይተኽላይ የተባለ ምንጭ አጠገብ በስተምሥራቅ፣ሙራዳ መንፈስ ቅዱስ የተባለ ቦታ፣እንዳ ኪዳነ ምሕረት የተባለ ገደል አካባቢ፣አብርሃ ወአ ጽብሃ ካነፁት መወጣጫ የገደል ደረጃ በስተ ምሥራቅ፣ ከደብረማርያም ቤተ መቅደስ ወደ ምሥራቅ ውስጥ ለውስጥ በአጠቃላይ አራት ያልተገለፁ ሥውር አብያተክርስቲያናት በቆርቆር ደብረ ማርያም አካባቢ እንደ ሚገኙ ያስረዳሉ::

ወደ አቡነ ዳንኤል ቤተክርስቲያን ወይም ቤተጸሎትና ውስጣዊ የሥዕል ይዘት ስንመለስ፤ አቀማመጥዋ እጅግ ከሚ ያስፈራ ገደል ጥግ ነው:: በርዋን ወደ ፀሐይ መውጫ በማድረግ ድፍን ምሥራቅ ትግራይን ገላልጣ የምታሳይ የተፈጥሮ ቴሌስኮፕ ናት:: ስፋቱ ከአንድ ሜትር የማይበልጠውን ገደል እየታከኩ ቤተ ጸሎ ቲቱ ዘንድ ሲደረስ ጠፈረ ቤተክርስቲያኗ በሙሉ በሥዕልና በሐረግ ያሸበረቀ ነው:: የሚከተሉትን ሥዕሎች አቀ ነባበራ የያዘች መዝገበ ሥዕል ናት ለማለት ያስደፍራል::

ቆሮቆር አቡነ ዳንኤል ቤተ ጸሎት

በምሥራቅ

ለዛቲ ቤተ ጸሎት ሐነፀዕክዋ አነ
ዳግማዊ ወእለ ወረስክሙ እም
ድህሬየ ግበሩ ተዝካርየ
ሀበ አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ
ጴጥሮስ ወጳውሎስ
ማርያም ድንግል ምሥለ ፍቁር ወልዳ

<u>በምዕራብ</u>

አብርሃም መስቀል
ይሳቅ መስቀል
ቴዎድሮስ
በናድሌዎስ
እስጢፋኖስ
መልከ ጼዴቅ
ቶማስ

<u>በሰሜን</u>

ሙሴ ጽንሐ
አሮን ጽንሐ
መርቆሬዎስ
ኡልያኖስ
ባስልዮስ
ጎርጎርዮስ

<u>ደቡብ</u>

ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት
ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ
ዳዊት ንጉሥ ምስለ በገና
ጊዮርጊስ
ዮሴፍ
ያዕቆብ፣

የተባሉ ሥዕሎች የሚታዩ ሲሆን በጣራው ላይ ክብ ሠርተው የተሳሉ ሥዕሎችም ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ሩፋኤል፣ማቴዎስ ዮሐንስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ ናቸው::

አንባብያን በዚህ ጽሑፍ ጠቋሚነት ይኸንን አስደናቂ ጥንታዊ ገዳም ከቦታው ድረስ እየሄዱ በማየት የቀደምት ቅዱሳን አባቶቻችንን ታላቅ ሥራ የቤተ ክርስቲያንን ማንነት፣ታሪክና ጥንታዊነት በይበልጥ መረዳት ይችላሉ:: ለገዳሙም ሆነ ለመነኮሳቱ የሚያስፈልገውን በመርዳት የበረከቱ ተካፋይ እንዲሆኑም እናሳስባለን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# መላእክት

*ዲ/ዳንኤል ክብረት*

*ባለፈው «መላእክት» ስለሚለው ቃል ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገን በመመልከት ሥነ ፍጥረታቸውን በመጠኑ ከቃኘን በኋላ ቆይቶ ቅዱሳንና ርኩሳን መላእክት በሚል ለሁለት ስለመከፈላቸው ዐይተናል:: ከዚያም የቅዱሳን መላእክትን አገልግሎት ብዛትና ማዕረግ በማየት በማዕረግ ቅደም ተከተል ኪሩቤልንና ሱራፌልን ዐይተናል:: ዛሬም ካቆምንበት እንቀጥላለን::*

## 3 ሊቃነ መላእክት

ሊቃነ መላእክት ማለት የመላእክት አለቆች ማለት ነው:: ወንጌ ላዊው ዮሐንስ በራእዩ «በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ::» /ራእይ.8÷2/ ያላቸው እነዚህን ሊቃነ መላእክት ነው:: ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትም ሁለቱንም ሦስቱንም ጠቅሰዋል:: ለምሳሌ ሄኖክ «ዑራኤል፣ሩፋኤል፣ራጉኤል፣ሚካኤል፣ሰራቃኤል፣ ገብርኤል»ን ጠቅሷቸዋል /ሄኖክ 6÷1 -7/:: ነቢዩ ዳንኤል ደግሞ ቅዱስ ሚካኤልንና ቅዱስ ገብርኤልን አንሥቷል:: /ዳን.8÷16፣ 10÷13/:: በመጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ደግሞ «የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ» /ቅዱስ ሚካኤል/ በማዕረጉ ተጠቅሷል:: /ኢያሱ.5÷15/:: ቅዱስ ሉቃስም ቅዱስ ገብርኤልን ጠቅሷል /ሉቃ 1÷19/:: ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «በመላእክት አለቃ ድምጽ ከሰማይ ይወርዳል» ሲል ቅዱስ ሚካኤልን አንሥቷል:: 1ተሰ .4÷16::

በይሁዳ መልእክት ላይም «የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል» /ይሁዳ.ቁ 9/ ሲል ቅዱስ ሚካኤልን የጠቀሰ ሲሆን በመጽሐፈ ጦቢት ደግሞ «የቅዱሳንን ጸሎት የሚያሳርጉ፣ወደከበረ ወደገ ነነ ወደ እግዚአብሔር ጌትነትም የሚያገቡ ከከበሩ ከሰባቱ አለቆች አንዱ አለቃ እኔ ሩፋኤል ነኝ» /ጦቢት 12÷ 15/ በማለት ሊቃነ መላእክት ሰባት መሆናቸውንና አንዱም ሩፋኤል መሆኑን ይገልጻል::

በመዝሙረ ዳዊትም «እኔ ግን አማልክት ናችሁ:: ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ:: ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ:: ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ» /መዝ.81÷6-7/ በማለት የዲያብሎስን መውደቅ «ከአለቆች እንደ አንዱ» ብሎታል:: ይህም በመላእክት ዘንድ ሊቃናት መኖራቸውን ያመለክታል::

በራእየ ዮሐንስም «ሚካኤልና መላእክቱ» ሲል ቅዱስ ሚካኤል በአለቅነት የተሾመባቸው መላእክት መኖራቸውን አስረድቷል:: ራእይ.12÷7::

## ቅዱስ ሚካኤል

ሚካኤል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሚ-መኑ፣ካ-ከመ፣ኤል አምላክ፡ መኑ ከመ አምላክ? እንደ እግዚአ ብሔር ያለ ማን ነው? ማለት ነው /ኪ ወ. ክ ገጽ 589/::

ቅዱስ ማካኤል ዲያብሎስ በትዕቢቱ ፈጣሪነትን ሽቶ በዓለመ መላእክት ሁከት ባስነሣ ጊዜ የቅዱሳን መላእክት ፊታውራሪ ሆኖ ዲያብሎስን የተዋጋ ጽኑዕ ኃያል መልአክ ነው:: «በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉት፡ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ:: አልቻላቸውም:: ከዚያም ወዲያ በሰማይ ሥፍራ አልተገኘላቸውም:: » ራእይ 12÷7-8::

ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ነው:: ይሁዳ በመልእክቱ «የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል» በማለት ሊቀ መላእክትነቱን ገልጾአል:: /ይሁዳ ቁ9/ ይህችውም ቅሩብ መንበር ተደርጉ የተፈጠረው ዲያብሎስ የተዋት ክብሩ ናት::

ቅዱስ ሚካኤል ይቅር የሚል ከመዓትም የራቀ ነው:: /ሄኖክ 10÷12/:: ለሰው ባደረገው በጐነት ለሕዝቡ ሁሉ ታዛዥ ነው:: ሄኖክ.6÷5::

ቅዱስ ሚካኤል ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚከራከር መልአክ ነው:: ዲያብሎስ የሙሴን መቃብር ለእሥራኤል አሳይቶ አምልኮተ ባዕድ እንዲፈጽሙ ለማስተማር በተነሣ ጊዜ የተከራከረውና እሥራኤላውያንን የጠበቃቸው እርሱ ነው:: /ይሁዳ.9/ እሥራኤልን ከጠላቶቻቸው መንጋጋ ለማውጣት ይረዳቸው የነበረ ቅዱስ ሚካኤል ነው:: /ዳን. 10÷13፣21/ በመጨረሻው ዘመንም ሕዝበ እግዚአብሔርን ከሐሳዊ መሲህ ጥፋት የሚጠብቃቸው እርሱ ነው:: /ዳን. 12÷1/ :: «ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ» በማለት ነቢዩ ዳንኤል የገለጠው በባቢሎን ምርኮ የተራዳው ቅዱስ ሚካኤል ነው:: /ዳን.10÷3/

እሥራኤልን የመራ /ዘጸ.14÷9/:: የኢያሪኮን ግንብ ያፈርሱ ዘንድ የተራዳ /ኢያሱ.3÷15/ እሥራኤል እግዚአብሔርን በበደሉና በተማረኩ ጊዜ ስለነርሱ ያማለደና ምሕረት ያሰጠ /ዘካ.1÷12/ ኢያሱን የጠበቀ ስለርሱም የተከራከረ /ዘካ.3÷1/ ለእሥራኤል ሕግ ሰጥቶ በሲና አብሮአቸው የነበረ /የሐዋ.7÷38/ ቅዱስ ሚካኤል ነው:: የሶምሶንን መወለድ ለማኑሄ ያበሰረ /መሳ.13÷15/ እሥራኤልን ሊያጠፋ የመጣውን 185.000 የአሦራውያንን ሠራዊት የገደለ /2ኛ ነገሥት 19÷35-37/ ሎጥን ከሰዶም ያወጣ /ዘፍ.19/፣ በአምልኮተ እግዚአብሔር በመቆየቱ ምክንያት ወደ አንበሶች ጉድጓድ ለተጣለው ለነቢዩ ዳንኤል ስንቅ አስይዞ ነብዩ ዕንባቆምን እስከ ባቢሎን ያደረሰው /ተረፈ.ዳን. 13÷35-38/ ሊቀ መላእክተ ቅዱስ ሚካኤል ነው::

በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕለተ ትንሣኤ የመቃብሩን ድን ጋይ ገልብጦ ለመግደላዊት ማርያም የታ የው /ማቴ.28÷2/ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን ከሄሮድስ እሥር ቤት ያወጣው /የሐዋ.12÷7-11/ በልቡ እግዚአብሔርን ይፈልግ ለነበረው ለአሎተኛው ለመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ በዘጠኝ ሰዓት የተገለጠለት /የሐዋ.10÷3/ ቅዱስ ሚካኤል ነው:: /ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት የተወሰደ / Simon I Homelie copte inedited sur s, Michel et le bon Larron" Oriental 3 (1934) p 217-42/

## ቅዱስ ሚካኤል በቤተክርስቲያን

ስለቅዱስ ሚካኤል ክብር፣ጠባቂነትና አማላጅነት ከቀደምት አበው የተማሩትን በኑሮአቸውም ያዩትን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጽፈዋል:: ከነዚህም መካከል ዮሐንስ አፈወርቅ /347-407 ዓ.ም/ ኤዎስጣቴዎስ ዘአንጾኪያ፣ ቅዱስ መቃርዮስ /300-390 ዓ.ም/ ቅዱስ ያሬድ በድጓው /6ኛው መ/ክ/ዘመን/ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በሰዓታቱ /1357- 1417 ዓ.ም./ በሰፊው ጽፈዋል::

ንግሥት ክሌዎፓትራ «ሳተርን» ለሚባለው ጣዖት ያሠራቸው ቤት በእስክንድርያ ነበር:: ይህ ቤተ ጣዖት እስከ እስክንድርያው ፓትርያርክ እለእ ስክንድሮስ /312-326/ ዘመን ድረስ ነበር:: እለእስክንደሮስ ሊያጠፋው ሲነሣ በሕዝቡ ልቡና ገና አምልኮ ጣዖት ስላ ልጠፋላቸው 18 ፓትርያርኮች ያልነኩትን አንተ ለምን ታፈርስብናለህ ብለው ተቃወሙት:: እለእስክንድሮስም ሕዝቡን መክሮና አስተምሮ የሳተርን በዓል ይው ልበት በነበረው ዕለት የቅዱስ ሚካኤል በዓልን እንዲያከብሩ ዐውጆ ቤተ ጣዖቱንም በቅዱስ ሚካኤል ስም ሰይሞ ቤተክርስቲያን አደረገው:: /ስንክሳር ኅዳር 12/ ከዚያ በኋላ በቅዱስ ሚካኤል ስም አያሌ አብያተ ክርስቲያናት መታነጽ ጀመሩ:: /cocitic engclopedia, vi S.P 1617/

በተለይም ኬልቄዶናውያን በትራቸውን በኦርቶዶክሳውያን ላይ በሰነዘሩበት በ4ኛው መ/ክ/ዘ በስማዕትነት ያለ ፈችው ግብጻዊቷ አፎምያና ባሏ በየወሩ አሥራ ሁለተኛ ቀን የቅዱስ ሚካኤልን ፣በ21 የእመቤታችንን በ29 ደግሞ በዓለ እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበር:: ባሏ በሞተ ጊዜ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በየወሩ ትዘክር ዘንድ አደራ ብሏት ነበር:: ለዚህም የሊቀ መላእክቱን ሥዕል ሰጥቷት ነበር::

ሰይጣን በመነኩሴ ተመስሎ በተደጋጋሚ በመምጣት ከሁን በኋላ እንዲህ ያለውን በቅዱስ ሚካኤል ስም የምታ ደርገውን በዓል እንድትተው ይነግራት ጀመር:: በተለይም በ12 ቀን እኔ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ ብሎ መጣ:: ነገር ግን በትረ መስቀል ባለያመዙ አፎምያ ተጠራጠረችው:: «አንተ ቅዱስ ሚካኤል ከሆንክ የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል አለኝ እርሱን ላምጣና ተሳለመው» አለችው:: በዚህ ጊዜ እንዳ ወቀችበት ስለገባው ዘሎ ያዛት:: ተራዳኢ

ው ቅዱስ ሚካኤል ፈጥኖ በመድረስ ዲያብሎስን ድል አደረገላት፡፡

ከዚህ በኋላ የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሰፊው መከበር ጀመረ፡፡ /የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስንክሳር /ኅዳር 12/ የግብጽ ቤተክርስቲያን ስንክሳር /ኅዳር 12/፡፡

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥነ ሥዕል ሰፊ ቦታ ካላቸው መካከል የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል አንዱ ነው፡፡ በመቅደስ የፊት ለፊት ግድግዳ ላይና በመቅደስ በር ላይ በብዛት ተሥሎ ይገኛል፡፡ በመቅደስ ግድግዳ ላይ የሚሳሉት ሥዕሎች ቅዱስ ሚካኤልን በመንበሩ የሚያሳዩ ሲሆን በመቅደስ በር ላይ ደግሞ ልብሰ ተክህኖ ለብሶና ሰይፍ ይዞ እንደቆመ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከእመቤታችን በስተቀኝ /ቅዱስ ገብርኤል በግራ/ ተስሎም እናገኘዋለን፡፡ በአንዳንድ ምእመናን ቤት የሚገኘው «የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል» ግን ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ያልጠበቀ ቅዱስ ሚካኤልን እንደወታደር የጦር ጥሩር አልብሶ፣ዲያብሎስን ደግሞ በአፍሪካዊ ሰው አምሳል የሚያስቀምጥ የተሳሳተ ሥዕል ነው፡፡

በቅዱሳን ገድል ውስጥም የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት በልዩ ልዩ ቦታ ተገልጧል፡፡ በቀዳሜ መነኰሳት አባ እንጦንስ ታሪክ ውስጥ ቅዱስ ሚካኤል ሥርዓተ ምንኩስናን እንዳስተማረውና ከዲያብሎስ ፈተና ይጠብቀው እንደነበር ተገልጧል፡፡ በገድለ አቡነ ተክለሃይማኖትም የአቡነ ተክለሃይማኖት ጠባቂ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ሞተሎሚን ድል ነሥቶ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እናት እግዚእኀርያን ከዳሞት ወደ ኢቲሳ እንደመለሳት ተጽፏል፡፡ በገድለ ክርስቶስ ሠምራም የክርስቶስ ሠምራ ጠባቂ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል እንደነበረና በተጋድሎዋ ሁሉ ይራዳት እንደነበር በሰፊው ተዘርዝሯል፡፡

## ቅዱስ ገብርኤል

ገብርኤል ማለት በዕብራይስጥ «ኃይል የእግዚአብሔር ነው» ማለት ነው፡፡ /Holman Bible Dictionary/

መጽሐፈ ሄኖክ «በእባቦች ላይ በገነትም ባሉ ጻድቃን ላይ በኪሩቤልም ላይ የተሾመ ከከበሩ መላእክት አንዱ ገብርኤል ነው» ይለዋል፡፡ ሄኖክ.6÷7፡፡ በሌላም በኩል በዚህ ዓለም የሚኖሩ በመላእክት ጌታ ስምም አምነው ስለሚለምኑ ሰዎች የሚማልድ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ሄኖክ.10÷7፡፡

ለነቢዩ ዳንኤል ያጽናናውና ራእዩን ይተረጉምለት የነበረው ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡ «አስቀድሞ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ፡፡ በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ፡፡ አስተማረኝም፡፡ ተናገረኝም፡፡» ዳን.9÷22፣ ዳን.8÷15፡፡

ቅዱስ ገብርኤል አብሣሪ መልአክ ነው፡፡ ለዘካርያስ የመጥምቀ መለኰት ቅዱስ ዮሐንስን መወለድ ለእመቤታችን የመድኃኔዓለምን መወለድ ያበሠረ እርሱ ነው፡፡ /ሉቃ.1÷8–19፣26–56/ ቅዱስ ገብርኤል «በልዑል እግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ» እንዳለ፡፡ /ሉቃ. 1÷19/፡፡

ከቅዱስ ሚካኤል ጋር ሰዶምን ያጠፋ /ዘፍ.18÷2/፣እመቤታችንን ይዞ ወደ ግብጽ የሸሸ፣ሄሮድስ ከሞተም በኋላ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ለዮሴፍ የተናገረ፣ በጉዞአቸውም ጠባቂ የነበረ፣ ይህ ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡ /ማቴ. 2÷13፣19/

ለጣዖት አንሰግድም በማለታቸው በናቡከደነፆር ትዕዛዝ ወደ እሳት የተጣሉትን ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያወጣቸውን ነቢዩ ዳንኤል «ሰው» በማለት እንደገለጸው ሁሉ ናቡከደነፆርም «የአማልክት ልጅ» በማለት የተናገረለት ይህ ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡ ዳን. 3÷24–27፡፡

ዲያብሎስ በመላእክት ዘንድ ሁከት ባስነሣ ጊዜ «አምላካችንን እስክናውቅ ድረስ ጸንታችሁ ቁሙ» በማለት መላእክትን ያረጋጋ፣ነቢዩ ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ በተጣለ ጊዜ /ዳን.6÷23/፡፡ ፈጥኖ በመድረስ የአናብስቱን አፍ የዘጋ ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡

## ቅዱስ ገብርኤል በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

ቅዱስ ገብርኤል በቀደምት ቅዱሳን ድርሳናትና ገድላት ውስጥም ታላቅ ቦታ አለው፡፡ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በድርሳናቸው በሰፊው ጽፈውታል፡፡ /Grat, 1944-1953, Vol.1 p 544/፡፡ ሐዋርያው ስምዖን በሰማዕትነት ባለፈ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ተገልጾ ያበረታው ነበር፡፡ /Zoega, G catalogues codicn copticorum manuscript to rumqui in muxo boraiano veliteris adservantur. Rome 1810 pp.137/ ቅዱስ ቂርቆስና ቅድስት ኢየሉጣ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን በፈላ ውኃ ውስጥ ሲጣሉ ያዳናቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስም በመጻሕፍታቸው እንደ ቅዱስ ሚካኤል ሁሉ በሰፊው ጽፈውለታል፡፡ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ግእዝ የተተረጐመው ድርሳነ ገብርኤል የመልአኩን ገቢረ ተአምራት በዝርዝር የሚገልጥ መጽሐፍ ነው፡፡

በቤተክርስቲያናችን ታኅሳስ 19 /ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያዳነበት /እና ሐምሌ 19 /ቅዱስ ቂርቆስንና ቅድስት ኢየሉጣን ከፈላ ውኃ ያሞነበት ዕለታት በዋናነት የሚከበሩ የቅዱስ ገብርኤል በዓላት ናቸው፡፡

ቅዱስ ገብርኤል በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥነ ሥዕል ጉልህ ሥፍራ ከያዙት ሊቃነ መላእክት ከቅዱስ ሚካኤል ቀጥሎ የሚገኝ ነው፡፡ በተለይም እመቤታችንን ሲያበሥራት፣ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ሲያወጣ፣ቂርቆስና ኢየሉጣን ከፈላ ውኃ ሲያድን የሚያሳዩት ሥዕሎች በአብያተ ክርስቲያናት የመቅደስ ግድግዳዎችና በምእመናን ቤት በብዛት የሚገኙ ናቸው፡፡ በቤተ መቅደስ በር ላይ ደግሞ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ሰይፍ ታጥቆ በትረ መስቀል ይዞ ከቅዱስ ሚካኤል ጋር ይሳላል፡፡

## ቅዱስ ሩፋኤል

ሩፋኤል /ዕብ.ሩፋኤል/ ፈውስ አምላክ፣ፈዋሴ አምላክ፣ዘሥዩም ዲበ ፈውስ /በፈውስ ላይ የተሾመ/ ማለት ነው፡፡ /ኪ.ወ.ክ.836፣ /The Eerdmans Bible Dictionary/ መጽሐፈ ሄኖክም «በሰው ቁስል የተሾመ ከከበሩ ከመላእክት አንዱ ሩፋኤል ነው» ይላል፡፡ ሄኖክ 6÷3፡፡ እንዲሁም ሰዳዴ አጋንንት መሆኑንም ያስረዳል፡፡ ሄኖክ10÷8፡፡ ጎርጎርዮስ ዘዐቢይ «በዓለ መድኃኒት ዘእግዚአብሔር» ብሎታል፡፡ ፈታሔ ማኅጸንም ይባላል፡፡ እናቶች ሲወልዱ መከራ እንዳይበዛባቸው የሚራዳ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቅዱስ ሩፋኤል አማላጅነት ተራዳኢነት በሰፊው ተዘርዝሮ የምናገኘው በመጽሐፈ ጦቢት ነው፡፡ ከጌታችን ልደት በፊት 3ኛው መ/ክ/ዘ በተጻፈው በዚህ መጽሐፍ ላይ ጦቢት የተባለው በፋርስ የተማረከ ጽኑ እሥራኤላዊ ዕለተ ሞቱ በደረሰ ጊዜ በሜዶን ሀገር ገባኤል በተባለ ሰው እጅ ያስቀመጠውን ገንዘብ ለማምጣት ወደደ፡፡ ይህንንም ለልጁ ለጦብያ ነገረ ውና ሊልከው አሰበ፡፡ ጦብያም ሀገሩን አላውቀውም ስላለው አብሮህ የሚሄድ ሰው ፈልግ እኔም የድካሙን ዋጋ እከ ፍለዋለሁ አለው፡፡

መልአኩ ሩፋኤልም ሰው ተመስሎ ለጦብያ ተገለጠለትና አብሮት ወደ ሜዶን ለመጓዝ ፈቃደኝነቱን ነገረው፡፡ ጦቢትም ሀገሩንና ወገኑን ቢጠይቀው የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ አዛርያ ነኝ አለው፡፡ አዛርያ ማለት «እግዚአብሔር ተራዳኢ ነው» ማለት ነው፡፡ ጦቢትም ከአዛርያ ጋር ዋጋ ተነጋግረው ስንቅ አስያዛቸውና ጦብያንና አዛርያን ላካ ቸው፡፡

አዛርያ በመንገድ ጦብያን ይራዳው ነበር፡፡ ጦቢያም በሄደበት ሀገር መልካም ሚስት እንዲያገኝ አደረገው፡፡ ገንዘቡን ይዘው ሲመለሱም ለአባቱ ከዓሣ ሆድ የወጣ መድኃኒት /ጦቢት ታውሮ ስለነበር/ ለጦቢያ ሰጠው፡ ጦቢትም በዚያ መድኃኒት ታሽቶ ዓይኑ በራለት፡፡

ጦቢያ ለአዛርያ ዋጋውን ካመጣው ገንዘብ ግማሹን እንዲወስድ ነገረው፡፡ አዛርያም ጦቢያና ጦቢትን ጠርቶ ሰማያዊ ምሥጢር ገልጦ አስተማራቸው፡፡ መከራቸው፡፡ መልአኩ ሩፋኤል መሆኑንም ገለጠላቸውና ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ /መጽሐፈ.ጦቢት ከምዕ. 1–12/

## ቅዱስ ሩፋኤል በቤተክርስቲያን

ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መካከል ስለ ቅዱስ ሩፋኤል በሰፊው በመጻፍ የታወቀው ዮሐንስ አፈወርቅ ነው ፡፡ /Budge,1915 pp.526-533/ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በዚህ ድርሳኑ «መራሔ ፍኖት» ብሎታል፡፡ ጦቢያን በቀና መንገድ መርቶታልና፡፡ «መልአከ

ከብካብ» ብሎታል:: ጠቢያና ሣራን ያጋባ ጋብቻቸውንም የባረከ በመሆኑ::

በዚህ ድርሳን ሩፋኤል የዮሐንስ አፈወርቅ ጠባቂ መልአክ እንደነበር ተገልጧል:: «ለአንዲት ሰዓት፣ለግማሽ ሰዓት ለዓይን ጥቅሻም ቢሆን አይለየውም ነበር» ይላል:: ዮሐንስ አፈወርቅን ወደ ንጉሥ አርቃድዮስ የላከውም ሩፋኤል ነው:: ንጉሥ አርቃድ ዮስም በቅዱስ ሩፋኤል ስም /ምናልባት የመጀመሪያውን/ ቤተክርስቲያን ሠርቶለታል::

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ዘእስክንድርያ /385–412 ዓ.ም./በጻፉት /In Raphaelem Archangelum/ ድርሳን ውስጥ የሚከተለው ታሪክ ተገልጧል::

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ከንጉሥ ቴዎዶስዮስ ጋር የቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያ ከተማ እንዲታነጽ ጠየቁ:: በመጨረሻም በሜዲትራንያን ባሕር በምትገኘው ጳጥሬስ /Patres/ በተባለችው ደሴት በቅዱስ ሩፋኤል ስም ቤተክርስቲያን ታነፀ:: ይህ ቤተ ክርስቲያን የታነፀው ደሴት መስሎ በተኛ ዓሣ አንበሪ ላይ በመሆኑ ሕዝበ ክርስቲያኑ ለክብረ በዓል በሄደበት ጊዜ አንበሪው ተነቃንቆ ቤተክርስቲያንዋም ልትፈርስ ደረሰች:: ሕዝቡም ወደ መልአኩ ሩፋኤል ጮኹ:: በዚህ ጊዜ ሊቀ መልአኩ ደርሶ አንበሪውን በጦር ወግቶ ጸንቶ እንዲተኛ አደረገው:: (Orlando, T. " Un enco mio, cop to di Rafaela Archangelo" Rivista degli Studi orientali 47 /1972/ pp /412–414, coptic encylclpedia p 2054/

ቅዱስ ቄርሎስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ያሠሩትን የቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ጳጉሜን 3ቀን ቅዳሴ ቤቱን አክብሮአል::

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስለ ቅዱስ ሩፋኤል የተጻፈና በሰፊው የሚታወቀው መጽሐፍ ድርሳነ ሩፋኤል ነው:: ዓመታዊ በዓሉ ጳጉሜን 3 ቀን ይከበራል:: በዚህ ዕለትም የሚጸለዩትን ጸሎቶች ሁሉ እንዲያሣርግ፣በእግዚአብሔር ፊትም እንደ ሠርክ መሥዋዕት እንደሚቀርብለት ቃል ኪዳን ተሰጥቶታል:: በዚህ የተነሣ አበው ጳጉሜን 3 ቀን በጸሎት ተግተው ይውላሉ::

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በብዛት የምናገኛቸው የቅዱስ ሩፋኤል ሥዕሎች ሁለት ዓይነት ናቸው:: የመጀመሪያው ዓሣ አንበሪውን በጦር ወግቶ እንደያዘ ሁለተኛው ደግሞ ከጦቢት ጋር በመንገድ ላይ ሲጓዝ የሚያሳየው ነው::

### ቅዱስ ሱርያል /ዑራኤል

ሱርያል የሚለው ስም በአንዳንድ ድርሳናት ካልሆነ እምብዛም አይታወቅም:: ትርጉሙ «ዐለቴ እግዚአብሔር ነው» ማለት ነው:: /Coptic encyclopedia Vol. 7 p.2160/ የዑራኤል ሌላ ስሙ ነው:: ዑራኤል ማለት «እግዚአብሔር ብርሃን ነው» ማለት ነው /Holman Bible Dictionary p.1385/ በቤተ ክርስቲያናችን በስፋት የሚታወቀው ዑራኤል የሚለው ስም ነው:: /ድርሳነ ዑራኤል፣ 1991፣ገጽ 14/

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ቅዱስ ዑራኤል በስፋት የምናገኘው በመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ነው:: ዕዝራን ይራዳው የነበረ:: ለዕዝራም መጻሕፍትን እንደገና እንዲጽፋቸው ጽዋዐ ልቡና አጠጥቶ ምሥጢር የገለጠ ቅዱስ ሩፋኤል ነው:: /ዕዝራ.ሱቱ.2/ መጽሐፈ ሄኖክ «በመብረቅና ነጐድጓድ ላይ የተሾመ» ሄኖክ 6÷–2/ ይለዋል:: ምሥጢረ ሰማይን ለሄኖክ ያሳየው ዕውቀትም የገለጠለት እርሱ መሆኑን ጽፏል:: /ሄኖክ. 28÷13–14/::

### ቅዱስ ዑራኤል በቤተ ክርስቲያን

እመቤታችን በኪደተ እግርዋ በኢትዮጵያን በዞረች ጊዜ ቅዱስ ዑራኤል ያገለ ግላት እንደነበር በድርሳነ ዑራኤል ላይ ተጽፏል:: በመጽሐፈ ስንክሳርም ለአዳም የድኅነትን ዜና የነገረው፣ዮሴፍን ብርታት ሰጥቶ ከብእሲተ ጲጥፋራ ያዳነው፣ለዕዝራ ምሥጢር የገለጠለት፣ የሚያረጋጋ ለኃጢአተኞችም አማላጅ ነው» ይላል:: /ስንክሳር ጥር ቀን 27/::

በቅዱሳን ገድልም ውስጥ የቅዱስ ዑራኤልን ተራዳኢነትን እናነባለን:: በስንክሳር /የካቲት 9/ ጳውሎስ የተባለ የእ ስሙናይ ሰው በአረማዊ ንጉሥ ለሰማዕትነት በተወሰደ ጊዜ ያበረታው እንደ ነበር ተጽፏል:: በአባ–ጊዮርጊስ ታሪክም ውስጥ የቅዱስ ዑራኤልን ተራዳኢነት እናያለን::

በዛሬው ደቡብ ውሎ ቦረና /በጥንቱ ለኩ መልዛ/ ሸግላ በተባለች ቀበሌ ሕዝበ ጽዮን እና እምነ ጽዮን የተባሉ ባልና ሚስት ይኖሩ ነበር:: በ12ኛው መ/ክ/ዘ/ እነዚህ ደጋግ ባልና ሚስት ልጅ ባለማግኘታቸው እያዘኑ እግዚአብሔርን ይለምኑት ነበር:: ልዑል እግዚአብሔርም ልመናቸውን ሰምቶ በ1357 ዓ.ም. መልአኩ ዑራኤልን ልኮ ወንድ ልጅ እንደሚወለድና ስሙንም ጊዮርጊስ ብለው እን ዲጠሩት ነገራቸው::

እነዚህ ደጋግ ባልና ሚስት ልጃ ቸው ሰባት ዓመት ሲሞላው ወደ ሐይቅ ገዳም ሠረቀ ብርሃን ከሚባሉ መምህር ዘንድ እንዲማር ላኩት:: ነገር ግን ለሰባት ዓመታት በገዳሙ ቢቆይም የፊደል ዘር እንኳን መለየት ባለመቻሉ መምህሩ ወደ ቤቱ መለሱት:: ሕዝበ ጽዮን ግን ለእግዚአብሔር ብፅዐት ሰጥቼዋለሁ ብለው ወደ መምህሩ መልሰው አመጡት::

ጊዮርጊስ ለገዳሙ መነኩሳት እህል እየፈጨ፣ውኃ እየቀዳ፣ እመቤታችንን እየተማፀነ ሲኖር አንድ ቀን ከሥዕሏ ሥር እየሰገደ ሳለ መልአኩ ዑራኤል ተገልጦ ጽዋዐ ልቡና አጠጣው:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ተገልጦለት ከ40 በላይ መጻሕፍት ደርሷል:: /*መጽሐፈ አርጋኖን /1939/ መግቢያ*

በቤተክርስቲያን ሥነ ሥዕል ቅዱስ ዑራኤልን ለእዝራና ለአባ ጊዮርጊስ ጽዋዐ ልቡና ሲያጠጣና እመቤታችንን በስደቷ ጊዜ ሲራዳት ተስሎ ይገኛል::

በስንክሳሩ መሠረት ዓመታዊ ክብረ በዓሉ ጥር 27 ነው:: ትንሣኤ ዘጉ ባኤ ማ/ቤት ባሳተመው የየዓመቱ የቀን መቁጠሪያ የበዓላት ዝርዝር ውስጥም የቅዱስ ዑራኤል በዓል ጥር 27 መሆኑን ነው የሚገልጸው፣ ግጻዌውም እንዲሁ:: በአሁኑ ጊዜ ዓመታዊ በዓሉ ሲከበር የሚታየው ግን ጥር 22 /በድርሳኑ/ ነው:: ይኼን ጉዳይ ሊቃውንቱ አንድ ሊሉት ይገባል::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## ሩት

*[ከገጽ 8 የዞረ]*

ኑኃሚን በሞዓብ ያላገኘችውን በቤተልሔም አገኘችው፣ከሥጋ ፍሬዋ ያላገኘችውን ከመንፈስ ፍሬዋ አገኘችው:: ለኛም እንዲሁ ነው:: ሩት ግን አተረፈች:: ትታው ከመጣችው በላይ አተረፈች:: ለእግዚአብሐር ሲሉ ማጣት እጥፍ ድርብ ያስገኛልና::

«ስለስሜ ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል::» ማቴ.19÷29::

ኢዮብ ስለ እውነት ተፈትኖ ሁሉን አጣ:: ነገር ግን በኋላ የተቀበለው በፊት ከነበረው ይበልጣል:: ካጣው ይልቅ አጥቶ ያገኘውን መዘነ:: «እግዚአብሔርም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን ለኢዮብ ባረከ::» ኢዮብ. 42÷12::

«ቤኤዝም ሩትን ወሰደ:: ሚስትም ሆነችው ደረሰባትም እግዚአብሔርም ፅንስ ሰጣት::» ሩት 4÷13:: በእሥራኤል ልማድ «አብርሃም ይስሐቅን ወለደ» ነው የሚባለው:: አሁን ግን «እግዚአብሔርም ፅንስን ሰጣት» ተባለ፡ የሥጋ ፍሬ አይደለም:: ሰው በመሆንዋ ብቻ ያገኘችው አይደለም:: የሩት የትጋትዋ፣የጽናትዋ፣የእምነቷ፣የፍቅርና የመታዘዝዋ ፍሬ በመሆኑ እግዚአብሔር ፅንስ ሰጣት ተባለ:: ቦኤዝ ኢዮቤድን ወለደ ከመባሉ በፊት እግዚአብሔር ፅንስን ሰጣት ተባለ::

የኑኃሚን ሐዘን ወደደስታ ተለወጠ:: እግዚአብሔር በሩት በኩል በሰጣት ፍሬ:: ኦሪት ፍሬ ለማፍራት ደክማ ነበር:: እሥራኤል ፍሬ ለማፍራት አልቻለችም ነበር:: እግዚአብሔር ከበለስ እሥራኤል ያጣውን ፍሬ ከአሕዛብ አገኘ:: «ኑኃሚን ሕፃኑን አቀፈችው ሞግዚትም ሆነችው» ሩት 4÷16:: ኦሪት ባትኖር ኖሮ ክርስትና ሞግዚት ባላገኘም ነበር:: ለሥርዓት፣ለሕግ ለትምህርት ለአምልኰት መሠረቱ ብሉይ ኪዳን ነውና ሐዋርያት ወንጌ ልን በብሉይ ሞግዚትነት ነው ያሳደ ጉት:: ቤተ ክርስቲያንን በቤተ ምኩራብ ሞግዚትነት ነው ያሳደጉዋት:: ከብሉይ ጠቅሰው ነው በሐዲስ የተረጐሙት የብሉይን መሠረት አድርገው ነው የሐዲሱን ቤት የሠሩት::

በእምነት ፣በተስፋ፣በፍቅር ፣በመታዘዝ፣በመጽናት፣በትዕግሥት የተገኘው የሩት ፍሬ «ከሰባት ወንዶች ልጆች ይልቅ ለአንቺ ከምትሻል ከምትወድሽ ምራትሽ ተወልደሻልና ሰውነትሽን ያሳድሰዋል:: በእርጅናሽም ይመግብሻል» ነበር ጐረቤቶቿ ያሏት:: ሩት 4÷4–14::

/ወደ ገጽ 23 ዞሯል/

# ምሥራፍ

## «እንቅቅልህ»

### ባሰፍርንዱስ ቃል

ፍርንዱስ ማለት ቅልቅል ማለት ነው። ፍጹም ግእዝ ፍጹም አማርኛ ሳይሆን ከሁለቱ ቋንቋዎች ፊደላት ተጋጥመው አንድ ቃል ሲሰጡ «ፍርንዱስ ቃል» ይባላል። «እንቆቅ» ከግእዙ «ልህ» ከአማርኛ ተወስዶ ቃሉ በፍፀጹም ግእዝ ተነግሮ ቢሆን «እንቆቅሆ ለከ» ይባል ነበር። በፍጹም አማርኛም ቢነገር «እንቁላል አለህ /ለአንተ/» የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር። ምሥጢሩም እንቁላል ብስ የሌለው ድፍን ነገር እንደሆነ፣ እንዲሁም የአበው ተረትና ምሳሌ ስውር ነገር ስለሆነ በእንቁላል መልክ ተነግሯል።

/ምንጭ፣ ሀገረ መጻሕፍት ክፍል 1 ፣ ከአለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፣ ገጽ 27/

*በዚህ አጋጣሚ*
*«እንቆቅልህም» እንበ ልዎ:*
*ሲወጡ በንብረት ለእብደት፣*
*ሲወርዱ በውርደት ለቅጣት፣*

መልሱ፦ የሰናዖር ሰዎች ሐሳብና የባቢሎን ግንብ መፍረስ የቋንቋቸው መደባለቅ ዘፍ.11፥1–9/

ገብረ አዶናይ
/አ.አ/

## አንተስ ኢየሱስ ክርስቶስን ማን ትለዋለህ?

- *አምላኬ ትለዋለህ፣ ግን ፈቃዱን ለማድረግ ራስህን ሰጥተሃል?*
- *ጌታዬ ትለዋለህ፣ ግን በሕይወትህ ሁሉ ትገዛለታለህ ?*
- *ንጉሤ ትለዋለህ፣ ግን ለቅዱስ ቃሉ ትታዘዛለህ?*
- *አባቴ ትለዋለህ፣ ግን እንደ ልጅ ትቀርበዋለህን?*
- *እረኛዬ ትለዋለህ፣ ግን ከበጎቹ ጋር በበረት አለኸን?*
- *መመኪያዬ ትለዋለህ፣ ግን በመከራ ጊዜ በእርሱ ተማምነሃል?*
- *መድኃኒቴ ትለዋለህ፣ ግን በፍጹም ንስሐ ነጽተህ ወደ ሥጋ ወደሙ ቀርበሃል?*

*ምንጭ፦ ስይፈ ሚሉስ መጽሔት፣ 1ኛ ዓመት ቁ 1/*

## ወደ ሙት ባሕር እንዳንገባ...

*. . .*

*ይህን በዓል ለማክበር የተሰበሰባችሁ ምእመናን ጥምቀት ለክርስቲያኖች የሕይወት በዓል ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ሰውን ለመፈ ለግ ሰውን ለማዳን የመጣ እንደ መሆኑ የወደቅንባትን ቦታ ሁሉ አስሶታል። አሁን ዛሬ የምናየው የምናከብረው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በውኃ ውስጥ ሲፈልገው ነው። ፈልጎም አላጣው አግኝቶታል። ተዘግቶ የነበረው ሰማይ ተከፈተ። የአምላኩን ገጽታ አጥቶ ጣዖታትን ያመልክ የነበረው የሰው ልጅ የአምላኩን ፊት አየ። አምላኩን አወቀ። በጥፋቱ ያጣትን ገነት እንደገና ተከፍታ አያት፣ አገሩ መሆኗን አወቀ ወደ እሷም ገባ።*

*...ምእመናን የጥምቀት ልጆች እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ፤ እኛ እንግዲህ በክርስቶስ ጥምቀት የተጠራን ኹሉ በዚህ ጥምቀት የተከፈተልንን የእግዚአብሔር ቤት መልሰን እንዳናዘጋው። ወደ ምድረ ርስት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከገባን በኋላ እንደገና ወደኋላ እንዳንመለስ፣ ዮርዳኖስ የሕይወት ውኃ ነው፤ የሕይወት ወንዝ ነው፤ የበረከት በር ነው። ይህንን ርስተንና ዘንግተን ወደሙት ባሕር እንዳንገባ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ብዙ ሰዎች ዛሬ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት ወደ እግዚአ ብሔር መንግሥት ከገቡ በኋላ እን ደገና ወደሙት ባሕር እየዘለሉ እየ ገቡ ነው። ታዲያ በሙት ባሕር ሕይወት ስለሌለ እዚያው ቀልጠው ይቀራሉ። ይህም ያሳዝናል የዘለዓለም ሞት ነውና። እዚህ ላላችሁት አደራ የምን ለው ሕይወታችሁ እንዳይጋለጥ ነው። ተመለ ሱ፥በንስሐ ወደ ምድረ ርስት መሻገሪያ ወደፈለገ ንስሐ ተመልከቱ የመድኃኒታችንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀበሉ። ለዘለዓለም ሕይወት ይሆንላችኋል።*

*ምንጭ፦ አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ አገረ ስብከት ሊቀጳጳስ በጽሑፍ ካዘጋጁት ስብከት የተወሰደ።*

## ቅኔ

ላልይበላ ቅዱስ እንደምን ከበረ፣
ጊዜ ኃያል ኬላን በመስቀል ሰበረ፣
ቀርያና አስጊጦ የወርቅ መንበሩን፣
በመቅደስ አኖራት ሊገልጥባት ክብሩን፣

*ከብሥራተ ገብርኤል -*

## ጾም

ቁስለ ነፍስን
የምታደርቅ
ፈቃደ ሥጋን
የምታርቅ
የፈጣሪን
ደጅ መጥኛ
የፈቃዱ መገለጫ
መታመኛ
የሥጋን ፈረስ
መለጕሚያ
የጠላትን ጦር
መቃወሚያ
የንስሐ እኅቷ
የጸሎት እናቷ
የይቅርታ መንገድ
አቀራረተ መሸት
ከብሪ ትመጣለች
የንጉሥ አዋጅ
ቀድሷታልና
አንዱ የአብ ልጅ።

*2ኛ ዜና 13ቁ21።*

*ከሱናማዊት*

## በደሙ አተመኝ

ለሌባ ዋስ የለው
ለቀማኛ ዘመድ
ከጓደኛዬ ጋር
ተቀበልን የሞት ፍርድ
ተገልጾ ሲታየኝ
በደሉና ጽድቀ
የጸጸትን እንባ
ዓይኖቼ አፈለቁ
ለካስ ከሞት ሀገር
ሕይወትም ይገኛል
የዕድሜ ልክን ኃጢአት
ንስሐ ያጠራል
ዕንባዬን አብሶ
የተስፋ ቃል ሰጠኝ
ዳግም እንዳልጠፋ
በደሙ አተመኝ
ቁልፉን ተረክቤ
ከሕይወት ባለቤት
አዳምን ቀድሜ
ገባሁ ወደ ገነት

ከሙሉነሽ/

# «ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊነትን ላላየውና ላልቀመሰው የኦርቶዶክሳዊነት ብርሃን ላልበራለት ለቀሪው የአፍሪካ ክፍል የማድረስ ኃላፊነት አለባት»



*ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም ካሪም በ1957 ዓ.ም. ካሽሊ ሦሪያ ተወለዱ:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደፈጸሙ በ1969 ዓ.ም. ሊባኖስ ወደሚገኘው ወደ ቅዱስ ኤፍሬም መንፈሳዊ ት/ቤት ገቡ:: በ1974 ዓ.ም. ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁም በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆይተው ከፍ ላለ ትምህርት ወደ ግብፅ አመሩ:: በዚያም የሥነ መለኮት ትምህርታቸውን በመከታተል በ1980 ዓ.ም በሥነ መለኮት የባችለር ዲግሪ አግኝተዋል::*

*በ1977 ዓ.ም. ወደ ምንኩስናው ዓለም የገቡት ብፁዕነታቸው በ1980 ዓ.ም. ቅስናን ከተቀበሉ በኋላ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጸሐፊ እንዲሁም በደማስቆ የቅዱስ ኤፍሬም መንፈሳዊ ት/ቤት መምህር በመሆን ሠርተዋል:: ለትምህርት ባላቸው ከፍተኛ ፍቅርም በ1981 ዓ.ም ለሌላ ጥናት ከአየርላንድ ቅዱስ ፓትሪክ ኮሌጅ በመግባት በ1983 ዓ.ም. የነገረ መለኮት ፈቃድ /Licentiate Of Sacred Theology/ እንዲሁም በ1986 ዓ.ም. በሥነ መለኮት የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል::*

*ራሳቸውን በተለያየ መስክ ለትልቅ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ሲያ ዘጋጁ የቆዩት ብፁዕነታቸው በጥር ወር 1988 ዓ.ም በሦርያው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግናጥዮስ ዘካ ኢወዝ እጅ ማዕረገ ኤጲስ ቆጶስነትን ተቀብለው የምሥራቅ አሜሪካ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ:: ከተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪነታቸው ባሻገር ጌታችን ያስተማረበት የሦሪያ አራማይክ ቋንቋን ጠንቅቀው ያውቃሉ:: በጥር ወር 1993 ዓ.ም ለዓለም አብያተክርስቲያናት ስብሰባ ወደ ጀርመን ተጉዞ ከነበረው ከዲ.ን ኤፍሬም እሸቴ ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል:: ተከታተሏቸው::*

<u>ሐመር</u> :- *ስለ ሦርያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአጭሩ ቢገልጹልን?*

<u>አቡነ ኤፍሬም</u> : – ቤተክርስቲያናችን ጥንታዊት ከመሆኗም ባሻገር በክርስትናው ዓለም ትልቅ ታሪክ አላት:: በኢየሩሳሌም ከተማ በሐዋርያት፣በሰባክያን እና በሌሎች አይሁዳውያን እንዲሁም ከአረማዊነት በተመለሱ ምእመናን የተመሠረተች የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ናት:: በሥነ ጽሑፍ፣ በመንፈሳዊ ሀብቷ የበለጸገች ቤተክርስቲያን ናት:: ዛሬም ድረስ ጌታችን ያስተማረው የሦሪያ አራማይክ ቋንቋን ትጠቀማለች:: መንበረ ፓትርያርኩ አሁን ካለበት ደማስቆ ከመጽናቱ በፊት በተለያዩ አገሮች ሲዘዋወር ቆይቶ ነበር:: ምክንያቱ ቤተክርስቲያኒቱ ጸንቶባት የነበረው ስደትና መከራ ነበር:: ለዚህም ነው የታሪክ ምሁራን ሳይቀሩ የቤተክርስቲያኒቱን ከዚያ ሁሉ መከራ መውጣት «ተአምር ነው» የሚሉት:: ፓትርያርካችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ምራን ሞር አግናጥዮስ ዘካ አንደኛ ኢወዝ ናቸው:: ቤተክርስቲያናችን በመላው ዓለም ከ4 ሚሊዮን በላይ ምእምናን አሏት::

<u>ሐመር</u> : – *በአሁኑ ወቅትስ ቤተክርስቲያኒቱ ያለችበት ሁኔታ ምን ይመስላል?*

<u>አቡነ ኤፍሬም</u> : – ያለፉት 30 እና 40 ዓመታት በአንፃራዊነት በሰላም የኖርንበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል:: ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈሳዊም ሆነ በሌላው ዘርፍ ትልቅ ዕድገት አሳይታለች:: ብዙ ክርስቲያኖች ገዳማዊ ሕይወት እየመረጡ በመመንኮስ ላይ ናቸው:: በቅስና ለማገ ልገል የወሰኑም አያሌ ናቸው:: ለዚህም ራሳቸውን የሚያዘጋጁ ወጣቶች አስቀድመው ወደ መንፈሳዊ ት/ቤት ስለሚገቡ ት/ቤቶች ሁሉ ሙሉ ናቸው::

ቤተክርስቲያናችን ባሳለፈቻቸው የመከራ ዓመታት ምክንያት በመካከለኛው ምሥራቅ /በአገራችን/ ካሉት አንጉረ ስብከት ይልቅ በሌላው ዓለም በዝርወት ያሉት ይበልጣሉ:: ለእነዚህ አንጉረ ስብከትና አጥቢያዎች አገልጋዮችን የምንልከው ከመካከለኛው ምሥራቅ ነው:: እስካሁን ድረስ በአውሮፓና አሜሪካ ካሉት ምእመናን መካከል በምንኩስና ለመኖር የሚወስኑ ወጣቶች ማግኘት አልቻልንም:: ለወደፊቱ ይህ ችግር ትልቅ ፈተና ይሆንብናል ብለን እንሰጋለን:: ምክንያቱም የነዚህን አገሮች ቋንቋዎች እና አስተሳሰቦች ማግኘት የምንችለው ከእነዚሁ መካከል ነውና:: በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙት ምእመናን በሁለት ባሕሎችና ግንኙነቶች /Ident ity/ መካከል ተወጥረዋል:: ይህንን ለመፍታት መሞከር ይኖርብናል:: አለ በለዚያ ወጣቶቻችንን ልናጣ እንችላለን:: አብዛኞዎቹ ከየሚኖሩባቸው አገሮች ሕዝቦች ጋር በመዋሐድ /Assi milation/ላይ ናቸው:: ውሕደቱ ደግሞ ፈጣን ነው:: በአጠቃላይ ሁኔታ ከታየ ግን ቤተክርስቲያናችን በጥሩ ደረጃ ላይ ናት ማለት ይቻላል::

<u>ሐመር</u> : – *በአጠቃላይ ሲመለከቱት ቤተ ክርስቲያኒቱ በአሁኑ ጊዜ የገጠማት ትልቅ ችግር ምንድን ነው ይላሉ?*

<u>አቡነ ኤፍሬም</u> : –እኔ ትልቅ ችግር ነው የምለው የሕዝባችን ከፍተኛ ስደት ነው::

<u>ሐመር</u> : – *ለምንድነው የሚሰደዱት? ይህንንም ጨምረው ቢመልሱልን?*

<u>አቡነ ኤፍሬም</u> :- የተለያዩ ምክንያቶች አሉ:: ዋነኛ ግን የኢኮኖሚ ጉዳይ ነው:: የተሻለ ኑሮ ሊኖሩባቸው የሚችሉባቸው አገሮች ይሄዳሉ:: በእርግጥ ድሮ የነበረው ስደት ምክንያት ከዚህኛው ይለያል:: በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ከአገራችን ከቱርክ ደቡባዊ ምሥራቅ እንድንሰደድ የተገደድነው ክርስቲ ያኖች መጨፍጨፍ ስለበዛ ነበር:: በዚህ የኦቶማን ቱሪክ ቱሪኮች ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር በ19ኛው መ/ክ/ዘመን ያደረጓቸውን ጦርነቶች ያስታውሷል:: ከጭፍጨፋ ከ300.000 በላይ ምእመናን አልቀዋል:: ከጭፍጨፋው የተረፉትም አገራቸውን ጥለው በመሔድ በሌሎች አውሮፓ፣የአሜሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ለመኖር ተገደዋል::

በ1950 ዎቹና 60ዎቹ ደግሞ ሌላ የስደት ማዕበል ተነሣ:: በኢኮኖ

ሚ ምክንያት:: የተሻለ ኑሮ ፍለጋ:: ስለዚህ አገልግሎታችን በሁለት ወገን ተወጥሯል:: በስደት ያሉ ምእመናንን ለማገልገል በአውሮፓ፣በካናዳ፣በአሜሪካና በደቡብ አሜሪካ የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናትንና አገር ቤት ያሉትን በማገልገል መካከል:: በውጪ ያለውን ለማጠንከር መሞከራችን የአገር ቤቱን ያዳክምብናል::

በሌላ በኩል በስደት ያሉትን ምእመናን ለማገልገል ጳጳሳቱና ቀሳውስቱ የተለያዩ አገሮች ቋንቋዎችንና ባሕሎችን ለማጥናት ከልክ በላይ ለመዘጋጀት ተገደዋል:: ከዚህ በተረፈ ከሌሎች የኦርቶዶክስ ቤተሰቦች የተለየ ችግር ገጥሞናል አልልም::

ሐመር :- *ብዙዎቹ ምእምናን በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ ከሆነ በነዚህ አኅጉሮች ያለውን ዘመናዊነትና መንፈሳዊነቱን እንዴት ሊታስታርቁላቸው ቻላችሁ?*

አቡነ ኤፍሬም :- በጣም ጥሩና አስፈላጊ ጥያቄ ነው:: ይኼን ሐሳብ ማንሳትህ ደስ ብሎኛል:: ምክንያቱም ጉዳዩ ዕለት ተዕለት የሚገጥመኝ በመሆኑ ነው:: እኔ አሜሪካ ከሄድኩ ገና አምስት ዓመቴ ነው:: ያገሬ ሰዎች ግን 100 ዓመት /አንድ ክ/ዘመን/ ሆኗቸዋል:: ብዙዎቹም ሙሉ በሙሉ ከአገሩ ሕዝብ ጋር ተዋሕደዋል:: አሜሪካውያን ሆነዋ[illegible]:: አሜሪካዊ ያለሆኑም ቢሆኑ በመጨረሻ ሕልማቸው አሜሪካዊነት ሆኗል:: የዚህም ሰበቡ «አማ[illegible] የኔ ናት» የሚል አንድ ዘር ወ[illegible] ጎሳ ባለመኖሩ ነው:: ማንኛ[illegible]ም ሰው አሜሪካዊ መሆን ይችላል::

ይሄ የተለመደ ክስተት ቢሆንም ቤተክርስቲያን ለዚህ መዘጋጀት አለባት:: ባሕላችንን፣ ማንነታችንን፣ ቋንቋችንንና መንፈሳዊነታችንን ከመጠበቅ ጋር ይህንን ህብታችንን ለዘመኑ ትውልድ ተስማሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ አለብን:: ይህንንም ለማድረግ ብዙዎቹን መጽሐፎቻችንን ወደ እንግሊዝኛ በመተርጎም ላይ ነን:: ቅዳሴዎቻችን በብዛት የሚከናወኑት በእንግሊዝኛ ነው:: ይህ ማለት ግን ከሥርዓዊ ትውፊታችን ወጥተናል ማለት አይደለም:: አገልግሎታችንን ለዘመኑ ሰው በሚገባ መልኩ እናዘጋጃለን ማለቴ ነው:: ወጣቱ «ወደ ቤተክርስቲያን መሔድ አልፈልግም:: ቤተክርስቲያኒቱ የአባቴና የአያቴ ነው እንጂ የኔ አይደለም» እንዲል አልፈልግም:: ቤተክርስቲያኒቱ የርሱም መሆኗን እንዲያውቅ፣«የኔ ናት» እንዲል እንፈልጋለን:: ስለዚህም ቅዳሴውን ጨምሮ በሌሎች መርሐ ግብሮችና ጸሎቶች የምእመናን ተሳትፎ ምሉዕ እንዲሆን እያደረግን ነው::

ሐመር :-*የሦርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሦርያውያን ብቻ ናት?*

አቡነ ኤፍሬም : - በድጋሚ ይህም *በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው:: የብዙዎቹን የኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት በተለይም ለአንድ አገር ብቻ የተቋቋሙትን / Ethnic Churches/ ሕይወት ይመለከታል:: በርግጥ ቤተክርስቲያን አሐቲ፣ ቅድስት ፣ሐዋርያዊትና ዓለም አቀፋዊት ናት:: «ዓለማቀፋዊት ናት» የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው የአንጾኪያው 3ኛ ፓትርያርክ ቅዱስ አግናጥዮስ* ነው:: በአንጾኪያ የነበሩት ክርስቲያኖች ከአይሁድነት የተመለሱ፣ ከአረማዊነት የመጡ ወዘተ ተባብለው ተለያይተው በተለያዩ ጳጳሳት ሲመሩ ቆይተው በመጨረሻ በቅዱስ አግናጥዮስ መሪነት በአንድ መንበር ሥር በመጠቃለላቸው የተናገረው ቃል ነው::

ይህም የሚያሳየን ቤተክርስ ቲያናችን የሁሉም መሆኗን ነው:: ለምሳሌ በሕንድ ትልቅ ቤተክርስቲያን አለን:: የሦርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሕንድ:: በርግጥ አሁን ራሣቸውን ችለዋል:: ቢሆንም ለብዙ ዘመናት መምህራንና አባቶች ሲላኩ የነበሩት ከሦርያ ነበር:: አሁን አሁን ግን በዚህ በኩል እየደከምን መጥተናል:: ለዚህም ነው ምእመናኖቻችን ሦርያውያን ወይም ራሣቸውን ሦርያዊ አድርገው የሚቆጥሩት ብቻ የሆኑት:: ምናልባት ወደፊት እናሻሽል ይሆናል::

ሐመር : - *ቀሳውስታችሁ ምእምናንን ለማስተማር፣ለመጠበቅ ለመምከር ወዘተ ምን ያህል ዝግጁ ናቸው?*

አቡነ ኤፍሬም : - በቀደመው ዘመን የነበሩት ቀሳውስት ከምእመኑ ጋር የሚኖሩ፣የሚበሉ፣የሚጠጡ የሕዝብ አካሎች ነበሩ:: ሕዝቡም ከምግባራቸው ይማር ነበር እንጂ በሥነ መለኮት ትምህ ርት እጅግ በጣም የረቀቁ አልነበሩም:: መነኮሳቱ ግን ገዳማውያን በመሆናቸውና ገዳሞቻችንም የትምህርትና የምርምር ተቋሞች በመሆናቸው የተማሩ ናቸው::

የቀሳውስቱን ዕውቀት ለመጨመር፣ምእመናንን ለማስተማርና ከክፉ ትምህርት ለመጠበቅ ቤተክርስቲያን ብዙ መሥራት እንዳለባት ተረድተናል:: ለዚህም በብዙ ቦታዎች መንፈሳዊ ት/ቤቶች አቋቁመናል:: ከዚያ በሚያገኙት ዕውቀትም የዘመኑን ችግር የዘመኑን ጥያቄ ለመመለስ ይችላሉ::

ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያን ያለውን አገልግሎት በተመለከተ ኃላፊነቱን በሙሉ በቀሳውስቱ ትከሻ ላይ መጣል አልፈልግም:: ምእምናንም ቀሳውስቱን መርዳት አለባቸው:: ቢያንስ መሠረታዊውን የሃይማኖት ትምህርት ለማስተማር፣ስለሃይማኖታቸው ለሚጠይቋቸው ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጁ መሆን አለባቸው:: በዚህ ረገድ ብዙ ወጣቶች የሰንበት ት/ቤት መምህራን፣የወጣቶች መሪዎች ሆነው በማየቴ እምላኬን አመሰግነዋለሁ:: ቢሆንም ገና ይቀረናል::

ሐመር: - *እስቲ በሀ/ስብከትዎ ስላሉት የሦርያ ወጣቶች አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ተሣትፎ ይግለ ጹልኝ::*

አቡነ ኤፍሬም : - በሀ/ስብከታችን ውስጥ በሚገኙ አጥቢያዎች በሙሉ ሰንበት ት/ቤቶች አሉን:: በአባቶች መመሪያ ከቤተክርስቲያኑ የተለያዩ ተቋማት ጋር በመተባበር ይሠራሉ:: ዋነኛው ኃላፊነታቸው ዕድሜያቸው ከ 13–30 የሆኑ ወጣቶችን ማሰባሰብ፣ ክርስትናቸውንና በተግባር የሚገልጡበትን መንገድና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጡበትን መንገድ ማመቻቸት ናቸው::

ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ከአገሬው ሕዝብ ጋር መዋሐዱ በፍጥነት እየተከናወነ በመሆኑና እግረ መንገዱን ወጣቶቻችን በሌሎች ባሕል ሰምጠው እንዳይቀሩ በጥንቃቄ እንከታተላለን:: ይህም እንዳይሆን ለወጣቶቻችን ትምህርቶችን፣ ስብሰባዎችን፣ጉዞዎችን እንዲሁም ለአራትና አምስት ቀናት ከከተማ ወጣ ብለው አብረው የሚቆዩበትን፣መጽሐፍ ቅዱስ የሚያጠኑበትን... ዝግጅት እና ዘጋጃለን:: ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ የሥነ ጥበብ ትዕይንት /Art Exhibition/ በማዘጋጀት ወጣቶቹ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙበት እናደርጋለን:: ከመካከላቸው ጥሩ ውጤት ያመጡትንም እንሸልማለን:: ይህንን ሁሉ የምናደርገው ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን እንዲኖሩ ለማድረግ ነው:: ለዚህም የበለጠ ልምድ ያላቸውንና ወጣቶችን በመያዝ በኩል የተሣካላቸው አብያተክርስቲያናትን ልምድ እንወስዳለን::

ሐመር : - *በአሜሪካ አካባቢ ያላችሁት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነታችሁ ምን ይመስላል? አብራችሁ ትሠራላችሁ?*

አቡነ ኤፍሬም : - አብረን በመሥራት ላይ ነን:: ሥራውን ለማቀላጠፍ የጳጳሳት ቋሚ ጉባኤ /Special Standing Conference of Bishops/አለን:: በነዚህ ስብሰባዎች ላይም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብፁዕ አቡነ ማትያስና አንድ ቄስ ተካፋዮች ናቸው:: እርሳቸው በማይመጡበት ጊዜ ቄሱ ይኖራሉ:: በዚህም ወደ ጥሩ ደረጃ ለመድረስ ችለናል:: ለምሳሌ ያህል በጋራ ልንቀድ የምንችልበትን ሁኔታ አመቻችተናል:: ድሮ ግን የየራሳችንን ቅዳሴ ነበር የምንቀድሰው:: አንድ ጊዜ የአርመንን፣ ሌላ ጊዜ የግብፅ ወይም የሦርያ ይቀደስ ነበር:: የአርመኑ ሲቀድስ ሌሎቻችን እንሣተፍም ነበር:: አሁን ግን የየትኛውም ቤተክርስቲያን ቅዳሴ ቢሆን ሁላችንም የምንሣተፍበትን መንገድ አዘጋጀተናል:: ምእመናኑም የአንዱ ቤተክርስቲያን /ወደ ገጽ 11 ዞሯል/

# በባቢሎን ወንዞች አጠገብ

/ዲ.ኤፍሬም እሸቴ/

ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ነው:: እንቅልፍ በአውራ ጎዳናዎቿ ላይ ቀር ወጥቶ የፈሰሰባት የጅዳ ከተማ በኤሌክትሪክ ብርሃን ነድዳለች:: ጌታዬና እመቤቲቱ ከተኙ ቆይተዋል:: የኔ የዕረፍት ሰዓት ገና ነው:: ችኮላዬ ከአይሻ ጋር ያለን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሰዓት ከመድረሱ በፊት ሥራዬን ለማጠናቀቅ ነው:: ከስምንት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ያለው የኔና የርሷ የጸሎትም የትምህርትም ጊዜያችን ነው:: ደግሞ ትንሽም ቢሆን መተኛት አለብኝ:: አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ለመነሣት:: መቼም እዚህ አገር ረዥም የዕረፍት ሌሊት የሚባል አይታሰብም:: መጽናኛዬም ማረፊያዬም ቃለ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ይመስገን አሁንማ አይሻን አግኝቻለሁ::

የአረብኛ መጽሐፍ ቅዱሴን በድብቅ ካስቀመጥኩበት ትራሴ መሐል ፈልፍዬ አውጥቼ ወደ አይሻ መኝታ ክፍል አመራሁ:: ተፍ ተፍ ስል አሥር ደቂቃ አሳልፌ ባታለሁ:: በሩን ከፍቼ ስገባ ተዘጋጅታ ስትጠብቀኝ ደረስሁ:: ሥዕሎቿን ከሚደበቁበት የምሥጢር አገሮቻቸው ሰብስባለች:: ሁለት ሻማዎች ከግራና ከቀኝ አብርታለች:: የኔን ነጣላ መስቀልያ አጣፍታ ለብሳሳያት ቀይ የመንደሬ ኮረዳ እንጂ የቱጃር አረብ ልጅ አልመሰለችኝም ነበር:: መጽሐፍ ቅዱሴን በነጠቁኝና የአንገት ክሬን በጥሰው በጣሉብኝ ቢቻላቸው ከመግደል በማይመለሱት ሰዎች መካከል መኖሬን አሥረሳችኝ:: ፍዝዝ ማለቴን ተመልክታ ኧረ ቶሎ በይ ሰዓቱ እየሄደ ነው ባትለኝ ኖሮ በቆምኩበት የህሳብ ማዕበል ሲንጠኝ ማደሬ ነበር::

የካይሮ ጓደኞቼ የላኩልኝን የአረብኛ የጸሎት መጻሕፍት አውጥተን ጸሎት ስንጀምር ሰዓቱ 8:30 ላይ ደርሶ ነበር:: ጸሎቱን በተኮላተፈ አረብኛዬ አሔደው ገባሁ:: አገር ቤት በእናቴ በአባቴ ቋንቋ ስጸልይ እንኳን ኀሊናዬን ለመሥረቅ የሚንደረደረው የህሳብ ሠልፊኛ አቀላጥፌ በማልናገረው ቋንቋ ስጸልይ ቦታ አለማግኘቱ የእግዚአብሔር ቸርነት በመሆኑ ሁሌም ይደንቀኛል:: በጨለማው መካከል ስለገለጠልን ብርሃን አምላካችንን ስናመሰግን ቆይተን ወደ ዕለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ስንመለስ ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ደቂቃ ብቻ ነበር የቀረን:: የምናጠፋው ትርፍ ጊዜ የለንም:: ከሰዓቱ ጋር መሽቀዳደም አለብን:: የዕለቱን ንባብ አይሻ እንድታነብ ጠቆምኳት:: ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈው መልእክት ምዕራፍ ሁለትን:: በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ ብሎ የሚጀምረውን::

* * *

የጅዳ ሕዝብ ኑሮ እንደአስፖልቱና ሕንፃው ያማረ አይደለም:: የመጣሁ ጊዜ ቆሻሻ የሚናፈቅበት አገር ማለቴን አስታውሳለሁ:: ቆሻሻው ከመንገድ የጠፋው የሰው ሕይወት ውስጥ ተደብቆ መሆኑን መች አወቅሁና:: ኑሯቸው ከንጽሕና በብዙ የራቀ መሆኑን የተመለከትኩት በኋላ ነው::

አይሻ እንደነገረችኝ አባቷ ከዚህ በፊት ሠራተኝነት ተቀጥረው ከነበሩ ፊልፒናውያን ጋር በመዳራታቸው ቤቱ ሰላም የለውም:: እናትየውም ከአባቷ ሕንዳዊ ሾፌር ጋር የተለየ ግንኙነት እንዳላቸው ታውቃለች:: ወንድሟ በሐሺሽ ንፍዝ ማለቱን አይቻለሁ:: በዚህ ዓይነት ምስቅልቅል መካከል ስኖር ከሥራው ይልቅ የነርሱን ጠባይ እንዲያስችለኝ አምላኬን አጥብቄ እለምን ነበር:: ምንም የማይሣነው ጌታ ኃይሉን አድሎኝም በርትቻለሁ::

* * *

አይሻ ማንበቧን ቀጥላለች:: «በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው» የሚለው ላይ ደርሳለች:: ከሁሉም ግን የወጣቷ የአይሻ ነገር ያሳዝነኝ ነበር:: ሌሊት የወላጆቿን መተኛት ጠብቃ ስትወጣ አያታለሁ:: በድብቅ ስትወጣ ከግር ጥፍር እስከ ራስ ጠጉር መሸፋፈን የለም:: ትልቅ ጥቁር ካፖርት ከመደረቧ በስተቀር ከውስጥ የለበሰችው አካሏን የሚያራቁት ልብስ ነው:: ወደ ዳንስ ቤት መሆኑን አላጣሁትም:: ካፖርቱም በኋላ ይወልቃል:: «የነርሱ የመጠጥ ሐራምነት ቀን ብቻ ነው እንዴ?» እላለሁ ለራሴ::

አንድ ቀን ነው:: እንደተለመደው ከዳንሷ ስትመጣ ሰዓቱ ከኔ የጸሎት ሰዓት ጋር ተገጣጠመ:: ሥዕሎቼን ዘርግቼ፣ ሻማዎቼን አብርቼ እየጸለይኩ ነበር:: የመኝታ ቤቴን በር አለመቆለፌን አላስታወስኩም:: አይሻ ገርበብ ያለውን በር ከፍታ ስትገባ የሚያማምሩ ሥዕሎች ፊት ቆሜ አየችኝ:: እኔ አላየኋትም:: አላቋረጠችኝም:: ጨርሼ ዞር ስል በር ተደግፋ ቆማለች:: ሰውነቴን አንዳች ነገር ነዘረኝ:: ፊቷ ላይ ከንዴት ይልቅ ግርምት ነግሦበታል::

ከዚያ ጊዜ በፊት ክርስቲያን መሆኔን ማንም አያውቅም:: ባሪያቸው በመሆኔ ለስግደቱ ጊዜ ባያስታውሱኝም እስላም ለመሆኔ ግን ጥርጥር አልነበራቸውም:: ዛሬ ተገለጠ::

«ክርስቲያን ነኝ!» አልኳት በጎረነነ ድምፅ::

*«ይሄ ከታወቀ አንገትሽን ሊያሰይፍሽ እንደሚችል አታውቂም?»*

«አውቃለሁ!»

*«አትፈሪም?»*

«አልፈራም:: ግን ለመጠንቀቅ ሞክሬያለሁ::»

«ያ የተሰቀለው ማነው?» አለችኝ:: ድንገት ወደ ሥዕለ መድኃኒዓለም እየጠቆመች:: ያልጠበቅሁት ጥያቄ ነበር:: በጩኸት አገር ምድሩን ታናውጠዋለች ብዬ የገመትኳት ቀበጥ ልጅ ተረጋግታ ስመለከታት የያዘኝ ግርምት ሳይለቀኝ ጥያቄዋ የበለጠ አስደነቀኝ::

«የዓለም መድኃኒት፣ ለሁላችን ቤዛነት የሞተው የማርያም ልጅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ማለቴን አስታውሳለሁ:: ንግግሩ የኔ አልመሰለኝም ነበር::

«እግዚአብሔር አይወርድም

አይወለድም» አለችኝ ጠንከር ባለ
አነጋገር::

«ወርዷል ተወልዷል:: ይሄ ተሰ
ቅሎ የምታይው እርሱ ነው» አልኳት::
የንግግር ድፍረቴ ሳይገርማት አል
ቀረም::

የዚያን ዕለት በዚሁ ተለያ
የን:: ለቤተሰቦቿ ነግራቸው ከሆነ ፖሊ
ስ መምጣቱ አይቀርም ብዬ ስጠብቅ
ቀናት አለፉ:: የመጣ ሰው አል
ነበረም:: እኔም በሌሊት ለጸሎት
መቆሜን አላቆምሁም:: ሁለተኛ የተ
ገናኘን ቀን አስባበት የመጣች ትመ
ስላለች:: ለዚህ ጉዳይ የመጣች እንዳ
ይመስልባት ብትጠነቀቅም:: ጓዳ ድረ
ስ መጥታ አጠገቤ ተቀመጠች::

በኋላም

«ስለተሰቀለው ፈጣሪሽ ንገሪኝ እስ
ቲ» አለችኝ:: ደነገጥሁ:: የእንቅልፍ
ሰዓት ስላልደረሰ ባለቤቶቹ የሚሰሙን
መሰለኝ:: ደግሞ ይህንን መልካም አጋ
ጣሚ በዝምታ ላልፈው አልፈለግ
ሁም:: ነገርኳት:: እግዚአብሔር ያቀበ
ለኝን ያህል:: አስቀድመው ነቢያት
የተናገሩትን:: በኋላም ትንቢቱ ተፈ
ፅሞ በወንጌል የተጻፈውን በሙሉ::
በጥሞና አዳመጠችኝ:: ማዳመጥ ትች
ልበታለች:: የበለጠ ለመረዳት ከፈለ
ገች ብዬ የአረብኛ መጽሐፍ ቅዱስ
ሰጠኋት:: ተቀብላ ዝም ብላ ስትመለ
ከተው ቆየች:: ለመግለጥ የፈራች ት
መስላለች:: ለማጣትም አልፈለገችም::
በኋላ ምንም መልስ ሳትሰጠኝ ቱር
ብላ ወጣች:: አንዲትም ምላሽ ሳትሰጠ
ኝ በመሄዷ ተረበሽኩኝ:: «ሳላውቀው
አስቀይሜያት ይሆን?» ብዬ አሰብሁ::
ወደ ልቡናዬ ስመለስ ደግሞ «እኔ
ብናገርም ሥራውን የሚሠራው መድኃ
ኔዓለም አይደል?» ብዬ ተጽናናሁ::

ከሁለተኛ ቀን ንግግራችን በኋ
ላ ሳንገናኝ ለብዙ ጊዜ ቆየን:: ባገኘሁት
ም ከቤተሰቦቿ ጋር ስለምትሆን በዓይን
ከመፈላለግ በስተቀር መነጋገር አልነበ
ረም:: አንድ ለውጥ ግን አይቼባ
ታለሁ:: እንደበፊቱ የቤተሰቦቿን መተ
ኛት እያረጋገጠች መውጣት ትታ
ለች:: ቶሎ እንደማትተኛም አውቃ
ለሁ:: ምን እንደምትሠራ ግን እንጃ::

* * *

የኤፌሶን መልእክት ንባብ
ቀጥሏል:: «በዚህም ዓለም ተስፋን አጥ
ታችሁ ከእግዚአብሔር ተለይታ ችሁ
ያለክርስቶስ ነበራችሁ:: አሁን ግን ...
በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ
ደም ቀርባችኋል::»

አንድ ቀን እንደተለመደው ሥ
ራዬን ጨርሼ ወገቤን መሬት ከ
ማሥነካቴ በፊት ጸሎት ለማድረግ
እየተዘጋጀሁ ነበር:: በሬ ተንኳኳ::
ሥዕሎቼን አውጥቼአለሁ:: ሻማዎ
ቼንም እንዲሁ:: ደነገጥሁ:: በፍ
ጥነት በብርድ ልብሴ ሸፋፈንኳቸ
ውና በሩን ልከፍት ሄድኩ:: አይሻ
ናት:: ተኝታ የምታውቅ አትመ
ስልም:: ዓይኗ ቀይ ኳስ አክሏል::
አልፋኝ ገብታ አልጋዬ ላይ ተቀ
መጠች:: ዝም ብዬ ቆምኩ:: ጥያቄ
የለም:: መልስም የለም:: የማደ
ርገው ጠፋኝ:: ኋላ ዝምታችንን
የሰበረችው እርሷ ራሷው ነበረች::

«የጸሎት ሰዓትሽ ደርሷል::» ጥያቄ
ሳይሆን አስተያየት ይመስላል::
ዝም አልኳት::

«ስትጸልዪ አጠገብሽ ብሆን ቅር
ይልሻል?» አለችኝ::

*«በፍጹም!»*

«እንግዲይውስ ጸልይ:: ለኔም
ጸልይልኝ::»

*«እሺ» አልኳት የራሴ ባልሆነ
ድምፅ::*

«ግን እግዚአብሔር የሚወደኝ ይመ
ስልሻል? ስለሠራሁት ኃጢአት ሁሉ
ይቅር የሚለኝ ይመስልሻል?» ስት
ናገር ልቧ በኃዘን የተሰበረ ይመ
ስላል:: በጣም አሳነዘችኝ::

*«የሞተው እኮ ላንቺ ነው አንቺን
ለማዳን ነው» አልኳት የርሷ ኃዘንና
የልብ መሰበር ለኔም እንደተጋባ
ሁሉ ውስጤ እዝን እያለ::*

*«ከዚህ በፊት እርሱን ሳታውቂው፣
ያደረገልሽንም የፍቅር ሥራ ሳት
ገነዘቢ ቆይተሻል:: አሁን ግን ላንቺ
ብሎ እንደተሰቀለ ያወቅሽ ይመ
ስለኛል» አልኳት::*

«አዎ! ስሞኑን ሳነብ የነበረው እር
ሱኑ ነበር:: አውቄያለሁ:: በእርሱ
አምናለሁ:: ለኔ በሞተው ጌታ
አምናለሁ!» አለችኝ::

ቀስ ብሎ የጀመረው ንግግሯ እየ
ጨመረ ሲመጣ ሮጬ በሩን ዘጋ
ሁት:: ያየችኝ አትመስል:: ዕንባ
ከዓይኖቿ እየፈለቀ ጉንጯቿን ገም
ሦ ይወርዳል:: ሳይታወቀኝ አብሬ
ያት አለቅስ ገባሁ:: ከዚያን ቀን
ጀምሮ እኔና አይሻ የሌሊት ጓደ
ኞሞች ሆንን:: ሁለት ኒቆዲሞሦች
በእስማኤል መንደር::

* *

የኤፌሶን ንባብ መካከል ላይ
የካይሮ ጓደኞቼ የላኩልኝን የአረ
ብኛ መዝሙር አብረን መዘመር
ጀመርን:: እግዚአብሔር ለሰው
ልጆች ያደረገውን ነገር የሚያዘክር
ድንቅ መዝሙር ነው:: ድምፃችን ከፍ
ማለቱ አልታወቀንም:: አገሬ ያለሁ
እንጂ በሰው ምድር፣በባቢሎን ወንዞች
አጠገብ መቀመጤን ራሱ ዘንግቼዋ
ለሁ:: ከሰንበት ትምህርት ቤቴ ልጆች
ጋር አብሬ እንደምዘምር ሁሉ በደስታ
ተውጫለሁ:: ድንገት የመኝታ ቤቱ
በር ሲበረገድ ከየሄድንበት ዓለም ተመ
ለስን:: አባቷ ናቸው:: ዓይናቸውን
ማመን የቻሉ አልመሰለኝም:: አፋ
ቸውን በእጃቸው ይዘው ደርቀው ቀር
ተዋል:: በኋላቸው የመጡት እናትየው
ተዝለፍልፈው ሊወድቁ ሲሉ ግድግ
ዳው ታደጋቸውና ተንሸራትተው
መሬት ላይ ዘጭ አሉ:: የሚሰማው
«ያ አላህ!» የሚለው የአባቷ ድምፅ
ብቻ ነበረ::

* * *

/ይቀጥላል/

## *ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊነትን*

/ከገጽ 11 የዞረ/

*ጥያቄዎቹን ፈጽሜያለሁ:: ሳልጠቅሰው ያለ
ፍኩትና ማንሣት የሚፈልጉት ነጥብ ካለ
ወይም ኢትዮጵያ ለምንገኝ የመንፈስ
ቅዱስ ልጆችዎ ሊያስተላልፉት የሚፈል
ጉት መልእክት ካለ ቢነግሩኝ::*

<u>አቡነ ኤፍሬም</u> : -ይህንን አጋጣሚ በማ
ግኘቴ እንዲሁም በእናንተም በኩል ከኢ
ትዮጵያ ምእመናን ጋር ለመገናኘት በመ
ቻሌ በጣም ደስ ብሎኛል::

ኢትዮጵያውያን ከጥንት አባቶቻሁ የወረ
ሣችሁት ብዙ መንፈሳዊ ሀብት አላችሁ::
በቤተክርስቲያናችሁ የሚፈጸሙ በሌሎች
ቦታዎች የጠፉ ጥንታውያን ሥርዓቶችም
ንጽሕናቸው እንደተጠበቀ የሚገኙት እና
ንተ ዘንድ ብቻ ነው:: ይህ ጥንታዊ ሀብት
እንደተጠበቀ ይቆያል ብዬ ተስፋ አደር
ጋለሁ:: በተጨማሪም በአባቶች መካከል
ያለው መለያየት ተወግዶ ቤተክርስቲያኒቱ
በአንድ መስመር ትሄዳለች ብዬ ተስፋ
አደርጋለሁ:: በእውነት በቤተ ክርስቲያን
አባቶች መካከል የተፈጠረውን መለያየት
ስንሰማ ልባችን ነው የደማው:: ችግሩ ይወ
ገድ ዘንድም የሁልጊዜ ጸሎታችን ነው::
ይህ መለያየት ተወግዶ ቤተክርስቲያን ለጋ
ራ ሃይማኖታችን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
መስፋፋት በጠነከረ መንገድ የምትሠራ
በትን ጊዜ ለማየት እናፍቃለሁ::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ከሌሎች የኦሪየንታል አብያ
ተክርስቲያናት የተለየና የከበደ ኃላፊነት
አለባት:: ይህም በአፍሪካ በመኖሯና አፍሪ
ካዊት ከመሆኗ ጋር የተያያዘ ነው:: ኢት
ዮጵያ ኦርቶዶክሳዊነትን ላላየውና ላልቀ
መሰው፣የኦርቶዶክሳዊነት ብርሃን ላልበራ
ለት ለቀሪው የአፍሪካ ክፍል የማድረስ ኃላ
ፊነት አለባት:: በርግጥ ግብፅን የመሳሰሉ
ሌሎች የኦርቶዶክስ አብያተክርስቲ ያናት
በማስተማር ላይ ናቸው:: ነገር ግን በኔ
አስተያየት አፍሪካን ለማስተማር ትልቁ
ኃላፊነት ያለባት የኢትዮጵያ ቤተ
ክርስቲያን ናት::

<u>ሐመር</u> : - *እግዚአብሔር ይስጥልን ብፁዕ
አባታችን::*

# ደብረ ማርያም ቆርቆር ዘገረዓልታ

*አቶ ግርማ ኤልያስ*

*በሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 4 እትም ላይ ባወጣነው ጽሑፋቸው በምሥራቅ ትግራይ ሀገረ ስብከት የሚገኘውን ደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ገዳምን ያስተዋወቁን አቶ ግርማ ኤልያስ በዚህ እትም ደግሞ በገረዓልታ ገደላማ ተራራዎች ሽቅብ ይዘውን ወጥተው የቀደምት አባቶቻችንን የሃይማኖት ፍቅር፣ጽናትና ተጋድሎ እንድናስተውል የቆርቆር ደብረ ማርያምን ጥንታዊት ገዳም የማየት ያህል ያስነብቡናል። ለዚህም መልካም ሥራቸው በእግዚአብሔር ስም ምሥጋናችንን እናቀርባለን።*



ትግራይ... ከመቀሌ ተነሥቶ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመኪና ከ40 ኪሎ ሜትር ጉዞ በኋላ በምሥራቅ የዓዕዳ ዕምባ ተራሮች፣ከፊት ለፊት የዓይባ ገማድ ተራሮች ድቅን ብለው ይታያሉ። የውቅሮ ከተማን አቋርጦ ድልድዩን ተሻግሮ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ከ17 ኪ.ሜ ርቀት በኋላ ጥንታዊውና ታሪካዊው የአብርሃ ወአፅብሃ ገዳም በስተቀኝ አቅጣጫ በቅርበት ይገኛል። ስሉህ ከተባለው ወንዝ ባሻገር ከጥቂት ኪሎ ሜትሮች በኋላ ነጭ፣ቢጫ፣ቀይና ሐምራዊ ሕብረ ቀለማት ያላቸው አሸዋማ ድንጋዮች የገረዓልታ ተራሮች እና ዓምባ ምድሮች ደረታቸውን ሰጥተዋል። የአካባቢው ተወላጅ ወይንም ዕድል አጋጥሞት ጎብኝቷቸው የተመለሰ ካልሆነ በስተቀር ዝንጀሮና ጦጣ እንጂ የሰው ልጅ የሚደርስባቸው ቦታዎች አይመስሉም። ምሥጢራቸውንም ለማያውቅ እንግዳ ደራሽ መንገደኛ በእነዚህ ገደላማ ተራሮች አናት ላይ ቅዱሳን አባቶች ተአምር ሰርተውባቸዋል ብሎ መገመት አይቻልም።

በእነዚህ የገረዓልታ ተራሮች አናት ላይ የአባቶቻችን የጽናት፣ ጥረትና ጥበብ ውጤት ከሆኑት ጥንታውያን ገዳማት መካከል አንዱ ከባሕር ወለል በላይ 2700 ሜትር ከፍታ ላይ ጉብ ብሎ የሚገኘው የቆርቆር ደብረ ማርያም ገዳም ነው።

በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት እንደታነጸ የሚነገርለትንና በአውላላ ሜዳ ላይ የተሠራውን ድጉም ሥላሴን አልፎ ወደ ሃውዜን በሚወስደው አውራጐዳና ሲጓዙ ወደምዕራብ አቅጣጫ እንደ ግብጽ ፒራሚዶች ተደርድረው ከሚታዩት የሆዓ ገረዓልታ ተራሮች ሰሜናዊ ጠርዝ ላይ ይደረሳል። በዚያ ቆርቆር ደብረ ማርያም የተመሠረተችበት ከፍተኛ ተራራ ፊት ለፊት ይታያል።

ከዋናው አውራ ጐዳና ወደ ምዕራብ ተገንጥሎ እስከ ቆርቆር ደብረ ማርያም ገደላማው ተራራ ስር ለመድረስ አንድ ሰዓት ያህል በእግር ያስኬዳል። በዚህ መንገድ ላይ ወደ ደብረ ማርያም የሚጓዙ መናንያን የሚያርፉባት ምዕራፈ ጻድቃን የተባለች ጥንታዊት ትንሽ የህድሞ ቤተ ክርስቲያን አለች። በዚያ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ዕረፍት ይደረጋል። መውጫና መውረጃው በየት እንደሆነ ግራ የሚያጋባውንና ነጭና ቀይ ቀለም የተዋሐደውን አስፈሪ ገደል ቀና ብለው ሲያዩት አናት ላይ የሚወድቅ ይመስል ሆድ ያባባል።

ከ1600 ዘመናት በፊት የነበሩት ቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአፅብሃ ከአክሱም ወደ ቆርቆር ደብረ ማርያም የሚያስወጣውን የሚያስፈራራ ገደል አይተው አስቸጋሪነቱን ተገነዘቡ። ከዚያ መላ ፈለጉና መወጣጫ መንገድ ለማሠራት አሰቡ። ያንን የሚያስፈራራ ገደል ለሁለት አስተረተሩት። ሽቅብ ወደ ላይ ለሁለት ያስተረተሩትን ገደል ሐፀም ከሚባል የአክሱም ሜዳማ ስፍራ ጥቁር እና ድቡልቡል ድንጋይ እያስጋዙ በመሙላት 500 ሜትር ያህል ርዝመት ያለውን የገደል ጐዳና አስደልድለው አሠሩት። በዚህ ዓይነት ወደዚህ የተቀደሰ ቦታ ለሚወጡና ለሚ ወርዱ ቅዱሳን መልካም ጐዳና እንዳሠሩላቸው ይነገራል።

በምዕራፈ ቅዱሳን /ጻድቃን/ ተብላ የምትታወቀው ቤተክርስቲያን ዕረፍት ከተደረገ በኋላ በዚያ ጥንታዊ የገደል ላይ መንገድ ሽቅብ መውጣት ይጀመራል። ልብ ድካም ያለበትና አቅሙ ያነሰ ሰው በዚያች ዕረፍት ባደረገባት ቦታ ተቀምጦ ወደ ላይ አንጋጦ እየተመለከተ የወጡት እስኪመለሱ ከመጠበቅ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለውም። የተሟላ ጤንነትና አቅሙ የበረታ ግን የዛሬ 1600 ዘመናት አብርሃ ወአፅብሃ ባሠሩት የገደል ላይ ደረጃ መሰል ጎዳና ወደ ደብረ ማርያም ጉዞውን ይቀጥላል። የዚህን ጎዳና ገፅታ ለመግለጽ ያህል ሁለት ሜትር ስፋት ባለው ደረጃ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ላይ ሳይጠማዘዙ ቁና ቁና እየተነፈሱ ቀጥ ብሎ ወደ ላይ እንደ መውጣት ማለት ነው። አንደኛው ደረጃ አቀበት እንደ አለቀ ከሁለተኛው ምዕራፈ ቅዱሳን ይደረስና በዚያ ከተሰዓቱ ቅዱሳን አንዱ የሆኑት አባ ይምዓታ የመሠረቱትን ገዳም እንዳባ ይምዓታ ሹል ተራሮችን ወደ ምዕራብ እየተመለከቱ ጥቂት ደቂቃዎች እንዳረፉ የሁለተኛው እርከን አቀበት ይቀጥላል። በዚህ ምዕራፈ ቅዱሳን ግን እንደዛሬ ሳይሆን ብዙ መነኮሳት በነበሩበት፣ረድኤትና በረከት ባልተለየበት ዘመን እንግዳ ተቀባዮቹ መነኮሳት የመንገደኛውን እግር አጥበው ምግብና ውኃ ሰጥተው ያስተናግዱበት የነበረ ከዓለት የተፈለፈለ ትልቅ ሕንፃ ዋሻ ጥቀርሻ ለብሶ ቆሻሻ ሞልቶበት ይገኛል። እዚህ ሆኖ ከፊት ለፊት በመጨረሻው ረዥሙ የገረዓልታ ተራሮች ጫፍ ላይ የተመሠረተችው ቀመር አርባእቱ እንስሳ ወደ ተባለችው ድንቅ ሕንፃ ቤተክርስቲያን የሚያስወጣው ጠመዝማዛ የገደል ላይ ጐዳና በሩቁ ይታያል።

የሁለተኛውን ምዕራፍ ጉዞ በአገሬው ሰዎች መሪነት የምዕራባዊው የቆርቆር ደብረ ማርያምን ገዳም እጅግ በጣም ጠባብና ገደላማ ጎዳና በጥንቃቄ ለግማሽ ሰዓት ያህል ወደ ላይ ከተጓዙ በኋላ ቅዱሳን የፈለፈሉት ትልቅ ዋሻ በቀኝ በኩል ጨለማ ለብሶ ዳዋ ውጦት ይታያል። ይህ ዋሻ በጥንት ጊዜ የደብረ ማርያም መነኮሳት ጸሎተ ፍትሃት፣ ተዝካርና ድልዋን እየተደገሰ ካህናቱ ፣ዲያቆናቱ፣መነኮሳቱና ተማሪዎቹ የሚ መገቡበት የገዳሙ ልዩ ቤተ ምርፋቅ እንደ ነበረ ይነገራል። በአሁኑ ወቅት ግን ዳዋ ለብሶ፣እሾህና አሜኬላ በቅሎበት የዱር አራዊት መደበቂያ ሆኖ ይገኛል።

የሁለተኛው የገደል እርከን /ደረጃ/ እንዳለቀ የቆርቆር ደብረ ማርያም ሕንፃ ቤተክርስቲያን ተፈልፍሎ የታነፀባት ገደ

ላማ ዓምባ እንደመሶብ ለብቻዋ ተለይታ ትታያለች:: በሰሜን ታቦተ ማርያም፣ በደቡብ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን፣በምሥራቅ የዚችው ገዳም ዝነኛ አባት የአቡነ ዳንኤል ቤተ ጸሎትና ሕንፃ ቤተክርስቲያን፣በአናቷ ላይ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ጸሎት ቤት የታነጹበት አምባ ይገኛል:: በአቡነ ተክለሃይማኖት ስም የተሰየመው የገዳሙ ፈዋሽ ጠበል በስተግራ በኩል ካለው ገደል ውስጥ አለ:: በዚህ ሁኔታ አድካሚው ገደላማ ጉዞ ከተጠናቀቀ በኋላ በትንሽ የድንጋይ ካብ ከታጠረው የደብረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይደረሳል::

የገዳሙን አመሠራረት ታሪክ በተመለከተ በጽሑፍ የተቀመጠ ተጨባጭ መረጃ አይገኝም:: ከአበው እየተላለፈ በመጣው ታሪክ መሠረት ግን ቆርቆር ደብረ ማርያም በአብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግሥት ከዓለት ተፈልፍሎ ቤተክርስቲያኑ እንደታነፀ ይነገራል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ገዳሙ በዓተ ቅዱሳን መካነ ጻድቃን ሆኖ ቆይቷል:: በይበልጥ ግን በአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእነ አቡነ ተክለሃይማኖትና አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ዘመን የነበሩ አቡነ ዳንኤል ወይም አቡነ እብነ ሰንበት በመባል የሚታወቁት ጻድቅ መነኩሴ እንደገና በገዳምነት አቅንተውታል::

ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በዚህ ገዳም ተምረው አድገው በመመንኮስ በዲቁናና በቅስና እያገለገሉ የኖሩት የዘጠና አምስት ዓመት የዕድሜ ባለጸጋና የቆርቆር ደብረ ማርያም አበምኔት አባ ኃይለ ሥላሴ ተድላ ገዳሙ በገሪዓልታ ታላቅና ዝነኛ መካነ ቅዱሳን ሆኖ እንደቆየ ይናገራሉ::

የቆርቆር ደብረ ማርያምን ሕንፃ ቤተክርስቲያን ታሪክና ውስጣዊ የግብረ ሕንፃና ሥዕሎች ይዘት እንመልከት:: ቤተክርስቲያኒቱ ቅድስቷና ቅኔ ማኅሌቷ ከታች እስከ ላይ በሥዕልና በሐረግ የተሞላ ባለ ሦስት ቤተመቅደስ ነች:: የድንጋይ ሕንፀቱ ጉዳይ ቀደም ሲል የተጠቆመው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥዕሉ ዕድሜ ግን ያለምንም ጥርጥር በአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ ዳንኤል ወይም በደቀመዝሙሮቻቸው የተሳለ ለመሆኑ በሥነ ጥበብ ታሪክ ተመራማሪዎች የተረጋገጠ ነው:: በዘመነ አክሱም ከተሳሉት የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ሥዕሎች ቀጥሎ በትግራይ ክልል በዕድሜ ርዝማኔው በሁለተኛነት ይመደባል:: ቆርቆር ደብረ ማርያም በመላው ትግራይ ከሚገኙ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ከበርካታዎቹ የገሪዓልታ አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ሥዕሎች በማምባር ቀደምትነት የምትገኘውም ለዚህ ነው::

በቆርቆር ደብረ ማርያም የተሳሉ ሥዕሎች በከፍተኛ ጉዳት ላይ የሚገኙ ናቸው:: በየሥዕሉ ግርጌ የተጻፈውን መግለጫ በማንበብ በተገኘው መረጃ መሠረት የአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቅዱሳን ሥዕሎች ይዘት ምን ይመስል እንደነበር የሚጠቁመን ይሆናል:: በሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙት ሥዕላት በየአቅጣጫው ሲተነተኑ የሚከተለውን መልክ ይይዛሉ::

1. ሰሜን

ሄዋን እንተ አስሃታ ከይሲ
ቂርቆስ ፀልይ በእንቲአነ
ሩፋኤል መልአክ
አባ እንጦንስ
አባ መቃርስ
ወአርባእቱ እንስሳ
ኢየሱስ ክርስቶስ በሆሳእና
ወዝንቱስ ባሕር ዘከመ ተፍአ ለዮናስ



2. በደቡብ

ዘከመ ወለደቶ ለክርስቶስ
ሚካኤል ገብርኤል
ሠለስቱ ደቂቅ ቅዱስ ገብርኤል
ሠራዊተ ናቡከደነፆር
ወዝንቱስ አብርሃም ወይስሐቅ ወልዱ
የጻድቅ ሥዕል
ቅዱስ ቴዎድሮስ
አባ ገሪማ ካህን ወሰማዕት
አራት ቅዱሳን በቅድስት ዓምድ
ጽሕሙ እስከ ዘባኑ

3/ መቅደስ

ስሙ ያልተገለጸ ጻድቅ
እስጢፋኖስ ጸለየ በእንቲአነ
አናፍሬምስ ዓምድ 2 የመሳሰሉት ሥዕሎች እስከነ ጽሑፎቻቸው በግልጽ ይነበባሉ::

ከዚህ ሌላ በደብረ ማርያም ከፍተኛ ተራራ ዙሪያ ከዓለት ተፈልፍለው የታነፁ በርከት ያሉ ቅዱሳን ቦታዎች ይገኛሉ::

በቆርቆር ደብረ ማርያም ገዳም አበምኔት በአባ ኃ/ሥላሴ ገለፃና መረጃ መሠረት ዝርዝር ታሪካቸውን በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ ባንችልም የቅዱሳን መካናቱን ስም ዝርዝር ብቻ ጠቁመን እናልፋለን::

ደብረ ማርያም ሕንፃ ቤተክርስቲያን ባለሦስት ቤተመቅደስና ባለ አሥራ ሁለት ዓምድ፣በደብረ ማርያም ሕንፃ ጥግ ቤተልሔምና ሁለት ቤተጸሎት፣ የአቡነ ዳንኤል ቤተ ጸሎትና ቤተልሔም፣እንዳ ጊዮርጊስ ሕንፃ ቤተክርስቲያንና ቤተልሔም፣እንዳ አቡነ እብነ ሰንበት ግብረ ሕንፃ፣ እንዳ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ቤተጸሎት፣ እንዳ አቡነ ጳውሎስ ግብረ ሕንፃ፣ እንዳ አቡነ ኤፍሬም ግብረ ሕንፃ፣ እንዳ መምህርና ዓምዱ፣እንዳ መምህር ገብረ ሕይወት፣እንዳ ግብረ ማህሬፅ ሕንፃ፣ ቤተማኅበር ምርፋ፣ ቤተ መነኮሳት ግብረ ሕንፃ /ጠቅላላ ስምንት/፣ ቤተመጻሕፍት ግብረ ሕንፃ ሦስት ክፍል፣የአባ ወልደ ሥላሴ አበራ መኖሪያ ቤት የተባለ በ1987 ዓ.ም ከቤተክርስቲያኑ በስተምሥራቅ ገጽ ሕንፃ አለ ብለው በመጠራጠር አንድ ወር ሙሉ አፈሩን እየዛቁ አውጥተውት ነበር:: ተደፍኗል:: በተጨማሪ በ1977 ዓ.ም.አባ ተስፋይ ገብረ ኢየሱስ የተባሉ መነኩሴ ያነፁዋቸው ሁለት መኖሪያ ክፍሎች ግብረ ሕንፃ፣ ጥንት የመነኮሳት ጸሎት ቤት የነ በሩትና ዘመነ ሽዬ ከተባለው ዘመነ ጦርነት ወዲህ በጦርነቱ የሞተው ሕዝብ አስከሬን የተቀመጠበትና የታሸጉ ከሠላሣ የማያንሱ ሕንፃዋሻዎች፣አባ ተስፋዬ የተባሉ መነኩሴ ለውኃ ማጠራቀሚያ ፈልፍለው ያነጿቸው ጉድጓዶች፣በደብረ ማርያም ገዳም ቤተክርስቲያኑ ሲታነፅ አብረው የታነፁ፣ መግቢያቸው አንድ ሆኖ ከሁለት ሜትር ጥልቀት በኋላ በአራት ማዕዘን በሮችና በውስጣቸው ሰፋፊ ክፍሎች ያሏቸው መልካብ መካነ መቃብር በመባል የሚታወቁ /9X4=36/ ክፍሎች ይገኛሉ::

በእነዚህ ክፍሎች የጥንት ነገሥታት፣ የበቁ ቅዱሳን፣የታላላቅ ሰዎች መቃብሮች እንደሚገኙ በዝርዝር ያስረዳሉ:: አባ ኃይለ ሥላሴ የዘጠና አምስት ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ቢሆኑም የደብረ ማርያም ገዳምን ታሪክና ሁኔታ በስፊው ስለሚያውቁ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ያለምንም እንከን አዳምጠው መልስ የሚሰጡ አባት ናቸው:: ከአባቶች ባገኙት መረጃ መሠረት ተስው ረውያሉና ለወደፊት በዕድለኞች የሚከፈቱ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ይናገራሉ:: /ወደ ገጽ 11 ዞራል/

# አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ



እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የፍቅሯን ምልክት ነጭ ዕጣንና የሚያበራ ዕንቁ ሰጥታቸዋለች:: አባታችንም «እነዚህን ሥጦታዎች የምትሰጭኝ ምን ባደረግሁ ነው?» ብለው በጠየቋት ጊዜ «ዕጣኑ የምዑዝ ክህነትህ ፣ዕንቁው የንጽሕና የድንግልናህ እና የቅድስናህ ናቸው» በማለት ተርጉማ ነግራቸዋለች::

ገዳም ገብተው ማደሪያ መጠለያ ሳይፈልጉ ጫካ ለጫካ፣ፍርክታ ለፍርክታ ከአናብርት፣ ከአናብስት፣ ከዝሆኖች ጋር አብረው በአንድነት ይኖሩ ነበር:: ሌሎችም አራዊት ሲያይዋቸው እናቱን እንዳየ እንቦሳ በደስታ ይፈነጩ ነበር:: እኚህ ጻድቅ አባት ከአንዱ ገዳም ወደ አንዱ ገዳም..ከቦታ ወደ ቦታ በሚዘዋወሩበት ጊዜ እሳቸው በአንድ አንበሳ ተቀምጠው መጻሕፍቶቻቸውን ደግሞ በሌላው አንበሳ ላይ ጭነው እንደሆነ በገድላቸው ላይ የተጻፈው ታሪካቸው ያስረዳናል::

የጻድቁ አባታችንን ታሪክ ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ያመጡልን አባ ገብረ እግዚአብሔር አብርሃ ዘዋልድባ ናቸው:: ስላደረጉልን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም ምሥጋናችንን እያቀረብን ለመጽሔት በሚሆን መልኩ እንዲህ አቀናብረነዋል::

አቡነ ሳሙኤል የተባሉት እኚህ ታላቅ ጻድቅ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ክፍለ አገር በአክሱም ከተማ አካባቢ በ1295 ዓ.ም. ተወለዱ:: ወላጅ አባታቸው እስጢፋኖስ እናታቸው አመተ ማርያም ይባላሉ:: ከቅዱስ ያሬድ የትውልድ ሐረግ እንዳላቸውም ይነገራል:: ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በአክሱም ጽዮን በነበሩት መምህራን ከፊደል ጀምረው የቅዱስ ያሬድን ጾዋትወ ዜማና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ተምረው ለሰባት ዓመታት ያህል በዲቁና ማዕረግ ሲያገለግሉ ቆይተዋል:: ከዚህ በኋላ ከአክሱም ከተማ በስተሰሜን ምዕራብ ወደሚገኘው የታላቁ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ገዳም ሄዱ:: በዚሁ ገዳም በወቅቱ ከነበሩት ሊቃውንት ዘንድ የብሉያትና የሐዲሳትን ትርጓሜ ፣ሥርዓተ ምንኩስናን ተምረው በገዳሙ አባት በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ እጅ ሰባቱ ከዋክብት ተብለው ከሚጠሩት ቅዱሳን አባቶች ጋር በአንድነት መንኩሰዋል:: እነዚሁም አባቶች አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣አባ ሳሙኤል ዘቆየፃ፣አባ ሳሙኤል ዘጣሬጣ፣አባ ዮሐንስ ዘዛግራ ነቀወ፣አባ ይሳይ ዘመንዳባ፣አባ ያፌቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤ፣አባ ታዴዎስ ዘባርዋ ታርዋ ናቸው::

ጻደቁ አባታችን በዚሁ በደብረ በንኮል ገዳም ሌት ተቀን በጾም በጸሎት በስጊድ በቀዋም ፈጣሪያቸውን እየለመኑ አባታቸው አቡነ መድኃኒነ እግዚእን እየረዱ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ሳይለዩ ብዙ ገድልና ትሩፋት ፈጽመዋል:: ይህም ሲሆን ትሩፋታቸውን ለማንም አይገልጹም ነበር:: አንድ ቀን አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ማኅበሩን ሰብስበው ጉባኤ ሠርተው በሚያስተምሩበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው የወደፊት ሁኔታ ተገልጾላቸው ከምርቃት ጋር ከተናገሩ በኋላ «ከእናንተ ከልጆቼ መካከል ከእሱ በፊትም ከእሱ በኋላም እንደሱ ያለ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አይገኝም» አሏቸው:: ደቀመዛሙርቱም «ማን ነው?» ሲሉ ጠየቋቸው:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ «ሳሙኤል ነው» በማለት መለሱ:: ሳሙኤል የሚባሉት ብዙ ነበሩና ማንኛው ሳሙኤል ነው? ቢሉአቸው «በአክሱም የተወለደው ልጄ ሳሙኤል ነው» ሲሉ ነገሯቸው:: አቡነ ሳሙኤል የተሰበሰበው ጉባኤ ሁሉ በመገረምና በአክብሮት ሲመለከታቸው አፍረው ሮጠው ሄዱና ከአንድ መናኝ አጽፍ ተጠግተው ተሸሸጉ::

ጻድቁ አባታችን ትምህርተ ወንጌልን በማስፋፋት በምዕራባዊ የትግራይ ክፍል ለብዙ ዘመናት ቆይተዋል:: በሰሜናዊ ምዕራብ የጐንደር ክፍለ አገርም የወንጌልን ትምህርት በሰፊው አዳርሰዋል:: ብዙ ትሩፋትና ገድል ፈጽመዋል:: ጣና ውስጥ በሚገኙት ገዳማትና መንዳባ ገሊላ ጋራ ከመሳሰሉት ቦታዎች በምድር ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው እየገቡ ከእህል ውኃ ተለይተው ምንም ሳይቀምሱ ሁለትና ሶስት ሱባኤ ይፈጽሙ ነበር:: በየሄዱበትም ሁሉ አበው ቅዱሳንን መጠየቅ፣ ትምህርታቸውንና መንፈሳዊ ጥበባቸውን መቅሰም፣አቅመ ደካሞችን መርዳት የተለመደ ተግባራቸው ነበር::

ከሁለት ቅዱሳን ወንድሞቻቸው ከአባ ሳሙኤል ዘወገግና ከአባ ቢንያም ዘታህታይ በጌምድር ጋር በመሆን ዝቋላና ምድረከብድ ድረስ ሄደው ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጋር በተገናኙ ጊዜ ብዙ ተአምራት እንደተደረገላቸው መጽሐፈ ገድላቸው ያስረዳል::

በኤርትራ የሚገኘውን ገዳም ከመሠረቱት ከአቡነ ፊልጶስ ጋር እየተገናኙ በጾም በጸሎት ቢጸኑ በብህትውና ቢወሰኑ የቱን ያህል ክብር እንዳገኙና መንፈሳዊ ምሥጢር እንደተገለጸላቸው ሁሉ ይወያዩ ነበር:: ገድለ ቅዱሳንን በማስታወስ አባ እንጦንስን፣ አባ መቃርስን፣አባ ጳኩሚስንና የመሳሰሉትን ገድልና ትሩፋታቸውን እንዲሁም ከፈጣሪያቸው ያገኙትን ጸጋና ክብር ይወያያሉ::

በዚህን ጊዜ አቡነ ፊልጶስ «ዛሬ በእኛ ጊዜ ከእነዚህ አባቶች ማዕረግ የሚደርስ የለም:: አንተም አባታችን ጾም ጸሎትህ ገድልህ ብዙ ነው:: ቢሆንም ከእነሱ ማዕረግ የምትደርስ አይመስለኝም» አሉአቸው:: አባ ሳሙኤል በትኅትና «አባ እስከዚህ ድረስ ለምን ትገምተኛለህ? እኔኮ ሰነፍ አገልጋይ ነኝ:: የታዘዝኩትንም አልሠራሁም:: በእርግጥ ፈጣሪ ያደረገልኝን ምሥጢር ከአንተ ከወንድሜ አልሰውርም:: እነሆ ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር በአንድነት መንበረ ጸባኦትን ማጠን ከጀመርኩ አሥራ ሁለት ዓመት

ሆኖኛል» በማለት ተናገሩ:: አቡነ ፊልጰስም በድንጋጤ ተነሥተው ለአቡነ ሳሙኤል ሰግደዋል::

ጻድቁ አባታችን አቡነ ሳሙኤል ከፈጣሪያቸው ባገኙት ጸጋ ትንቢት በዋልድባ እስከ ምጽዓት ድረስ እልፍ አእላፋት መንፈሳውያን ልጆች በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የሚወለዱላቸው፣መካነ ዕረፍታቸውም መካነ መቃብራቸውም መሆኑን አውቀዋል::

በሰኔ ሃያ አንድ ቀን በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዕለት አቡነ ሳሙኤል በመካነ ጸሎታቸው ተወስነው በትጋት ሲጸልዩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጸላቸው:: «ወዳጄ ሳሙኤል ሆይ ሰላምታ ይገባሃል» የሚል ድምዕ ሰሙና ደንግጠው ቆሙ:: ጌታችንም ቀረብ ብሎ «በዛሬው ዕለት የእናቴ የድንግል ማርያም በዓል ነውና እንድትቀድስ» በማለት አዘዛቸው:: እርሳቸውም «እኔ ኃጢአተኛ ነኝ:: ለመቀደስ አልበቃሁም በማለት ነው ከቤተክርስቲያን አገልግሎት የተለየሁት» ብለው መለሱ:: ጌታችን «ስለዚህ ትኅትናህ ነው በዛሬው ዕለት እንድትቀድስ የመረጥኩህ» አላቸው:: ወዲያውኑ አቡነ ሳሙኤል ከፈጣሪያቸው ሥርየትና ቡራኬ ተቀብለው ቅዳሴ ገቡ::

ሥርዓተ ቅዳሴውን አድርሰው ከፍሬቅዳሴው ደርሰው «ጐስዓ ልብየ ቃለ ሠናየ÷ ጐስዓ ልብየ ቃለ ሠናየ÷ ጐስዓ ልብየ ቃለ ሠናየ» ባሉ ጊዜ የሚቀድሱበት ቤተክርስቲያን አንድ ክንድ ከስንዝር ከምድር ለቆ እንደደመና በአየር ላይ ቆመ:: ቅዳሴው ተፈጽሞ እትው እስኪባልም እንደቆመ ቆይቷል:: በቅዳሴው ፍጻሜ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰው ልጆች የተወለዱትን ሁሉ ወደፊትም እስከ ምጽአት የሚወለዱትንም እልፍ አእላፋት መናንያን መነኮሳት ሰብስቦ በአምላካዊ ሥራው ሕያዋን አድርጐ አሳያቸው::

አቡነ ሳሙኤል በመገረም «አምላኬና ፈጣሪዬ ሆይ ይህንን ያህል ብዛት ያለው ሰው ከምን የመጣ ነው?» ብለው ጠየቁ:: ጌታችንም «እነዚህ እስከ ምጽአት ድረስ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከአንተ የሚወለዱልህ ልጆች ናቸው:: በአንተ እጅ እንዲባረኩ አምጥቻቸዋለሁ እና ባርካቸው» በማለት ነግሮአቸዋል:: በጊዜው የተወለዱትም ሆነ ወደፊት እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የሚወለደው፣ የአቡነ ሳሙኤልን ስም የሚጠራ፣መታሰቢያቸውን የሚያደርግ፣በአማላጅነታቸው የሚያምን ሁሉ በአንድነት ተባርኳል::

ጻድቁ አባታችን አቡነ ሳሙኤል ቅዳሴ ማርያምን አዘውትረው ይጸልዩ ነበር:: በጸሎታቸው መጨረሻ ውኃውን ሲባርኩት ተለውጦ ኅብስት ይሆንላቸው ነበር:: አሳቸውም ትንሽ ቀምሰው ንሥኡ ኅብስተ በረከት እያሉ ለደቀመዛሙርቱ ይሰጧቸው ነበር:: እመቤታችን «ቅዳሴዬን ከውዳሴዬ አንድ አድርጐ የሚጸልየውን አንተ ከገባህበት ውሳጤ መንጦላዕት አገባዋለሁ:: ይህንንም ለልጆችህ ለልጅ ልጆችህም ንገራቸው» በማለት ሰላዘዘቻቸው ዛሬ በዋልድባና በደብረ ዓባይ ቅዳሴ ማርያምን ከውዳሴ ማርያም ጋር ያጠናው በቃሉ ያላጠናው በመጽሐፍ ሳይደግም የሚውል የለም:: ይህ ቃል ኪዳን የተሰጠው ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን ለሚደግምና ለሚጸልይ ክርስቲያን ሁሉ ነው::

አቡነ ሳሙኤል የዋልድባን ምድር አስባርከውታል:: ከእሳቸው በፊት በቦታው የውኃና የቋርፍ ችግር እንደነበረ ታሪክ ይናገራል:: ጻድቁ አባታችን ካስባረኩት በኋላ ግን ወንዞቿና ምንጮቿ በበጋና በክረምት የማያቋርጡ ሆነዋል:: የተለያዩ ዛፎችና የቋርፍ ዓይነት፣ሥራሥርና ቅጠላ ቅጠሉ ሁሉ ለምልሞ እንደልብ የሚገኝበት ቦታ ሆኖአል:: ዋልድባ ብቻ ሳይሆን ደብረ ዓባይም አቡነ ሳሙኤል የደረሱበት ሁሉ ውኃ የሞላበት፣በልምላሜና በጽጌ ያጌጠ በረከት የበዛበት ነው::

ጻድቁ አባታችን ዘወትር በጾምና በጸሎት ተወስነው ሌሊትና ቀን እንደ ምሰሶ ቆመው ይልቁንም በሰባቱ አጽዋማት ምንም ሳይቀምሱ አጽዋማቱን ይፈጽሙ ነበር:: በፍስክ ጊዜ ግን ቅጠላ ቅጠል ይቀምሳሉ:: ከደቀመዝሙሮቻቸው አንዱ «አባታችን...እህል አትቀምስም፣ ውኃ አትጠጣም፣አይደክምህም፣ዕረፍት የለህ ሌት ከቀን ጸሎትና ቃለ እግዚአብሔር ከአንደበትህ አያቋርጥም፣ዕንባህ ከራስህ ላይ የውኃ ምንጭ እንዳለ ሁሉ ባለማቋረጥ ይፈስሳል:: የአንተ ሰውነት ከቶ ምን ዓይነት ሰውነት ነው?» ብሎ ጠየቃቸው:: አባታችንም «ልጄ ለእኔ የተደረገልኝን የእግዚአብሔር ሥራ አልሰውርህም:: እውነት እልሃለሁ ከመሬት ውስጥ ሰባት ክንድ የሚያህል ጉድጓድ ቆፍሬ ገብቼ ሱባኤ ይዤ በጸሎት በምኅላ ፈጣሪዬን ስለምነው፣ ከአለሁበት መጥቶ «ወዳጄ ሳሙኤል ሆይ ቸር አለህን?» አለኝ:: በክቡሩ እጆቹ ሰውነቴን አሻሽቶ አውራጣቱን ባጠባኝ ጊዜ ረሀብና ጥም፣ድካምና እንቅልፍ፣ ሥጋዊ ፈቃድ ሁሉ ፈጽሞ ጠፉልኝ» በማለት አስረድተውታል::

አቡነ ሳሙኤል ሃምሳ ዓመት ሙሉ በዋልድባና በደብረ ዓባይ በብህትውና በትህርምት በነበሩበት ወቅት የአባታቸውን የአቡነ መድኃኒነ እግዚእን መቃብርና በዚያው በደብረ በንኮል የሚኖሩ ባሕታውያን አረጋውያንን በየጊዜው እየሄዱ ይጐበኙ ነበር:: ከማኅበሩም በተገኙ ጊዜ ቀድሰው እንዲያቆርቡአቸው ይለምኑአቸው ነበር:: ይህም ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ዕረፍት ከአርባኛው ቀን ጀምረው ነው:: እንዲሁም ፀዓዳ ዓምባ ከአቡነ መርዓዊ ክርስቶስ ገዳም በብርሃን ሠረገላ እየሄዱ ይቀድሱ ነበር::

ጻድቁ አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ በተወለዱ በአንድ መቶ ዓመት ዕድሜያቸው፣ከዚህ ዓለም በምናኔ በምንኩስና ተለይተው፣ ግርማ ሌሊቱን፣ድምፀ አራዊቱን፣ ቁረ ሌሊቱን ዋዕየ ፀሐዩን ታግሠው፣ረሀቡን ጽምዑን ችለው፣ ዕድሜልካቸውን የተቀበሉትን ጸዋትወ መከራ አይቶ፣ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ገነት መንግሥተ ሰማያትንም ያወርሳቸው ዘንድ፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ካሉበት በቅዱሳን መላእክት ታጅቦ ነቢያትን፣ሐዋርያትን፣ ጻድቃንና ሰማዕታትን አስከትሎ መጣና ተገለጸላቸው:: በሕይወታቸው ሳሉ እንደ ሰጣቸው በዕረፍታቸው ደግሞ «ስምህን የጠራ፣መታሰቢያህንጠያደረገ፣በጸሎትህ በአማላጅነትህ ያመነ፣ በመቃብርህ በመካነ አጽምህ የተማፀነውን የአንተ ቤተሰብ ሆኖ አንተ ከገባህበት አገባዋለሁ:: ርስት መንግሥተ ሰማያትን አወርሰዋለሁ» ብሎ ቃል ኪዳን ሰጣቸው:: ንጽሕት ጽዕድት ነፍሳቸውም በእደ መላእክት በመ አዛ ገነት ከሥጋዋ ተለየች::

ቅዱሳን መላእክት «ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር» እያሉ በዝማሬ በይባቤ በዕልልታ በሕይወት ወደ ዘለዓለማዊ የዕረፍት ቦታ አስገቡዋት::

ጻድቁ አባታችን በ1295 ዓ.ም ተወልደው በ1395 ዓ.ም. ታኅሣሥ 12 ቀን ማክሰኞ ዕለት በዘጠኝ ሰዓት ዋልድባ አብረንታንት አርፈዋል:: በዚያው ከተቀበሩ በኋላ ለሰባት ዓመታት ያህል ቆይተው በደብረ ዓባይ የነበሩ መነኮሳት ልጆቻቸው አጽማቸውን መስከረም ስድስት ቀን አፍልሰው ወደ ደብረ ዓባይ ወሰዱአቸው:: በዚህ ምክንያት በየዓመቱ የጻድቁ አቡነ ሳሙኤል ታኅሣሥ 12 ቀን በዓለ ዕረፍታቸው መስከረም 6 ቀን በዓለ ፍልሰታቸው እየተባለ በደብረ ዓባይና በዋልድባ በታላቅ በሥነ ሥርዓት ይከበራል::

የአባታችን በረከትና ምልጃቸው አይለየን አሜን::

---

## ሩት

/ከገጽ 14 የዞረ/ ከሥጋ ፍሬ ይልቅ የመንፈስ ፍሬ ሰባት እጥፍ ይበልጣል:: ከችኩልነት ፍሬ ይልቅ የትዕግሥት ፍሬ ሰባት እጥፍ ይበልጣል:: ከሞዓብ ፍሬ ይልቅ የቤተልሔም ፍሬ ሰባት እጥፍ ይበልጣልና::

*መጽሐፈ ሩት ሲጠናቀቅ እንዲህ ይለናል::*

*«ቦኤዝ ኢዮቤድን ወለደ፣ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፣ እሴይም ዳዊትን ወለደ::» ሩት.4÷22:: የነገሥታት እናት ሆነች የዳዊት፣የሰሎሞን::*

*ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል አለች ሩት ከዘር ሐረግ ገብታ ተቆጠረች:: አምላክሽ አምላኬ ይሆናል አለች:: «ልጂ» ሆነ:: መጣች ባለርስት ሆነች፣ ቃርሚያ በመቃረም ጀመረች ባለጠጋውን አገባች፣ ባዶ ቤት ተቀበላት፣ ባለጸጋ ሆነች፣ በድካም ጀመረች በዕረፍት ጨረሰች፣ በመታዘዝ ጀመረች በእመቤትነት ፈጸመች:: በስደተኝነት ጀመረች በባለርስትነት ፈጸመች:: በእንግድነት ጀመረች በባለቤትነት ፈጸመች::*

*«በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ:: መዝ125÷4*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ብቸኝነት

ዲ.ያሬድ ገ/መድኅን

ባለፈው እትም ዲ.ያሬድ በዚሁ ርዕስ ሥር የቃሉን ፍቺ አስቀድሞ በማየት ብቸኝነትን የሚጠቅምና የሚጐዳ በሚል በአጭሩ ካቀረበልን በኋላ አንድን ሰው ብቸኝነትን እንዲመርጥ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ውስጥ ውጫዊ ያላቸውን አስነብቦናል:: እነዚህም ባይተዋርነት፣አስተዳደግ፣አለመተማመን፣ባሕል፣ ልማድ፣የኅብረተሰብ አመለካከት፣አደጋና ሞት ናቸው:: ዛሬ ደግሞ ውስጣዊ የሚላቸውን ምክንያቶች እንደሚከተለው ያቀርብልናል:: መልካም ንባብ

## ሀ. የበታችነት ስሜት /Inferiority Complex/

### ውስጣዊ ምክንያት

በዚህ ጽሑፍ ውስጣዊ ምክንያት ስንል አንድን ሰው ብቸኝነትን እንዲመርጥ የሚያደርጉት የግሉ ውስጣዊ ባሕርያት ወይም ምክንያቶችን ማለታችን ነው:: በርዕሳችን ሥር በርካታ ነጥቦች ሊነሱ ይችላሉ:: ዋና ዋና የምንላቸውን እንደሚከተለው እናቀርባለን::

### ለራስ የሚሰጥ አመለካከት

ብዙ ጊዜ ሰዎች ለራሳቸው የሚኖራቸው አመለካከት አለ:: ይህ አመለካከት ምናልባት ውሎ አድሮ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ሊታወቅ ቢችልም ለጊዜው በራሳቸው ብቻ ከመታወቁ በላይ እንደግል እምነት ወይም አቋም ይወስዱትና ከሰው ሊለያቸው ይችላል:: ሰዎች በራሳቸው የሚኖራቸውን አመለካከት በሁለት ክፍለን ለማየት እንችላለን::

ክርስቲያኖች በትኅትና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እንዲኖሩ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን አብነት አድርጐ አስተምሮናል:: ማቴ.3÷13–15፣11÷29፣ሉ.ቃ.22÷27፣ ዮሐ.13÷5:: አባቶቻችን አስተምረውናል:: አብርሃም ዘፍ.18÷27:: ኢዮብ 22÷29፣ ዳዊትም መዝ.21/22/÷6::

ነገር ግን ብዙ ጊዜ ብቸኛ የሚሆኑ ሰዎች ራሳቸውን ዝቅ ማድረጋቸው በዚህ ዓይነት ስሜት የሚባለው አይደለም:: የበታችነት ስሜት ራሳቸውን ለምንም ነገር ብቁ እንዳልሆኑ ከሌሎች ሰዎች የማሰብ፣የመናገር፣የመሥራት ወዘተ ችሎታ በእጅጉ ያነሡ እንደሆኑ አድርገው የሚወስዱበት ነው:: ይህም በውስጣቸው ያለው የበታችነት ስሜት ከሚፈጥርባቸው በራስ ያለመተማመን ችግር የተነሣ ሊሆን ይችላል::

አንድ ሰው የዚህ ዓይነት እምነት በውስጡ ካሳደረ ከሰዎች መራቅን ይመርጣል:: ሰዎችም ቢርቁት እንጂ ቢቀርቡት አይወድም:: ሁልጊዜ ራሱን ብቁ እንዳልሆነ አድርጎ ስለሚቆጥርም እስከ መጨረሻው በብቸኝነት ፀንቶ ቢያልፍ ይወዳል::

ለመሆኑ አንድ ሰው የዚህ ዓይነት የበታችነት ስሜት እንዲያድርበት የሚያደርጉት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የተለያዩ ነጥቦች በዚህ ዙሪያ ሊነሡ ይችላሉ::

### ውድቀት

በአንድ ወቅት ውድቀት ያጋጠመው ሰው ይህ ወድቀት እስከመጨረሻው የሚያጋጥመው እየመሰለው ራሱን ለምንም ነገር ብቁ እንዳልሆነ በመቁጠር ሲናገር በዚያውም ብቸኝነትን ሲመርጥ ይታያል:: ለዚህ ዓይነቱ ስሜት መዳበር አካባቢ እንደምክንያት ሊመደብ ይችላል:: ለምሳሌ አንድ ተማሪ በክፍል ጓደኞቹ ፊት መምህሩ የጠየቀውን ጥያቄ መመለስ ሳይችል ቢቀርና ጓደኞቹ ቢስቁበት መቼም ቢሆን ተጠይቆ መመለስ እንደማይችል አድርጐ ራሱን በመቁጠር ከጓደኞቹ ጋር እኩል ማውራት ሳይችል ይኖራል:: የዚህም መጨረሻው ጓደኞቹን መራቅ ይሆናል::

ነገር ግን መውደቅና መነሣት በሰው ልጆች ሕይወት በተደጋጋሚ የሚታይ ገጽታ ነው:: በአንድ ወቅት የወደቀ ሰው በሌላ ጊዜ ሊነሣ ይችላል:: በአንድ ወቅት ገንዘብ ያጣ ሰው በሌላ ጊዜ ሊያገኝ ይችላል:: ስለዚህ በዚህ የተነሣ ራሳቸውን የበታች አድርገው የሚቆጥሩና በዚህም ከሰዎች የተገለሉ በሆነ ወቅት ያጋጠማቸው በተደጋጋሚ በሕይወታቸው እንደማይከሰት ተገንዝበው፣ሌላው የሌለው ነገር ግን እነሱ ያላቸው ነገር እንዳለ ዐውቀው በራሳቸው በመተማመን ከሌሎች ጋር ተቀራርበው ሊኖሩ ይገባል::

### ምስጋናን መሻት

በሌላ በኩል አንዳንድ ሰው ስለሠራው ሥራ ከሌሎች እንዲነገረው የሚፈልግ አለ:: ጎረቤቶች፣ የሥራ ባልደረቦቹ፣ ጓደኞቹ ቤተሰቦቹ ካላደነቁት በየ ሰዓቱ ስሙን እያነሱ ካላመሰገኑት የማይደሰት አይጠፋም:: ይኽ ችግር ያለበት ሰዎች ምስጋና ሲያጎድሉበት ውስጣዊ ሰላም ያጣል:: ምናልባትም እርሱ አጠገብ ስለ እርሱ ታላቅነት ሳይሆን ስለሌሎች ብርታት ከተነገረ ራሱን የበታች ማድረግ ይጀምራል:: በዚህም ሰዎችን እየሸሸ ብቸኛ መሆንን ሊመርጥ ይችላል:: በመሠረቱ መንፈሳዊ ሰው ምስጋናን ከሰዎች ሊጠብቅ አይገባም:: ምስጋና ሱስ ሊሆን ስለሚችል በጊዜ መራቅ ያስፈልጋል:: ከዚህ ሌላ ሰዎች በፊቱ ስለ ጥንካሬው ሊናገሩ እንደማይችሉ መገመት ይገባል:: ጥንካሬውን ቢናገሩለት እንኳን ለጓደኞቹ ነው:: ስለ ሌሎች ለእርሱ እንደሚነግሩ ስለ እርሱ ለሌሎች ይነግራሉ እንጂ ስለእርሱ ለራሱ አይነግሩትም:: ስለዚህ ስላልተመሰገነ ብቻ ሰዎች ለእኔ ያላቸው ግምት ዝቅተኛ ነው ብሎ ራሱን ሊያዋርድ /ሊያገል/ አይገባም::

### ነቀፌታ

ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር የሚወዱት ብቻ ሳይሆኑ የሚጠሉትም ሊኖሩ እንደሚችሉ ሊረዳ ይገባዋል:: የሚወዱት /የሚያደንቁት/ ጓደኞች ያሉትን ያህል የሚጠሉት የሚነቅፉትም አይጠፉም:: የአንዳንድ ሰው ችግር ይኽንን አለ መረዳት ላይ ነው:: ምናልባት በተደጋጋሚ ጥሩ አመለካከት ያላቸው ጓደኞች ሲገጥመው ቆይቶ አንድ ቀን ችግሩን እያነሳ የሚነቅፈው ሰው ሲገጥመው ይደነግጣል:: ከቅናት፣ወሬ ከመስማት ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተነሣ ሲነቀፍ ራሱን ይጠላል:: ከዚያም ሁሉን በመፍራት ወደ ብቸኝነት ጎራ መቀላቀል ይጀምራል::

ከዚህ ዓይነቱ ችግር ለመዳን የሚደግፈው ብቻ ሳይሆን የሚነቅፈውም እንዳለ እያሰበ መኖር አለበት:: እንኳን ጉድለት የሚገኝብኝ እኔ ክርስቶስንም የሚነቅፉ ነበሩ ሊል ይገባል:: ጌታችን ባልበደለው በደል ተከስሷል:: ሐዋርያት በአይሁድ በአሕዛብ ተነቅፈዋል:: ስለዚህ መነቀፍ ያለና የሚኖር ነገር ነው:: ጌታችን በስሜ ስትነቀፉ ደስ ይበላችሁ ያለንም ክርስቲያን ሊነቀፍ እንደሚችል ሲያስረዳን ነው:: ከዚህ አንጻር መንፈሳዊ ሰው በውስጥ ካሉ ከክርስቲያን ወንድሞቹም ሆነ በውጭ ከኢአማንያን መናፍቃን የሚደርስበትን ነቀፋ መቋቋም ይገባዋል:: ይኽ ሲባል ግን ስሕተት ሰርቶ ሲነገረው ልቡን ያደንድን ማለት አይደለም:: በአግባቡ እየተጓዘ የአባቶቹን ትምህርት ተግባራዊ እያደረገ ቢነቀፍ አይረበሽ ማለት እንጂ:: ስሕተት ሰርቶም ቢነቅፉት ማረም መልካም ነው:: ከዚህ አልፎ መደናገጥ ተስፋ መቁረጥ፣ብቸኛ መሆን ግን አይገባም::

## ለ. የበላይነት ስሜት /Superiority Complex/

የበላይነት ስሜት ስንል ራስን እንደዐዋቂ መቁጠር ነው:: ሌሎችን የሚያስተምር እንጂ ከሌሎች የማይማር፣ የሌሎችን ስሕተት የሚያርም እንጂ እሱ የማይሳሳት በጥቅሉ ራስን ከሌሎች በላይና ብቁ አድርጎ መቁጠር ማለታችን ነው:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ልናያቸው እንችላለን::

እነዚህ ሰዎች በቤታቸውም ሆነ በአካባቢያቸው የእነሱን የዕውቀትም ሆነ የብስለት ደረጃ የሚመጥን እንደሌለ አድርገው ስለሚቆጥሩ ብቸኝነትን ይመርጣሉ::

ከላይ ባነሳነው ንዑስ ርዕስ እንዳየነው ሁሉ በአንድ ሰው ላይ ለዚህ ዓይነት ስሜት መዳበር የተወሰኑ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል::

### የአንድ ወቅት ድል

በአንድ ወቅት ከእሱ አልፎ ሌሎችን ያስደነቀ ድል ያገኘ ሰው ከዚያ በኋላ በየትኛውም ውድድር ተመሳሳይ ድልን እቀዳጃለሁ በሚል ራሱን ኮፍሶ ሊኖር ይችላል:: በዚህ የተነሣም በራሱ ራሱን ካስቀመጠበት ቦታ የሚደርስ

እንደሌለ አድርጐ በመቁጠር በብቸኝነት ሲባዝን ይታያል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአንድ ወቅት ውድቀት ለዘላለም ሲከሰት እንደማይኖር ሁሉ የአንድ ወቅት ድልም ጠንክረው ካልሠሩ ወደፊትም ሲከሰት ይኖራል ማለት አይቻልም፡፡ እንደእነዚህ ዓይነት ሰዎች መሥራት ባለባቸው ጊዜ ሳይሠሩ ስለሚቀሩ በሕይወታቸው ሁሉ ከችግር ያልተለዩ በተለይ በዕድሜ ዘመናቸው መጨረሻ ችግራቸው የጸና ይሆናል፡፡ ስለዚህ የዚህ ዓይነት ባሕርይ ያለባቸው ሰዎች የሕይወትን ትምህርት ቤትነት ተገንዝበው እነሱ የሌላቸው ሌሎች ሰዎች ግን ያሏቸው በርካታ ነገሮች ይኖራሉና ራሳቸውን ለሌሎች በሚመች መልኩ ተግባብተው በፍቅርና በስምምነት እየኖሩ ሊማሩ ሊያስተምሩም ይገባል፡፡ ራስን ከሌሎች ሰዎች ከፍ አድርጐ ማየት /ትዕቢት/ የሥጋ ሥራ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታዎች ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ምሳ.6፥16–17፤ ዳን.4፥30–37፤፣ማቴ.23፥12፤ሉቃ.1፥51፡፡ የሐዋ.12፥21–23፤ሮሜ.1፥30፤1ቆሮ. 8፥1፤ያዕ.4፥6፡፡

### ከንቱ ውዳሴ

ከንቱ ውዳሴ /የማይገባ ምስጋና/ ለብቸኝነት ከሚዳርጉ ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ ሰው ዕለት ዕለት የሚመሰገን ከሆነ ራሱን ከፍ ያደርጋል መታበይም ይጀምራል፡፡ የተለየ የተከበረ... እንደሆነ ስለሚነገረው ያንን ተቀብሎ ከሰው የተለየ የተከበረ እንደሆነ ያስባል፡፡ ከዚህ በኋላ አብሮት መጫወት፣መብላት፣መጠጣት፣ መሥራት የሚችል እንደሌለ በማመን ሰውን ይርቃል፡፡ የሚቀርቡትን ሁሉ ይንቅና ለራሱ የተለየ ቦታ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም የሚመስለኝ አጣሁ በማለት ብቸኛ መሆኑን ይመርጣል፡፡

እንዲህ ያለ ሰው ክርስቲያን በሚያመሰግኑት ሰዎች አንደበት እንደሚፈተን ተረድቶ ከንቱ ውዳሴን መሸሽ ይገባዋል፡፡ ሰዎች ዛሬ ያነሱትን ያህል ነገ ሊጥሉት ስለሚችሉ ለምስጋና ጆሮውን መስጠት የለበትም፡፡ በሌላ በኩል ተመስገንኩ ብሎ ራሱን ገለልተኛ ካደረገ ነገ ውድቀት ቢመጣበት የሚደርስለት የለም፡፡ በተከበረበት ወቅት የናቃቸው ሁሉ መልሰው ይንቁታል፡፡ ስለዚህ የሌለውን ክብር ቢሰጡት እንኳ በከንቱ ውዳሴ ሳይሸነፍ ምስጋናን ሳይቀበል ከሰው ሁሉ ጋር በትኅትና ሆኖ ሊኖር ይገባዋል እንዳይታበይ / ራሱን ከፍ እንዳያደርግ/ መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡

እዚህ ላይ ያለው ነጥብ ከላይ ካለው /ከአንድ ወቅት ድል/ የሚለይ እንደሆነ እንዘንጋ፡፡ ከላይ ያለው ችግር ያለበት ሰው ሊመሰገንም ላይመሰገንም ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ ድል ካደረገ በዚያ እየታበየ በትምክህት ከሰው የሚለይ ነው፡፡ ይኸኛው ግን ሠር ቶም ይሁን ሳይሠራ ሰዎች ስላመ ሰገኑት ብቻ ለራሱ የተለየ ቦታ ይሰጣል ብቸኛም ይሆናል፡፡

ከዚህ ላይ ያየነው ለራስ የሚሰጥ አመለካከት እንዴት ከሰው እንደ ሚለይ ነው፡፡ ቀጥለን ደግሞ ሌሎች ምክንያቶችን እናያለን፡፡

## ተስፋ መቁረጥ

አንድ ሰው ለያዘው ዓላማ መሳካት የተቻለውን ሁሉ ጥረት አድርጐ ሳይሳካለት ሲቀር ተስፋ ይቆርጥና ሁሉ ነገሩ ያስጠላዋል፡፡ ከሰዎች መራቅን ይፈልጋል፡፡ ይህ ዓይነት ነገር በብዛት በወጣቶች ላይ ይታያል፡፡ ሥራ ለማግኘት የሚቻለውን ሁሉ አድርጐ ማለትም በየቦታው አመልክቶ እግዚአብሔር ይህንን ሀሳቡን እንዲያሳካለትም በጸሎት ጠይቆ የፈለገውን ሥራ ሳያገኝ ሲቀር ተስ ፋው ባዶ ይሆንበትና ከሰዎች ይርቃል፡፡

ነገር ግን ክርስትና ለያዙት ዓላማ ፀንተው እስከመጨረሻው የሚታገሉበት ሕይወት እንጂ ትግሉን ጀምረው የሚያቋርጡት አይደለም፡፡ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገው ጥረት ያደረጉ ሁሉ ሲወድቁ ተጽፎ አላነበብንም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በርካታ አባቶቻችን ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ቢያጋጥማቸውም በእግዚአብሔር ታምነው ጸንተው እናገኛለን፡፡

ኢዮብ በደረሰበት ፈተና ዕናት የተነሣ የተወለደበትን ቀን ሳይቀር ቢረግምም /ኢዮ.3፥3/ እግዚአብሔር ከዚህ ችግር እንደ ሚያላቅቀው ተስፋ በማድረግ አጥብቆ ይናገር ነበር፡፡ ኢዮ.2፥10፡፡

ሦስቱ ሕፃናት «ንጉሥ ላቆመው ጣዖት አንሰግድም፡፡» በማለታቸው ከእቶን እሣት ላይ ሲጣሉ «ወይ መከራችን እሳቱ በላን» አላሉም፡፡ ይልቁንም እምነታቸውን አጠንክረው እግዚአብሔር ያድነናል እያሉ ወደ እሣቱ ተወርውረዋል፡፡ ዳን.3፥1፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተጠራለት ዓላማ ሲጓዝ የተለያዩ ችግሮች ደርሰውበታል፡፡ ነገር ግን ያን ሁሉ ሳይመለከት ተስፋ ሳይቆርጥ ዕለት ዕለት የሚያሳስበው የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ነገር ነበር፡፡ 2ቆሮ.11፥22–28፡፡ በዚህ ጽናቱም የድልን አክሊል ተቀዳጅቷል፡፡

እነዚህን አባቶች ለአብነት ማቅረባችን ከእነሱ ጽናት ትምህርት እንድናገኝ ነው፡፡ ክርስትና በሚፈጸም ተስፋ የሚኖሩት ሕይወት ነው፡፡ ተስፋ ያደረግነው ነገር እውን እንዲሆን ታዲያ ከነበረን ትጋት ሳንቀንስ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ *ያ ተስፋ ያደረግነው ነገር ዕውን እንደ ማይሆን አድርገን በመቁጠር* የነበረንን ተስፋ አሚጠን ራሳችንን ከሰዎች ማግለሉ ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደሌለው ማወቅ ይገባናል፡፡ ስለዚህ ዛሬ ያጣነው ነገ እንደሚሆንልን ተስፋ በማድረግ ከሰዎች ጋር በመግባባት እንኑር፡፡

## የሚመስለኝ አጣሁ ማለት

ይህ ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ላይ የሚታይ ችግር ነው፡፡ በአነ ጋገር፣ በአስተሳሰብ፣ በአካሄድ፣ በአመጋገብ... እንደ እነርሱ የሚሆን ይፈልጋሉ፡፡ የሚናገሩትን የሚሰማ እንደ ሚያስቡት የሚያስብ ሲያገኙም ይቀርባሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ከሆነና የሚኖሩበት ኅብረተሰብ ሊመስላቸው ካልቻለ ግን ይርቃሉ፡፡ ከዚህ ላይ በውጫዊ ምክንያትነት ካየነው ከባይተዋርነት የሚለይ ነገር አለ፡፡ ባይተዋር የሚባለው በሃይማኖት የሚመስለው፣በቋንቋ በባሕል አብሮት የሚሄድ ያጣ ነው፡፡ በዚህ ርዕስ ሥር የምናየው ግን በሃይማኖት ከሚመስሉት ጋር አብሮ እየኖረ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚለየው ግን በጠባይ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰንበት ት/ቤት ቀይሮ አካባቢ ለቆ ወደ ሌላ ሥፍራ ሲሄድ፡፡ ቤተክርስቲያን ካሉ መንፈሳዊ ወንድም እኅቶች አይግባባም፡፡ መንፈሳዊነታቸውን... ቢመለከትም ጠባያችን አልገጠመም በሚል ፈሊጥ ይርቃቸዋል፡፡ በጉባኤ ከመማር ከማስቀደስ ውጭ መቅረብ ማነጋገር አይፈልግም፡፡ ራሱን ከአካባቢው ጋር ማመሳሰል ስለማይችል ገለልተኛ ይሆናል፡፡

እዚህ ላይ በእርግጥ በብቸኝነቱ /በመራቁ/ ካልተረበሸበት ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን ጠባያቸው ከጠባዩ ስላልገጠመ የሚጨነቅ ከሆነ ራሱን በተቻለ መጠን ለማመሳሰል ቢሞክር መልካም ነው፡፡ ሳቅ በይወድም ለመሳቅ፣ ለመናገር ባይፈልግም በተወሰነ ደረጃ ለመነጋገር...ቢጥር መልካም ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው» እንዳለ ራሳችንን እግዚአብሔርን መምሰል /ሁሉን መቻል ከሁሉ ጋር መኖርን ልናስለምደው ይገባናል፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ ብቸኝነት ሲባል «ስለስሜ ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ እጥፍ ይቀበላል፤ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል፡፡» ማቴ. 19፥29፡፡ የተባለውን አምላካዊ ትእዛዝ ሰምቶ ራስን ከሰው አርቆ በብሕትውና የሚኖረውን ሕይወት አያጠቃልልም፡፡ በዓለም አብርሃም እየተኖረ ከሰዎች ጋር ተገናኝቶ በፍቅር በስምምነት መኖር ሲቻል ራስን ከሰው አግልሎ የሚኖር ሰው የሚጐዳው ራሱን ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ዐቢይ ርዕስ ዙሪያ ሊነሡ የሚገባቸው ሁሉ ተነሥተዋል ማለት አያስደፍርም፡፡ የሆነው ሆኖ በተወሰነ ደረጃ ጥቂት ነጥቦችን ለመነካካት ሞክረናል፡፡ ከምንም በላይ እንደእዚህ ዓይነት ችግሮች ያለባቸው ሰዎች የተለያዩ መፍትሔዎች መጠቀም ይችላሉና አባቶችን ማማከር ይገባል፡፡ እራሳችንን ከብቸኝነት አርቀን ከሰዎች ጋር እንድንኖር አምላከ ቅዱሳን ይርዳን፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# የወጣቱ አስተዋጽኦ በቤተክርስቲያን

ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ
በአ/አ/ተ/ቢ/ ሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ኃላፊ

/የመጨረሻ ክፍል/

አባታችን ዛሬም ከእኛ ጋር ናቸው:: ሦስተኛው ክፍል በሆነው በዚህ ጽሑፋቸው የወጣቱ አገልግሎት ለማን? የወጣቱ አገልግሎት በምን? የወጣቱ አስተዋጽኦ በቤተክርስቲያን እንዴት? በሚሉት ዐበይት አርእስት ዙሪያ ያተኩራሉ፣ በደብዳቤ፣በስልክና በአካል እየተገኛችሁ የጽሑፉን ጠቃሚነት የገለጻችሁልንን እያመሰገንን የመጨረሻውን ክፍል እናቀርባለን:: ባለፉት ሁለት እትሞቻችን ለተከሰቱት አንዳንድ ግድፈቶች ተጠያቂው ዝግጅት ክፍሉ በመሆኑ፣ አባታችንንም ሆነ አንባብያንን ይቅርታ እንጠይቃለን:: መልካም ንባብ::

## ሀ/ የወጣቱ አገልግሎት ለማን?

በጉብዝናው ወራት ፈጣሪውን የማሰብና የማገልገል ኃላፊነት ያለበት ወጣት፣አገልግሎቱ ሰፊና ውስብስብ እንደሆነ አከራካሪ አይሆንም:: አገልግሎት የሚለው ቃል ሲነሣ፣የቃሉን ትርጉም በአግባቡ ለማወቅ፣ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል:: ይኸውም አገልግሎት ሲባል አገልጋይንና ተገልጋይን ያማከለ ማኅበራዊ ገጽታ ያለው ሆኖ ይገኛል:: ታዲያ እዚህ ላይ «የወጣቱ አገልግሎት ለማን?» ሲባል፣ወጣቱ ማንን ማገልገል አለበት? የሚል ጽንሰ ሐሳብ ይዞ የተነሣ ጥያቄ መሆኑን እንረዳለን:: ለጥያቄው ያለን ግንዛቤ ይኸው ከሆነ ደግሞ፣አገልግሎትን ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ በሚል መስመር ለይተን ስንመለከት የአገልግሎትን ትክክለኛ ትርጉም በውል ለመረዳት ያስችለናል:: የሐዋ.6÷1–6::

እዚህ ላይ፣መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለይተን ማወቅ አለብን ስንል ማኅበራዊ አገልግሎት መንፈሳዊ አይሆንም መንፈሳዊ አገልግሎትም ማኅበራዊ ሊሆን አይችልም ለማለት አይደለም፣ ነገር ግን ማኅበራዊ አገል ግሎት አብዛኛውን ጊዜ በሥጋዊ መግቦት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ብቻ ነው::

በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ዘርፍ ያለውን የአገልግሎት ልዩነት ከተገነዘብን ደግሞ፣በአገልግሎቱ ውጤት ላይ ያተኮረ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል:: ሁላችንም በግልጽ እንደምናውቀው በአገልጋይና በተገልጋይ መካከል፣ይብዛም ይነስ ሁለቱን ወገኖች የሚያማክል፣በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ውጤት አለ:: ይኸውም፣ ተገልጋዩን የተገልጋይነት ውጤት ተጠቃሚ፣ አገልጋዩንም የአገልጋይነት ውጤት ተጠቃሚ የሚያደርግ የተሰናሰለ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል ማለት ነው:: ይህ ከሌለ በማኅበራዊ ዘርፍ ሊኖር የሚችል አገልግሎት ትርጉም አልባ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን::

ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት ስንመለስ ግን፣ውጤቱ ከማኅበራዊ አገልግሎት ውጤት የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን:: እንዲህ ሲባልም እንዴት ማለቱ አስፈላጊ ይሆናል፣ የዚህን ልዩነት ማየት የምንችለው፣በፍጡርና በፈጣሪ መካከል ያለውን የአገልግሎት ግንኙነትና ውጤቱን በማስተዋል ማጥናት ስንችል ነው::

በመሠረቱ ፍጡር ፈጣሪን በማገልገሉ የአገልግሎት ውጤት እንደማኅበራዊ አገልግሎት ለሁለቱ ተከፍሎ የታሰበ ተገልጋይንና አገልጋይን ሊያማክል በሚችል በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ውጤት ሆኖ አናየውም፣ውጤቱ ለሁለቱ የሚከፈል አይደለም፣ ይልቁንም አንዱን ብቻ ያውም አገልጋዩን ወገን ብቻ ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል አስደናቂ አስገራሚ ውጤት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን:: ምክንያቱም የምናገለግለው እግዚአብሔር፣ከአገልጋዩ ወይም ከፍጡሩ የሚያስፈልገው ወይም ይጠቅመኛል ብሎ የሚጠብቀው አንድም ነገር ስለማይኖር፣ ተገልጋይ እግዚአብሔር ከአገልጋዩ በሚገኝ ውጤት የመጠቀም ባሕርይ ፈጽሞ የለውም:: በማንኛውም መንፈሳዊ ዘርፍ የሚገኝ የአገልግሎት ውጤት ሁሉ ጥቅሙ ለዚያው ለአገልጋዩ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: በዚህም የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እንረዳለን::

ይህን አባባል ለማረጋገጥም «ወረከብኩ ውስቴታ ዘይብል ዘንተ ቅዳሴ ዘይቄድስ ካህን አኮ ማርያምሃ ዘይቄድስ፣ አላ ውእቱ ይትቄደስ ወእለ ሰምዕዎ ኵሎሙ ይትቄደሱ:: እስመ እግዝእትነሰ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወትረ በሰማይ ወበምድር:: ፣ይህን ቅዳሴ የሚቀድስ ካህን፣እመቤታችንን የሚቀድስ /የሚያከብር/ አይደለም፣እሱ ይቀደሳል ይከብራል እንጂ:: የሰሙትም ሁሉ ይከብራሉ እንጂ እመቤታችንስ በሰማይ በምድር፣በመላእክት በደቂቀ አዳም ዘንድ ሁል ጊዜ የከበረች ናት::» የሚለውን አብነት በምሳሌነት መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል:: /ቅዳ .ማር የመጨረሻው ክፍል/::

እንግዲህ የመንፈሳዊ አገልግሎት ውጤቱ፣ አገልጋዩን ወገን ማክበር ነው፣ በሚል መሠረታዊ ሐሳብ ከተስማማን፣ የወጣቱ አገልግሎት ለማን? ለሚለው ጥያቄም መልሱ፣ አገልግሎት ማግኘት በሚገባቸው ወገኖችና ለአገልግሎት መስጫ ዘርፎች በኩል፣ለራሱ የሚል እንደሚሆን እንገነዘባለን::

## ለ/ የወጣቱ አገልግሎት በምን?

የወጣቱ አገልግሎት በዚህ ሊሆን ይገባል ብሎ ውሱን መስመር መተለም ከባድ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም በተለይ ወጣቱ ዘርፈ ብዙ የሆነ አገልግሎት ሊፈጽም የሚችል ኃይል ቢሆንም ማንም ሰው እግዚአብሔር እንደሰጠው የጸጋ ስጦታ ማገልገል ያለበት በመሆኑ ነው:: 1ኛ ቆሮ.12÷4–11::

የሆነው ሆኖ የማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት ምንጩና መሠረቱ፣ የወንጌል አገልግሎት በመሆኑ፣የወንጌል አገልግሎትን አስመልክቶ በትንሹ ለማለት እንሞክር::

የወንጌል አገልግሎት ከጥንት ጀምሮ መንፈስ እግዚአብሔር ባልተለያቸው አበው ጥረት እየተስፋፋ፣ ምእመናን መፍቅደ ነፍስና መፍቀደ ሥጋ ተሟልቶላቸው የመገኘቱ ምሥጢር የአበውን የእምነት ጽናትና መንፈስ ጠንካራነት አጉልቶ ማሳየት የሚችል የታሪክ ሂደት ነው:: ይሁን እንጂ ዘመናችንን ስንመለከተው ደግሞ፣ ሥጋዊ ጥበብ የነገሠበት፣ቴክኖሎጂ የመጠቀበት፣የሰው ልጅ ከምድር በላይ ባሉ በሚሉአቸው ፕላኔቶች ላይ ለመሰልጠን ያልተቋረጠ የምርምር ተግባር የሚያከናውንበት ዘመን በመሆኑ የስብከተ ወንጌል አገልግሎታችንም ያንኑ ያህል፣የረቀቀ፣የመጠቀ፣የነጠረና የቀለጠፈ ይሆን ዘንድ ዘመኑ የሚጠይቀው እውነታ እንደሆነ አከራካሪ ሆኖ አይታይም:: ለዚህም የወጣቱ አገልግሎት፣ ምቹና ተስማሚ ይሆናል:: ጥራትና ብቃት ያለው፣የተሟላና የተቀላጠፈ የወንጌል አገልግሎት መኖር አለበት ሲባል ግን፣ የቅዱሳን መጻሕፍትን ምሥጢር ሳያዛቡ፣ትርጉማቸውንም ሳያፋልሱ በጥንቃቄ የሚከናወን አገልግሎት ይኑር ማለት እንጂ ዓለም ሰለጠነ በመባሉ ብቻ፣ መናፍቃን እንደሚያደርጉት መጻሕፍትን በልብ ወለድነት ለግል ፍላጎት እያጣመሙ በመናገርና ቃለመጻሕፍትን በመለወጥ አገልግሎቱ ቢከናወን ግድ የለም ማለት አይደለም:: «ወዘንተ ባሕቱ ቅድሙ አእምሮ ከመ ኵሉ ተነብዮ ዘውስተ መጽሐፍ አልቦ ላዕሌሁ ፍካሬሁ::...ግን በመጽሐፍ ያለ ትንቢት ሁሉ ትርጓሜው በላዩ እንደሌለ አስቀድማችሁ እወቁ:: ትንቢት በሰው ፈቃድ በሰውም ፍላጎት ከቶ አይሆንም፣ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩ እንጂ፣ከእግዚአብሔር ተልከው::» /2ኛ.ጴጥ.1÷20–21/:: «ወእለሰ አልቦሙ ትምህርት እለ ኢለበዉ ይመ ይጥዎ ለቃለ መጽሐፍ ከመ ሜጥዎን ለብዙኃት መጻሕፍት ለግዕዞሙ ወያማስኑ:: ያልተማሩ፣ የማያስተውሉ ግን የመጽሐፍን ቃል ይለውጣሉ፤ ብዙ ዎችን መጻሕፍት ወደ ክሕደታቸው እንደለወጡአቸው ያጠፉሉ» /2ኛ. ጴጥ. 3÷16/ ተብሎ የተጻፈውን

በጥንቃቄ በመመልከት ነው:: ብቁ የወንጌል አገልጋይ ለመሆን ግን የሚከተሉትን፣ መርሆች ተቀዳሚ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል:: እነዚህም፣

## 1. የወንጌልን መሠረተ ሐሳብ ጠንቅቆ ማወቅ

ወንጌል የሚለው ቃል ጥንተ ቃሉ ጽርዕ ሆኖ፣ «ዜና ሠናይ» ብሥራት የሚል ትርጉም እንዳለው ይታወቃል:: ወንጌል ማለት ስብከት ማለት መሆኑም ተገልጿል:: ወንጌል፣እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለድኅነተ ዓለም እንዳሰበ፣ዓለምም በኢየሱስ ክርስቶስ እንደዳነ የምታበሥር፣ ወልደ እግዚአብሔር ነገሠ፣ዲያብሎስ ተሻረ፣ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ጠፋ ብላ የምታውጅ፣ የእግዚአብሔርን ጌትነቱን፣ አዳኝነቱን የምታስተምር ዓለም በክርስቶስ ደም መዋጀቱን፣ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ መሆኑን የምታበሥር በመሆንዋ ብሥራት ተብላለች:: «እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልደ ዋሕደ መጠወ ወወሀበ ቤዛ ኩሉ:: አንድ ልጁን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ እስከ መስጠት ደርሶ እግዚአብሔር ዓለሙን ወዶታልና::» ተብሎ እንደተጻፈ:: ዮሐ. 3÷ 16:: ግብ.ሐዋ.20÷28::

ወንጌል፣ ሰላም በመሆንዋ አምላከ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስን ትሰብካለች፣ «ንሕነሰ ንሰብከ ክርስቶስሃ ዘተሰቅለ፡ እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን» 1ኛቆሮ.1÷23:: መጻሕፍተ ሐዲሳት ወንጌልን፣

- ወንጌለ እግዚአብሔር /ሮሜ.1÷1:: 1ኛ ተሰ.2÷9:: /
- ወንጌለ ክርስቶስ /ማር 1÷1፣ሮሜ 1÷16፣16÷19፣1ኛ ቆሮ. 9÷12፣ ገላ.1÷7::/
- ወንጌለ ሰላም /ኤፌ.6÷15/
- ቃለ ጽድቅ፡ ትምህርተ ሕይወት /ኤፌ.1÷13/::
- ስብሐተ ክርስቶስ:: /2ኛ ቆሮ. 4÷4/ ::
- ወንጌለ መንግሥት /ማቴ.4÷23፣ ም.24÷14/::
- ቃለ እግዚአብሔር /ግብ.ሐዋ. 8÷25/ በሚል ስያሜ ይገልጹአታል::

ስለሆነም የወንጌል አገልጋይ፣ሐዋርያ፣ካህን፣ኖላዊ የሚል ክብር የተሰጠው ሰው፣ የወንጌልን መሠረተ ሐሳብ በሚገባ ሲያውቅ በቂ አገልግሎት ማበርከት ይችላል::

ለትምህርተ ወንጌል መስፋፋት ወሳኙ ኃይል፣ኃይለ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይታወቃል:: ስለሆነም ኃይለ እግዚአብሔር በሰባኪው ላይ አድሮ ሥራውን እንዲሠራ ፈቃደ እግ ዚአብሔርን መጠየቅ ከአንድ መምህረ ወንጌል የሚፈለግ ዐቢይና ቀዳሚ ተግባር ነው::

## 2 ጸሎት

ሀ. «ወይእዜኒ አኀዊነ ጸልዩ ለነ ከመ ይሩጽ ቃለ እግዚአብሔር ወይሰባሕ በከመ በኀቤክሙ:: አሁንም ወንድሞቻችን ጸልዩልን የእግዚአብሔር ቃል እንዲፋጠንና እንዲገለጥ በእናንተ ዘንድ እንደ ሆነው» 2ኛ.ተሰ.3÷1::

ለ «ጸልዩ ወሰአሉ ለነኒ ከመ ያርኁ ለነ እግዚአብሔር አናቅጸ ቃል ከመ ንግር ምክረ ዘእምኀበ እግዚአብሔር:: ስለ እኛ ጸልዩ፣ማልዱልን፣እግዚአብሔር የቃሉን በር ይከፍትልን ዘንድ::» ቆላ. 4÷3

ሐ. «ትግሁ ወተጸመዱ ለጸሎት ኵሎ ጊዜ በእንተ ኵሎሙ ቅዱሳን ወበእንቲአየ ከመየሀበኒ ቃለ ወይከስት አፉየ ከመ እንግር ገሃደ ሕርመተ ትምህርት:: ስለቅዱሳን ሁሉም አዘውትራችሁ ለመጸለይ ጽሙዳን ሁኑ:: ለእኔም ጸልዩልኝ ቃልን እንዲሰጠኝ ወንጌልንም ገልጬ እንድናገር አንደበቴን ይከፍትልኝ ዘንድ::» ኤፌ.6÷18–19::

## 3 መልካም ሥነ ምግባር

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ላይ እንዲገኝ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ይታመንበታል:: ይልቁንም፣ለዚሁ አብነት መሪና ፊታውራሪ ሆኖ መገኘት ያለበት መምህረ ወንጌል ነው:: አንድ ሐዋርያ ወይም አንድ ካህን ወይም የወንጌል አገልጋይ አርአያነቱ ምን ያህል ለመሃይምናን ጠቃሚ እንደሚሆን ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙሩን ጢሞቴዎስን ሲመክር እንዲህ ብሎአል::

«ከመዝ መሀር ወገሥጽ፣ ወአልቦ ዘያስተአብድ ለውርዙትከ፣ ወኩኖሙ አርአያ ወአምሳለ ለመሃይምናን በቃልከ፣ ወበምግባሪከ፣በፍቅር ወበሃይማኖት ወበንጽህ:: እንዲህ ምከር፤ አስተምር፤ ሕፃንነትህን የሚንቃት አይ ኑር፤ በቃልህም በሥራህም ለመሃይምናን አርአያና ምሳሌ ሁናቸው:: በፍቅር በሃይማኖት በንጽሕናም:: ...ዘንተ አንብብ ወበዝ ሀሉ ከመ ይትዐወቅ ስላጤከ በኵለሄ:: ይህን አንብብ በዚህም ጸንተህ ኑር፣ፍጹምነትህ በሁሉ ይታወቅ ዘንድ:: ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰማህንም ታድናለህ::» /1ኛ.ጢሞ.4÷11–16:: /

የወንጌል ዓላማዋና አገልግሎትዋ፣ሰውን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ፣ ጨለማው ዓለም በብርሃን እንዲመላለስ፣ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ሆኖ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽነቱን እንዲያረጋግጥ ማድረግ ነው:: አልጫው ዓለም በቃለ ወንጌል ጣፍጦ ጣዕም እንዲኖረው ማድረግ የሚቻለውም፣የጨለማው ዓለም ብርሃኑ የሚበራ፣ልስሑን ዓለም ለማጣፈጥ የተሰጠውን ሰማያዊ ጸጋ በአግባቡ መጠቀም የሚችል ሐዋርያ ሲኖር ነው::

የሰባኪውና የተሰባኪው የዓላማ አንድነት፣መግባባትና መተማመን የወንጌልን አገልግሎት የሰመረ ያደርገዋል:: የመምህረ ወንጌሉ መንገድ ቀና ከሆነ፣ ምእመናንም ከተንኮል፣ከቂም ከበቀልና ከክፉ ነገር ሁሉ ርቀው ወደ እግዚአብሔር በምታደርሳቸው ጎዳና ለመጓዝ ይበቃሉ:: በጠባቂውና በመንጋው መካከል መግባባት ፣ መደማመጥና መተማመን ካለ ሐዋርያው፣«ንስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት» ሲል፣ምእመናንም ምንተ ንግበር» ይላሉ:: መምህረ ወንጌሉ ፣ «ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሠናየ ዘይደልወክሙ ለንስሐ ወትነሥኡ ጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱስ፣ ሲል ሕዝበ ክርስቲያኑም ልባቸው ይከፈታል:: እነሆ፣እሺ በጀ የሚለውን ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያደርጋሉ:: አንደበታቸው ለጸሎት እጃቸው ለምጽዋት የተዘጋጀ ይሆናል:: እንዲህ ሲሆንም የወንጌል አገልግሎት የሠመረ መሆንን ማረጋገጥ ይቻላል:: ግብ.ሐዋ 2÷37– 40፣3÷19::

## 4 በወንጌል አገልግሎት አለማፈር

በማንኛውም ሥራ ውጤት ማስገኘት የሚቻለው አምነውበት ሲሠሩ ነው:: ይልቁንም ትምህርተ ወንጌል፡ ፍጹም የሆነ መጥዎተ ርእስን ይጠይቃል፡ ከዚህም ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን ያስተምረናል::

ሀ. «እስመ ኢየኀፍር ምህሮ ወንጌሉ እስመ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ውእቱ ዘየሐይዎሙ ለኵሎሙ ለእለ የአምኑ ቦቱ:: ወንጌልን ማስተማሩን አላፍርምና የእግዚአብሔር ኃይሉ ስለሆነ ያመኑበትን ሁሉ የሚያድናቸው::» ሮሜ. 1÷16::

ለ «እስመ አኮ መንፈሰ ፍርሐት ዘወሀበነ እግዚአብሔር ዘእንበለ መንፈሰ ኃይል ወንጽሕ ወተፋቅሮ ወጥበብ:: እግዚአብሔር የፍርሐት መንፈስን የሰጠን አይደለምና የኃይል፣የንጽሕና የፍቅር የጥበብ መንፈስን እንጂ:: እንግዲህ ለጌታችን ስለመመስከር አትፈር፤ እኔንም እስረኛውን አታሳፍረኝ፡ በእግዚአብሔር ኃይል ለማስተማር ድከም እንጂ::» 2ኛ.ጢሞ. 1÷7–8::

## 5ኛ የሰማዕያንን አቅም መመጠን

የማስተማር ዘዴ፣ልዩ ሥልጠና የሚያስፈልገው፣ጥልቀትና ምጥቀት ያለው ሙያ እንደሆነ ይታመንበታል:: በዚህ ሙያ የሚመደቡ መምህራንም የሥነ ልቡና ጠበብት በመባል ይታወቃሉ:: ሙያቸውን በተግባር ለመተርጐም የሚጠበቅባቸው ጥረት ልዩ ነው:: ትምህርታቸውን ከሰው ኅሊና ለመቅረፅ የእያንዳንዱን ሰው ማንነት ፍላጐትና አቅም ይለካሉ:: ሰውን ወደ ትምህርታቸው የሚስቡት እነሱ በሚፈልጉት ብቻ ሳይሆን ሰውን በመምሰል ነው:: ይህንኑ ብልሃት ቅዱስ ጳውሎስ ሲጠቀምበት እንመለከታለን::

«ወከመ ዘለሕፃናት በሃይማኖተ ክርስቶስ ሐሊበ ወጋእኩክሙ፣ወአኮ መብልዐ ጽኑዐ ዘአብላዕኩክሙ፣እስመ አዲ ክሙ ኢጸናዕክሙ ወበሕግ ዘሥጋ ወደም ሀለውክሙ:: ክርስቶስን በማመን ሕፃናት እንደመሆናችሁ፣ ወተት ጋትኳችሁ፡ ጽኑ መብልም ያበ ላሁአችሁ አይደለም፡ ገና አልጠነከራችሁምና፡ በሥጋዊ በደማዊ ሥርዓትም ትኖራችሁና::» 1ኛ ቆሮ. 3÷2:: «እስመ ኵሉ ዘይትወጋእ ሐሊ

በ ሕፃን ውእቱ፣ኢያሐሥሥ፣ያእምር ቃለ ጽድቅ:: ወመብልዕሰ ጽኑዕ ለልሂቅ ውእቱ ዘይለምድ ተኀሥሦ በዘይፈልጥ ሠናየ ወእኩየ:: ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ነውና፤ እውነተኛውንም ነገር ሊያውቅ አይሻም:: ጽኑ ምግብስ ለትልቅ ሰው ነው፣ምርምርን ለሚለማመድ፣ክፉውንም መልካሙን ሊለይ» ዕብ.5÷13–14:: ከዚህ አባባል የሰዎች ባልተመጣጠነ የዕውቀት ደረጃ ላይ መገኘትን ተገንዝበን፣ ምሥጢራትን በማራቀቅ የግል ችሎታችንን ለመግለጽ ሰማዕያኑን በሚያደክም መራቀቅ ጊዜን ከማጥፋት ይልቅ፣ ትምህርታችን ለሁሉም ቀላልና ግልጽ ሆኖ መቅረብ ያለበት መሆኑን እንማራለን:: እንደዚህ ማለት ግን ሁሉም ሰማዕያን ጥልቀት ያለው ትምህርት አያሻቸውም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል::

## 6 የሚገባ ተግሣጽ

ብዙ ሰዎች ተግሣጽ አስፈላጊ አይደለም የሚል አመለካከት አላቸው:: ነገር ግን ተግሣጽና ምስጋና ጊዜያቸውንና ቦታቸውን ጠብቀው ሲነገሩ እኩል አገልግሎት አላቸው፤ ምስጋና አለቦታው ገብቶ ሲነገር የሚጐዳውን ያህል ተግሣጽም አለቦታውና አለጊዜው ሲነገር ይጐዳል:: ምስጋና በሚገባ ሲነገር የሚጠቅመውን ያህል ተግሣፅም በአግባቡ ሲነገር ጥቅሙ በእጅጉ የጐላ ይሆናል:: በመሆኑም መጻሕፍት በአግባቡ ተጠቅመውበታል::

«ወለእለሂ ስሕቱ፣በቅድመ ኵሉ ገሥጸሙ ከመ ባዕድኒ ይፍራሕ:: የተሳሳቱትንም በሰው ሁሉ ፊት ገሥጻቸው:: ሌላውም ይፈራ ዘንድ::» 1ኛጢሞ.5÷20፣4÷11፣5÷7::

«አ አብዳን ሰብአ ገላትያ መኑ አሕመመክሙ ከመ ኢትእመኑ በጽድቅ ዘያስተርኢ «...እናንተ የገላትያ ሰዎች በዐይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?» ገላ 3÷1::

«...አ ትውልደ አራዊተ ምድር መኑ እመረክሙ ትጐየዩ እመቅሠፍት፣ እምመንሱት ወእመዓት ዘይመፅእ፣ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሠናየ ዘይደልወክሙ ለንስሐ:: ...እናንተ የእፉኝት /የእባብ/ ልጆች፣ከሚመጣው ቁጣ፣ ጥፋትና መቅሠፍት ትሸሹ ዘንድ ማን አመለከታችሁ? እንኪያስ ለንስሐ የሚያበቃችሁን በጎ ሥራ ሥሩ::»ማቴ.3÷7–12:: ምሳሌ.23÷32::

«አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን:: ጻፎችና ፈሪሳውያን... ወዮላችሁ» ማቴ.23÷13–32::

« ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጽ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበ ተወክሎ መጻሕፍት ንረከብ ተስፋነ፤» የተጻፈው ኹሉ ልንመከርበት ተጻፈ፤ በመታገሳችን ተስፋችንን እናገኝ ዘንድ፤» ሮሜ 15÷4፣ 2ኛጢሞ. 3÷16–17::

## 7ኛ ምእመናንን ማበረታታት

ምእመናን በሃይማኖት የጸኑ፣በምግባር የቀኑ ይሆኑ ዘንድ በሞራል ሊገነቡ ይገባል:: እንደዚህ ሲባል ግን ከላይ እንደተጠቀሰው በእውነት ላይ የተመሠረተ ምስጋና፣ሞራላቸውን ይገነባል ለማለት እንጂ ባልሠሩት ይመስገኑ ማለት አይሆንም:: የማይገባ ምስጋና ስድብ ነው:: የሚገባ ምስጋና ግን ትልቅ ሽልማት ነው:: ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ ተጠቅሞበታል::

«ርቱዕ ነአኵቶ ለእግዚአብሔር በኵሉ ጊዜ በእንቲአክሙ አኀዊነ በከመ ይደልዎ፣ እስመ ዓብየት ሃይማኖትክሙ ወፈድፈደት ተፈቅሮትክሙ ምስለ ኵሉ ቢጽክሙ ከመንሕነሂ ንትመካሕ በክሙ በቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር በእንተ ሃይማኖትክሙ ወትዕግሥትክሙ በሕማምክሙ ወምንዳቤክሙ ዘትትዔገሡ:: ወንድሞቻችን ስለ እናንተ ዘወትር እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል:: እንደሚገባው ሃይማኖታችሁ ስፍታለችና፤ ከባልንጀራችሁ ሁሉ ጋር ፍቅራችሁም በዝታለች:: እኛም በእናንተ እንመካ ዘንድ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሃይማኖታችሁ፣ስለ ትዕግሥታችሁ፣ ታግሣችሁ በምትቀበሉት መከራ::» 2ኛ ተሰ.1÷3–4::

«ወንድሞቻችን እኛስ ዘወትር እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል፤ እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ ስለ እናንተ የሕይወት ባለቤት እግዚአብሔር ይቅር ብሎ መርጦአችኋልና፤ በመንፈስ በመቀደስና በእውነተኛ ሃይማኖት፤» 2ኛ ተሰ. 13÷17::

«መኑ ተስፋነ ወፍሥሐነ ወአክሊለ ምክሕነ አኮኑ አንትሙ በቅድመ እግዚአነ ኢየሱስ ክርስቶስ በምጽአቱ:: እስመ አንትሙ ክብርነ ወፍሥሐነ:: አለኝታችን ማነው? ደስታችንስ? የመመኪያችን ዘውድስ እናንተ አይደላችሁምን? በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በሚመጣበት ጊዜ፣ክብራችን ደስታችን እናንተ ናችሁና» 1ኛተሰ.2÷19–20::

## 8 <u>ተአማኒነት</u>

የማንኛውም አስተማሪ ዓላማ በሚያስተምረው ትምህርት ሌላውን ለመጥቀም ነው፤ ተቀባዩ ክፍል የበለጠ የሚማረውም ከቃል ይልቅ ተግባርን ነው፤ ከአስተማሪው እውቀት ይልቅ ተግባሩንና አርአያነቱን ይመርጣል፤ አያውቅም ተብሎ እንዲያውቅ የሚሰበሰበው ክፍል የራሱ የሆነ መለኪያና መስፈርት ስላለው ለአስተማሪው ያልተጠበቀ ግምት ይሰጣል፤ መስሎ መታየት የምንደኝነት ተግባር በመሆኑ ለጊዜው የጠቀመ ይምሰል እንጂ ጉጂነቱ አያጠያይቅም፤ የሚያምኑበትን ማስተማር፣በሚያስተምሩት አለማፈር እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ መስሎ ከመታየት መራቅ አስፈላጊ ነው:: ማቴ.23÷1–5፣ሮሜ2÷17–24::

መታመን ወይም ተአማኒነት ማለትም ከሁሉ በፊት ራስን መስበክ፣ራስን ማስተማር ራስን ማሸነፍ መቻል ማለት ነው:: ራሱን አስቀድሞ ያልሰበከ ሰባኪ ራሱን አስቀድሞ ያላስተማረ አስተማሪ ሌላውን ያንጻል ብሎ ማሰብ ከቶውኑ የሚቻል አይሆንም::

## 9 ፈሪሐ እግዚአብሔር

ፈሪሐ እግዚአብሔር የጥበብ ሁሉ መጀመሪያና ፍጻሜ ነው:: የዕውቀትም ሁሉ መሠረት ነው:: ምሳ. 1÷73፣መዝ110÷10::

በፈሪሐ እግዚአብሔር ያልተመሠረተ ጥበብ ፈራሽ ነው:: ፈሪሐ እግዚአብሔርን መነሻ ያላደረገ ጥበብ መድረሻው አይታወቅም:: በፈሪሐ እግዚአብሔር ያልታነፀ ልቡና ለማንም ለምንም አይበጅም:: በመሆኑም የምእመናንን ልቡና በፈሪሐ እግዚአብሔር ማነጽ ይቻል ዘንድ የወንጌል አገልግሎት በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ፣ የመጀመሪያውም የመ ጨረሻውም መንገድ ሊሆን ይገባል::

## የወጣቱ አስተዋጽኦ ለቤተክርስቲያን፤ እንዴት?

አስተዋጽኦ ማለት ወይም የአስተዋጽኦ ጽንሰ ሐሳብ፣የጐደለን ለመሙላት፣ያነሰን ለማብዛት፣የተቸገረን ለመርዳት፣ወይም ወገንነትንና ወዳጅነትን ለመግለጽ ከአንደኛው ወገን ለሁለተኛው የሚለገስ ሥጦታና ችሮታ ማለት እንደሆነ እንገነዘባለን::

ሆኖም አንድ ሰው የሕይወት ገጠመኙን ለማቆየት /ለመጠበቅ/ በሚያደርገው ጥረትና ውጣ ውረድ የሚያገኘው ውጤት ግን አስተዋጽኦ ከሚባል ይልቅ «የራስ ለራስ አገልግሎት» መባሉ የተመቸ ይሆናል::

እንግዲህ የአስተዋጽኦን መሠረተ ሐሳብ በዚህ መልኩ ካየነው፤ የወጣቱ አስተዋጽኦ ለቤተክርቲያን ስንል፣ ወጣቱን ከባለቤትነት ውጪ አድርገን አስተዋጽኦ አበርካች አድርገን መመልከቱ በመንፈሳዊ ረገድ ሊያመለክተን የሚችለውን የአስተዋጽኦን መን ፈሳዊ ትርጉምና ገጽታ የሚለውጥብን ይሆናል::

ስለሆነም ወጣቱ ለቤተክርስቲያን የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ራሱን ከማገልገል አኳያ የሚፈጸም መንፈሳዊ ጉዞ መሆኑን በመረዳት እንደ ቅዱስ ሉቃስ ሀብተ ጥበብ የተሰጠው በጥበቡና በመድኃኒቱ /ቆላ.4÷14/ እንደ ዜማስ ሕግን የማወቅ ጸጋ የተሰጠው በሕግ ሙያው፣ /ቲቶ.3÷13::/ ሀብተ ክህነት የተሰጠው በክህነቱ ፣የማስተማር ጸጋ የተሰጠው በማስተማሩ፣ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣በአጠቃላይ ሁሉም በተሰጠው የጸጋ ስጦታ መጠን ቤተክርስቲያኑን ሊያገለግል ይገባል:: 1ኛ ቆሮ.12÷14–31::

«እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቀን»

# ገዳማዊ ሕይወት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

/መርሻ አለኸኝ/

የገዳም ሕይወት ከሀብት፣
ከን ብረትና ከቤተሰብ ተለይቶ ፀብአ
አጋ ንንትን ግርማ ሌሊትን ሳይፈሩ
ራስን በገዳም ወስኖ ከእግዚአብሔር
ጋር እየተገናኙ የሚኖሩበት ሕይወት
ነው::

ሥርዓተ ምንኩስና የተጀመረው
የአዳም ሰባተኛ ትውልድ በሆነ
በሄኖክ ነው:: ሄኖክ ውሉደ እግዚ
አብሔር የተባሉት የሴት ልጆች
በሰይጣን ወጥመድ ተይዘው ከእግዚ
አብሔር ፈቃድ እንደ ወጡና በ
ማይገባ ፍትወት ተመስጠው ከደብር
ቅዱስ ሊወርዱ እንደተነሱ ሲያይ
«እናንተ ልጆች ወዮላችሁ፤ ተወ
የአባታችሁን መሀላ ያፈረሰ ከደብረ
ቅዱስ የወረደ፣ከአዋልደ ቃየል ጋርም
ኃጢአት የሠራ ተመልሶ ወደ ደብር
ቅዱስ አይገባም» ብሎ መክሯቸው
ነበር:: /ኩፋ.5÷21–22፣ ዘፍ.6÷1–3፣
ሄኖክ፣4÷69–88፣5÷1–8/:: እነሱ ግን
ይህን ምክሩን አልተቀበሉትም ነበር::
ሄኖክም በዚህ እያዘነ ከመብል ከመጠ
ጥ ራሱን ከልክሎ ሰው ወደሌለ በት
ወደ አንፃረ ገነት ሄዶ በግብረ ምን
ኩስና ጸንቷል:: በኋላም ፈቃደ እግዚ
አብሔር ወደ ብሔረ ሕያዋን አሳ
ርጎታል:: /ዘፍ.5÷24፣ዕብ.11÷5/::

በተጨማሪም መልከ ጼዴቅ
የእግዚአብሔር አገልጋይ /ካህን/
ሆኖ ጠጉሩን ሳይላጭ፣ጥፍሩን ሳይ
ቆረጥ፣ጠጅ ሳይጠጣ፣በስንዴና በወ
ይን እያስታኮተ ኖሯል::

ቴስብያዊ ኤልያስም ሄኖክን
አብነት አድርጎ በድንግልና ጸዋሚ
ተኀራሚ ሆኖ እግዚአብሔርን እያገ
ለገለ በሥልጣኑ ሰማይ ዝናም
ለዘር፤ ጠል ለመከር እንዳይሰጥ፣
ምድርም የተከሉባትን እንዳታጸድቅ
የዘሩባትን እንዳታበቅል እያወገዘ
በመንፈሳዊ ግርማ ታፍሮ ተከብሮ
ከኖረ በኋላ እንደሄኖክ በአፍራስ
ሠረገላ እሳት በእሳት ወደ ሰማይ ዐ
ርጓል:: 2ኛ ነገ.2÷11::

ብዙ ሰዎች ገዳማዊ /የምን
ኩስናን/ ሕይወት ከአምላክ የተለየ
ከንቱ ሰው ሠራሽ ግብር አድርገው
ይቆጥሩታል:: ነገር ግን እውነታው ያ
አይደለም:: ጌታችን መድኃኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ
ጽድቅ መንግሥተ ሰማያትን ለመው
ረስ የፈለገ ያለውን ትቶ መሄድ
እንደሚገባው አስተምሮአል:: «ስለ
ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን
ወይም እኅቶችን ወይም አባትን
ወይም እናትን ወይም ሚስትን
ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ
ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል:: የዘላለ
ምንም ሕይወት ይወርሳል» ማቴ. 19÷29
ሲል:: «እርሱ ግን ጌታ ሆይ አስቀድሜ ል
ሂድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ
አለ:: ኢየሱስም÷ ሙታናቸውን እንዲቀብሩ
ሙታንን ተዋቸው:: አንተስ ሂደህ የእግዚ
አብሔርን መንግሥት ስበክ አለው» /ሉቃ.
9÷60/:: ሐዋርያት ሁሉን ትተው ጌታን
ተከትለውታል:: ማቴ.10÷ 20፤19÷27::
ይህንን የጌታችንን ስብከት ሰምተው ሕዝ
ቡን አስተምረው ሕዝቡ ያላቸውን ሁሉ
ሸጠው ለድሆች ይከፋፈል ዘንድ በእግራ
ቸው ሥር አኑረዋል:: ሐዋ. 4÷35::

ይህን ጥሪ ሰምተው ራሳቸውን ከዓ
ለም ለይተው ንጽሕ ጠብቀው ለሚኖሩ
ሰዎች በሰማያት ታላቅ ተስፋ እንዳላቸው
ተጽፏል:: *ኤፌ.1÷18፣ቆላ.1÷15::* በዚህ
መሠረት በርካታ ገዳማውያን ራሳቸውን ከ
ማኅበረሰባቸው አግልለው ከጥሉላት በመ
ከልከል በዋሻ ውስጥ ይኖሩ ነበር:: ከነዚ
ህም ናዝራውያን /Nazraites/ ፣ሬካባውያን
Rochabites/ እና ካታኮይ /Catachoi/ የተባ
ሉት በአይሁዳውያን እምነት የሚጠቀሱ
ናቸው::

በዘመነ ሐዲስ የገዳም ሕይወት
የተጀመረው በአፍሪካ ክፍለ አኅጉር በግ
ብጽ ነው:: በ251 ዓ.ም በማዕከላዊ ግብጽ
የተወለደው ቅዱስ እንጦንስ በነገረ ሃይማ
ኖት ኮትኩተው ያሳደጉት ወላጆቹ ከዚ
ህ ዓለም በሞት ሲለዩ ትተውለት ያለፉ
ትን ሀብትና ንብረት በመሸጥ መነነ::
በመጀመሪያ የሄደው በወቅቱ ታዋቂ ቅዱስ
ወደነበረው የቴቤሱ ጳውሎስ /Paul of The-
bes/ ዘንድ ነበር:: ለዓመታት ከእሱ እግር
ሥር ተቀምጦ ምክርንና ትምህርትን
አገኘ:: አባ እንጦንስ ምንም እንኳን
ያገኘው ትም ህርት በሕገ እግዚአብሔር
ለመኖር የሚያ በቃው ቢሆንም ከዚህ
የበለጠ ራሱን ለመግ ዛትና ለማስተካከል
የናይልን ወንዝ አቋርጦ ሙቀቱ በእጅጉ
ወደሚፈታተነው ፒስፒር /Pispir/ በረሃ
ገባ:: /Meniardus ገጽ 18::/ ይህን ያዩና
የሰሙ በርካታ ግብፃውያን ክርስቲያኖች
አባ እንጦንስ ወደ ነበረበት በረሃ መጡ::
/ገድለ አበው/:: በዚህ በእ ጅጉ የተደሰተው
አባ እንጦንስም የመጡ ትን ሰዎች
በምክርና በትምህርት ዓላማቸ ውን እንዲ
ረዱ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው
እንዲሰጡ አደረገ:: ይህ አባ እንጦንስ የመ
ሠረተው ገዳም ታላቅ ቅዱስ ቦታ ለመሆን
በቃ::

ይሁን እንጂ ከበረሃው ጽናት
የተነሣ ገዳማውያኑ በረሃብና በበሽታ ያልቁ
ጀመር:: ይህንን ያየ አባ እንጦንስም ችግሩ
መሠረቱን የጣለውን የገዳም ሕይወት
ቀጣይነት የሚፈታተን እንደሚሆን
ተረዳ:: በመሆኑም የናይልን ወንዝ
ተከትሎ ውኃና የእርሻ ቦታ ያለበት
ቦታ ፈልጎ ገዳሙን ወደዚያ አዞረ::
አባ እንጦንስ ለተጠራለት ዓላማ በሚ
ገባ ከተጋደለ በኋላ የመሠረተውን ገዳ
ምና የሰበሰባቸውን ገዳማውያን ትቶ
በ105 ዓመቱ ዐረፈ::

በዚህ ሁኔታ በግብጽ የተጀ
መረው ገዳማዊ ሕይወት እየቆየ በሌ
ሎች የሀገሪቱ ክፍሎችና በአካባቢው
ሀገራትም እየተስፋፋ መጣ::

ይኸው ገዳማዊ ሕይወት በኢ
ትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጀመር የግ
ብጹ የገዳም ሕይወት እንቅስቃሴ ነጸብ
ራቅ እንደሆነ ይታመናል:: ይሁን
እንጂ አንዳንድ የቤተክርስቲያን ታሪክ
ተመራማሪዎች የገዳም ሕይወትን ለኢ
ትዮጵያ ያስተዋወቁት የሶርያና የጽርዕ
/ግሪክ / መነኮሳት እንደሆኑ ይገልጻሉ::
/ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን፣ገጽ
50::/ ነገር ግን የገዳም ሕይወት በሀገራ
ችን ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በመ
ጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት የነበረ
ውን የገዳም ሥርዓት ስንመለከት የግብ
ጻውያኑን ሥርዓት ተከትሎ እናየ
ዋለን:: ይህም ለሀገራችን የገዳም ሕ
ይወትን ያስተዋወቁት ግብፃውያን
ናቸው ያስብላል:: /ሀጐስ ገ/ማርያም፣
ገጽ33 /::

የሆነው ሆኖ የገዳም ሕይወት
በሀገራችን ከተጀመረ በኋላ ፈጣን ዕ
ድገት አሳይቷል:: ለዚህም የተለያዩ
ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ::

### 1.የውጭ ሀገር መነኮሳት ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

የሃገራችንን እንግዳ ተቀባይ የመ
ሆን አኩሪ ባሕል በመጠቀም በተለያዩ
ጊዜያት በተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ
በርካታ መነኮሳት ወደኢትዮጵያ መጥ
ተዋል:: ከባዕድ ሀገር መጥተው ለገ
ዳም ሕይወት መስፋፋት ከፍተኛ አስ
ተዋጽኦ ያደረጉትን መነኮሳት ለሁለት
በመክፈል እንመለከታቸዋለን::

1.1የጻድቃን ቅዱሳን /The Tzada-
kan Saints /

እነዚህ ቁጥራቸው በውል ያልታ
ወቀ መነኮሳት በዘመነ አክሱም ከቤዛ
ንታይን የመጡ ሲሆን የመጡበትን ዓላ
ማ በጽሑፍ ላገኘው አልቻልኩም::
መነኮሳቱ ወደኢትዮጳያ እንደ መጡ
መጠራ /matara / በተባለች ተራራማ
ቦታ /ኤርትራ ውስጥ ነው/ ተቀምጠ
ዋል:: መነኮሳቱ በአካባቢው ነዋሪዎች
የተገለሉ ነበሩ:: ምንም እንኳን የተ

ወስኑት በደረሰባቸው የመገለል ችግር የሚበሉት እያጡ «ከአሁን በኋላ ምን እናደርጋለን? ገብተን እንተኛና በዚያው እንሙት» እያሉ በየዋሻው እየገቡ በዚያው ቢያልቁም የቀሩት ግን በብዛት በኤርትራ የሚገኙ ገዳማትንና በተወሰነ ደረጃ በትግራይ የተወሰኑ ገዳማትን መሥርተዋል:: ከዚያም አልፎ በርካታ አሕዛብ ቤኒአሚሮችን አጥምቀዋል::

2.2 ዘጠኙ ቅዱሳን

እነዚህ ቅዱሳን መሠረቱ በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተጣለውን የክርስትና እምነት አጠናክረዋል:: ቅዱሳኑ በጉባኤ ኤፌሶን የተወገዘውን ኋላም በጉባኤ ኬልቄዶን መለካውያን መልኩን በንባብ ሸፍነው የተቀበሉትን የሁለት ባሕርይ እምነት አንቀበልም በማለታቸው በቢዛንታይን ነገሥታት ስቃይ ቢጸናባቸው ከሶርያና ከታናሽ እስያ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ናቸው:: የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብም በተመሰከረለት አብርሃማዊ የእንግዳ አቀባበል ባሕሉ ቅዱሳኑን ተቀብሏል:: እነሱም ኢትዮጵያን እንደተወለዱባት አገር ቆጥረው ክርስትናን በማስፋፋት ገዳማት መሥርተዋል:: እነዚህ ቅዱሳን የመሠረቷቸውን ገዳማትና የዕረፍት

| ተ.ቁ | ስም | የዕረፍት ቀን | ገዳም |
|---|---|---|---|
| 1 | አባ አሌፍ | መጋቢት 11 | ብዙኃን /አህስአ/ |
| 2 | አባ አረጋዊ | ጥቅምት 14 | ደብረ ዳሞ |
| 3 | አባ አፍጼ | ግንቦት 12 | ዮሐ /የሐ/ |
| 4 | አባ ሊቃኖስ | ኅዳር 21 | ደብረ ቆናጽል |
| 5 | አባ ገሪማ | ሰኔ 17 | መደራ |
| 6 | አባ ይመአታ | ግንቦት 29 | ገርዓልታ |
| 7 | አባ ጰንጠሌዎን | ጥቅምት 6 | እኩስም አጠገብ |
| 8 | አባ ጻሕማ | ጥር 16 | ጼዴንያ |
| 9 | አባ ጎባ | — | ጠቐራ |

ቀናቸውን ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ» /ገጽ 24/ በተሰኘው መጽሐፋቸው ያሰፈሩትን አስቀምጠነዋል::

2. የኢትዮጵያ ቅዱሳን ትጋት

ከላይ ከጠቀስናቸው ስደተኞች ቅዱሳን በተጨማሪ ኢትዮጵያኑ አባ ቶችም በሀገራችን ክርስትናን አስፋ ፍተዋል፤ ገዳማትን መሥርተዋል:: ታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም በአቡነ ተ/ሃይማኖት፣ ደብረ ሃሌ ሉያ በአቡነ ሳሙኤል፣ ፃዕዳ አምባ በአቡነ ይምርሐነ ክር ስቶስ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በአባ ኢየሱስ ሞዓ ፣ቆርቆር ደብረ ማርያም በአቡነ ዳንኤል፣ደብረ ፀራቢ በአቡነ ኤዎስጣቴዎስ፣ ደብረ በንኮል በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ፣ደብረ ሃሌ ሉያ በአባ ሳሙኤል ዘደብረ ሃሌ ሉያ፣ ቁየፃ ገዳም በአቡነ ሳሙኤል ዘቁየፃ ፣ዳግና ገብረ ክርስቶስ በአቡነ ገብረ ክርስቶስ ፣ዳዕዳ ዓምባ በአቡነ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ደብረ ሙጅና በአቡነ ያዕቆብ፣ መንዳባ በአቡነ ያሳይ፣ ዳጋ እስጠፋኖስ በአቡነ ሂሩተ አምላክ፣ክብራን ገብርኤል በአቡነ ዘዮሐንስ፣አሰቦት ገዳም በአቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ፣ መቄት በአቡነ አሮን፣መርጡ ለማርያም ርዕሰ ርዑሳን ተክለ ማርያም ደብረድማህ ጊዮርጊስ በአቡነ ተከስተ ብርሃን፣ ደብረ ቢዘን በአቡነ ፊልጶስ፣ዋልድባ ገዳም በአባ ሳሙኤል፣ ፣ጉንዳጉንዲ ገዳም በአባ ይስሐቅ፣ምሁር ኢየሱስ ገዳም በአቡነ ዜና ማርቆስ ሊጠቀሱ የሚችሉ ታላላቅ ገዳማት ናቸው::

3 የነገሥታት ድጋፍ

በኢትዮጵያ የታሪክ መዛግብት እንደ ምናገኘው በየዘመኑ የተነሡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ገዳማት እንዲቋቋሙ ለኢትዮ ጵያ ርዳታ ሲያደርጉ ቆይተዋል:: ይህም ለዘመነ መንግሥታቸው የቤተክርስቲያን ቀኝ እጅነት በማሰብ እንደሆነ የታሪክ መዛግብቱ አክለው ያስረዳሉ::

የገዳማት አስተዳደር

ገዳማት የራሳቸው የሆነ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ሥርዓት አላቸው:: በመጀ መሪያ አስተዳደራዊውን ሥርዓት እንመ ልከት:: አንድ ገዳም የራሱ የሆነ አስተ ዳደራዊ መዋቅር አለው::

ሀ. አበምኔት

አበምኔት ማለት የአንድ ገዳም የበላይ ኃላፊ ነው:: ገዳሙ የሴቶችም ከሆነ የበላይ ኃላፊዋ እመምኔት ትባ ላለች:: የአንድ ገዳም አበምኔት በትም ህርተ ፣በትሩፋቱና በአስተዳደር ችሎታ ውም የታወቀ መነኩሴ ከማኅበሩ ተመ ርጦ ይሾ ማል:: የሚሾመው የቁምስና ማዕረግ ያለው መነኩሴ መሆን አለበት:: ማንኛ ውም የማኅበሩ አባል ለአበምኔቱ ምክርና ትእዛዝ እንዲሁም መመሪያ መገዛት አለበት:: አበምኔቱ በገዳሙ ልዩ ልዩ የሥ ራ ክፍሎች በኃላ ፊነት የሚሾሙ መነ ኮሳትን በማኅበሩ አስመርጦ ይሾማቸዋል::

የአንድ ገዳም አበምኔት የሚ መረጥበት ሥርዓት አለው:: በመጀመ ሪያው የማኅበሩ ጉባኤ ምርጫው መቼ መሆን እንደሚገባው ይወስናሉ:: በተወ ሰነው ቀን መነኮሳቱ በቤተማኅበራቸው ተሰ ብስበው ከጸለዩ በኋላ ይመርጡ ታል:: የተ ለያዩ የአመራረጥ ዘዴዎች አሉ:: ነገር ግን ዋናውና በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው የእጅ ድምፅ ብልጫ ዘዴ ነው:: በ1964 ዓ. ም በፀደቀው የገዳማት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ አራት ላይ በገዳማት ውስጥ የሚ ደረግ ምርጫ በድምፅ መስጫ ሳጥን በሚሰ በሰብ ድምፅ እንዲሆን ተደንግጓል:: አበም ኔቱ ከተመረጠ በኋላ ወደቤተክርስቲያን በመሄድ ከማኅበሩ ጋር ጸሎት ያደርጋል:: ጸሎተ ቡራኬም ይደርሳል:: ከዚያም ከተ ዘጋጀለት ቦታ ይቀ መጥና መነኮሳቱ ተራ በተራ እየቀረቡ እጅ ይነሡታል:: በዚህ ሁኔታ የተመረጠው አበምኔት ወደ ፓ ትርያርኩ ይቀርብና ሹመቱ ይጸድቃል::

አበምኔቱ ፈጣን ውሳኔን የሚሻ ጉዳይ በገዳሙ ውስጥ ቢፈጠር ከገዳሙ ልዩ ልዩ ክፍሎች ኃላፊዎች ጋር መክሮ ውሳኔ ይሰጣል:: በዐበይት በዓላት ጊዜ ቅዳሴ ባይቀድስ እንኳን ተገኝቶ ጸሎተ ቡ ራኬ ማድረስ አለበት፤ /የገዳማት መተ ዳደሪያ ደንብ፣አንቀጽ 7/::

ከዚህ በኋላ አበምኔቱ በገዳሙ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ላይ በኃላፊነት የሚቀመጡ መነኮሳትን በማኅበሩ አስ መርጦ ይሾማል:: እነዚህም መጋቢ፣ ገበዝ፣ዕቃ ቤት ጠባቂ ፣አንድ ጸሐፊና ሒ ሳብ ያዥና ሊቀ አርድእት ናቸው:: በአንዳንድ ቦታዎች በገዳማቱ ለሚኖሩ አብያተክርስቲያናት በኃላፊነት ሊቀ ካህ ናት ይሾማል:: ለማንኛውም ከላይ የተ ዘረዘሩትን ኃላፊዎች የሥራ ዝርዝር እን መለከታለን::

ሀ. መጋቢ

መጋቢ በገዳሙ ውስጥ ከአበ ምኔት ቀጥሎ ከፍተኛ ኃላነፊት ያለበት ሰው ነው:: አበምኔቱ በገዳሙ ሳይኖር ሲ ቀር በተለይ በአበምኔቱ ከሚፈጸመው መንፈሳዊ አገልግሎት በቀር በአስተዳደር በኩል ያለውን ማንኛውንም ሥራ በኃላ ፊነት ይሠራል:: ማናቸውም የገዳሙ ገቢ ዎች በጊዜው እንዲሰበሰቡና ገቢ እንዲ ደረጉ ያደርጋል:: አስቸኳይ መፍትሔ የሚያሻቸውን የመወያያ ነጥቦች /አጀ ንዳዎች/ እየተቀበለ እንዲመከርባቸው ለአ በምኔቱ ያቀርባል:: በየወሩ መጨረሻ የገዳ ሙን አጠቃላይ የገንዘብ ሪፖርት ለአ በምኔቱ ያቀርባል:: ጉዋል መጋቢ የተሰኘ ምክትል አለው:: /ዝኒ. ከማሁ፣አንቀጽ 8/::

ለ. ገበዝ

ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተመደቡት መነኮሳት ሥራቸውን በት ክክል እንዲሠሩ ይቆጣጠራል፤ በጐደለ ይሞላል:: በፍትሐት፣ በአትርሱኝ፣ በሙ ታን ተዝካር፣በምጽዋት በመገበሪያና በሙ ጋድ ይህንንም በመሳሰለው ሁሉ ከምእ መናን የሚገኘውን ገንዘብ በደንበኛ የደ ረሰኝ ወረቀት እየተቀበለ በመጋቢው ኃላ ፊነት ወደ ገዳሙ ግምጃ ቤት እንዲገባ ያደርጋል:: የቤተክርስቲያኑን ጽዳት ይጠ ብቃል፤ያስጠብቃል:: የቤተክርስቲያኑ አል ባሳትና ንዋየ ቅድሳትም መጻሕፍትም በደ ንብ ተጠብቀው እንዲቀመጡ ያደ ርጋል:: /ዝኒ. ከማሁ፣አንቀጽ 9/::

ሐ. የዕቃ ቤት ጠባቂ

የዕቃ ቤት ጠባቂ አንዳንድ ጊዜ እንደ ገዳሙ ገንዘብ ያዥ በመሆን ያገለግላል::

መ. ጸሐፊ

በየጊዜው ስለሚቀበለው ገንዘብና ዕቃ እንዲሁም ማናቸውም ሀብት ኃላፊ ይሆናል፤ ስለወጪውም የገዳሙን ደንብ ተከትሎ ይሠራል:: ለዕለት ለገዳሙ አገልግሎት ከሚሆነው በቀር ማናቸውም የገዳሙ ተቀማጭ ሀብት እየተሰበሰበ ለመቀመጡ ኃላፊነት አለበት:: /ዝኒ. ከማሁ፣ አንቀጽ 10/::

በገዳሙ የአስተዳደር ቦርድ ተመ ክሮባቸው ውሳኔ ያለፈባቸው ጉዳዮች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል:: በሚተላለ ፈውም ትእዛዝ የጽ/ቤቱ ማኅተምና የባለ ሥልጣኑ ፊርማ ሳያርፍበት ማናቸውም ጉዳይ እንዳይሠራበት ተጠንቅቆ ይጠብቃል:: ለገዳሙ ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ የሚሆኑ መዝገቦችንና ደረሰኞችን ያዘጋጃል:: /ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 11/::

ሠ. ሊቀ አርድእት

ከመጋቢው በታች ከአርድእቱ በላይ ሆኖ ይሠራል:: ከቅጽረ ገዳሙ ውጭ ባሉት ርስት ጉልቶች እየዞረ አርሻ ያሳ ርሳል:: አትክልት ያስተካክላል:: ለማኅበሩ ምግብ የሚሆነውን የቀረበው ከማለቁ አስቀድሞ እያሰበ ያዘጋጃል:: /ዝኒ. ከማሁ፣ አንቀጽ 12/::

እንግዳ አቀባበል

ወደ አንድ ገዳም በእንግድነት የሚሄዱ ሰዎች በሁለት ይከፈላሉ:: የመጀመሪያዎቹ ንስሐ ለመቀበል በአበው ለመባረክ የሚመጡ ሲሆኑ እንደእነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች መጋቢው ተቀብሎ ካነጋገራቸው በኋላ ለአበምኔቱ አሳይቶ ለሦስት ቀናት ለእንግዳ ማረፊያ ከተሰናዳው ቤት አሳርፎ ሲያስተናግዳቸው ሰንብቶ ይሸኛቸዋል:: ሁለተኛዎቹ ደግሞ በሁለት ዓይነት መንገድ በገዳሙ ለመኖር የሚመጡ ናቸው:: አንድም በገዳሙ ውስጥ በጉል በታቸው እየተራዱ ለማገልገል የሚመጡ አሉ:: እነዚህን መጋቢው ተቀብሎ ለሰባት ቀናት ያስተናግዳቸውና በሰባተኛው ቀን ለማኅበሩ ካስተዋወቃቸው በኋላ እንደገዳሙ ሥርዓት አገልግሎታቸውን ይጀምራሉ::

ሥርዓተ ገዳሙን ፈጽመው በምንኩስና ለመኖር የሚመጡም አሉ:: በመጀመሪያ ወደገዳሙ ማኅበር በምንኩስና ለመዋሐድ የሚመጣ ማንኛውም ሰው ከፓትርያርኩ ወይም ከክፍሉ ሊቀጳጳስ የፈቃድ ወረቀት ይዞ መምጣት አለበት:: /ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 15/:: እነዚህንም መጋቢው ይቀበልና በአበምኔቱ አማካኝነት ለማኅበሩ ሃይማኖቱን በመሃላ ካረጋገጠ በኋላ ስማቸው ተመዝግቦ የአመክሮ ጊዜያቸውን ይጀምራሉ::

ዓለመ ምንኩስናን መርጦ ወደ ገዳም የሚሄድ አንድ ሰው እንደደረሰ የምንኩስና ቆብ አይደፋለትም:: ቢያንስ ለሦስት ዓመት ከማኅበሩ በተመረጡ አባቶች /መምህራን/ ልዩ ልዩ ትምህርቶችንና ሥልጠናዎችን እየወሰደ ይቆያል:: ይህም የእጩ መነኩሴው የአመክሮ ጊዜ ይባላል:: መምህራኑ በዚህ ቆይታው የውሳኔው ጽናትና ቆራጥነቱ ይታይ ዘንድ ልዩ ልዩ ከባድ ሥራዎች ይሰጡታል::

ገዳሙ የአንድነት ገዳም ከሆነ በማኅበሩ የሚኖር ማንኛውም መነኩሴ የግል ገንዘብ /ቁሪት/ እንዳይኖረው ተደንግጓል:: መናኙ ወደገዳሙ ከመምጣቱ በፊት ትዳር፣ሀብትና ንብረት ያለው ከሆነ ከሦስት ሁለት እጅ የሚሆነውን ለቤተሰቦቹ ትቶ ከሦስት አንዱን እጅ ለገዳሙ ገቢ ማድረግ አለበት:: /ዝኒ. ከማሁ፣አንቀጽ 13እና 14/::

አንድ መነኩሴ ከገዳሙ ስለሚባረርበት ሁኔታም ተደንግጓል:: መነኩሴው የገዳሙን ሕግና ትእዛዝ በመተላለፍ ያለአበምኔቱ ፈቃድ ከቅጽረ ገዳሙ ወጥቶ እንደዓለማውያኑ ከተማ ወይም መንደር ቢወጣና ቢወርድ በመጀመሪያ ከማኅበሩ ሁለት ሆነው ይምከሩት፤ ባይሰማ ወደ አበምኔቱ አቅርበው ያስመክሩት:: አበምኔቱንም ባይሰማ በማኅበሩ ፊት አቁመው ይምከሩት:: አሁንም ማኅበሩን ባይሰማ ከማኅበሩ ተለይቶ ቀኖና ይሰጠው:: ነገር ግን ቀኖናውን አልቀበልም ቢል ከማኅበሩ አንድነት ይለዩት:: /ዝኒ. ከማሁ አንቀጽ 15/::

የአመጋገብ ሥርዓት

ገዳማት እንደ የዓይነታቸው የየራሳቸው የአመጋገብ ሥርዓት አላቸው:: የአንድነት ገዳማት ከሆኑ ገዳማውያኑ በአንድነት በግብር ቤታቸው ይመገባሉ:: የቁሪት ከሆኑ ግን በማዕከልነት መቁነኑ ከሚዘጋጅበት ቦታ ገዳማውያኑ በሚቀርብላቸው ደወል አማካኝነት እየመጡ መቁነናቸውን በመውሰድ በየበዓታቸው /መኖሪያ ቤታቸው/ ይመገባሉ:: የመቁነኑ ዓይነትም ቢሆን ከቦታ ቦታ ይለያያል:: በብዛት ዳቤ የተባለ ዳቦ መሰል ምግብ ሲሆን በዋልድባ የደረቀ የሙዝ ዱቄት ቋርፍ በደብረ ቢዘን እንጀራና ወጥ በምሳሌነት ለየት ካሉት ናቸው:: የሆነው ሆኖ የመቁነን ሥርዓቱም ሆነ ይዘቱ ቢለያይም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እስከ ሚያውቀው ድረስ በየትኛውም ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት የሚመገቡት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው::

ገዳሙ የአንድነት ከሆነ በአበምኔቱ መሪነት ጸሎት ተደርጐ ማኅበረ መነኮሳቱ ይመገባሉ:: በመቁነን ወቅት እንደዜና አበው፣ መጽሐፈ ገነትና የመሳሰሉት መጻሕፍት ይነበባሉ:: የመቁነኑ ሥርዓት ሲፈጸምም በአበምኔቱ መሪነት አቡነ ዘበሰማያት የተሰኘው የጸሎት ክፍል በዜማ ይጸለያል::

በገዳሙ የሚኖሩ ማኅበረ መነኮሳት ለሕሙማን የዕለት መታመሚያ በአርድዕት አገልግሎት ማጠናከሪያ ከተፈቀደላቸው በቀር በመቁነን አይበላለጡም:: በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሁለተኛው ሲኖዶስ አንቀጽ 15 በተደነገገው መሠረት ለእያንዳንዱ መነኩሴ በየዓመቱ አንድ ጊዜ አንድ የሥራና አንድ የበዓል ልብስ ይሰጠዋል:: ዓመቱ ደርሶ ሌላ አዲስ ሲቀበል አሮጌውን ያስረክባል:: የብርድ ልብስና ምንጣፍ በሁለት ዓመት አንዴ ይታደላል:: /ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 18/::

የገዳማውያኑ ውሎ

ገዳማውያን መነኮሳት ከላይ ከተገለጹት የሥራ ክፍሎች አንጻር በርካታ የሥራ ኃላፊነት ቢኖርባቸውም በግን ባር ቀደምትነት ሕይወቱን ከመምረጣቸው አንጻር ከእግዚአብሔር በየጊዜው በጸሎት የመገናኘት ግዴታ አለባቸው:: በመሆኑም ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ «ተዘከርኩ በሌሊት ስመከ– በእኩለ ሌሊት አመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ» እንዳለ (መዝ.119÷62) ሌሊት ለጸሎት ይነሣሉ:: በዚያም ከሰዓታቱ ጋር መልክአ መልክዐ እና ተአምረ ማርያም ይነበባል:: ከሰዓታቱ በኋላ ሁለት የተመረጡ አባቶች ጸሎተ ዕጣን ያደር ሣሉ:: ከዚያም ጸሎተ ሃይማኖት፣ ዳዊትና ስንክሳር ይነበባል:: ሊነጋጋ ሲል በዕድሜ የበላይ በሆነ አባት መሪነት የማኅበሩ ጸሎት ይደርሣል:: በዚህ የማኅበር ጸሎት ለገዳሙ ስፋት፣ ለገዳማውያኑ ፍቅር፣ አንድነትና ከፈተና መጠበቅ፣ስለቤተክርስቲያን ከጠላት መጠበቅ፣ ስለሀገሪቷ ሰላም አንድነት ይጸለያል:: ከንጋቱ 12:00 ሲሆን መነኮሳቱ በየበዓታቸው ሄደው የግል ጸሎታቸውን እንዲያደርሱ ይለቀቃሉ::

ከረፋዱ 3:00 ሰዓት ሲሆን በአስተባባሪዎች አማካኝነት እያንዳንዱ መነኮሳት እንደየችሎታቸው ለሥራ ይሠማራሉ:: ከቀኑ 6:00 ሲሆን ወደቤተክርስ ቲያን በመ ሄድ እስከ 7:00 የግል ጸሎታቸውን ያደር ሱና 8:00 ሲሆን ሁለተኛው ጸሎተ ማኅበር ይደረጋል:: በዚህ ጊዜ መነኮሳቱ በውሏ ቸው የሠሩት ኃጢአት ካለ ወደ አበምኔቱ እየቀረቡ ንስሐ ይገባሉ:: ጸሎቱ ተጠናቆ 9:00 ሲሆን የመቁነን ደወል ይደወላል:: ከመቁነኑ ፍጻሜ በኋላ እስከ 12:00 መነ ኮሳቱ የፈለጉትን ሥራ በየበዓታቸው በጸጥታ ይሠሩ ዘንድ ነፃ ጊዜ ይሰጣቸዋል:: 12:00 ሲሆን ለኅብረት ጸሎት ደወል ይደወልና መነኮሳቱ ይሰበሰባሉ:: ጸሎቱ ከተፈጸመ በኋላ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ክፍሎች ይነበባሉ:: ስብሐተ እግዚአብሔር ይደርሳል፣የዕለቱን ውሎ አስመልክቶ አበምኔቱ የተገደፈው እንዲስተካከል፣ የተከናወነው እንዲበረታታ መመሪያ ይሰጥና መነኮሳቱ በየበዓታቸው ይገባሉ::

## <u>የገዳማት አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ</u>

በርካታ የቤተክርስቲያን የታሪክ መዛግብት እንደሚያስነብቡን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተቻቸው ሥጦታዎች ብዙ ናቸው:: ከነዚህም «ሙሉ ትምህርት፣ ፍጹም ቋንቋ ከነፊደሉ፣ሥነ ጽሑፍ ከነጠባዩ ከነሙያው፣ ኪነጥበብ በየዓይነቱ፣ሥነ ጥበብ በየመልኩ፣ ታሪካ ዊና ጥንታዊ ቅርስ፣ እምነት ከነፍልስ ፍናው፣ነፃነት ከነድንበሩ፣ከነፍቅሩ፣ስም ከነምልክቱና ከነትርጉሙ ይጠቀሳሉ::» /አባ ጎርጎርዮስ፣<u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ.ታሪክ</u> – ገጽ . 9/:: ታዲያ በዚህ ዓይነት በየዘርፉ አስተዋጽኦ

ካደረገችባቸው መድረ ኮች ውስጥ ገዳ ማት ዋነኞቹ ናቸው:: በየዘ መኑ በልዩ ልዩ አባቶች የተመሠረቱት ገዳማት ከአ ካባቢያቸው አልፈው ለአጠቃላይ የሀገ ራቱ ዕድገት በርካታ አስተዋጽኦዎች አበ ርክተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋና ዎቹን እንደሚከተለው እንመለከታለን::

### ሀ ለዘመናዊው ትምህርት መሠረት ጥለዋል

እንደሚታወቀው ሀገራችን ከዘ መናዊው ትምህርት ጋር ከመተዋወቋ በፊት የተለያዩ ጥንታውያን ገዳማት ከፍ ተኛ የትምህርት ማዕከላት ነበሩ:: ዛሬ በልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች አንጋፋ የሚባሉ የሀገራችን ምሁራን በእነዚሁ አድባራትና ገዳማት ፊደል የቆጠሩ መሆ ናቸው ይህንኑ ይመሰክራል:: በእነዚህ አድባራትና ገዳማት የሀገራችንን ታሪክ፣ መንፈሳዊ ፍልስፍና፣ጥበብ፣ ወዘተ ለዓ ለም የሚያስተዋውቁ በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል:: በመሆኑም ገዳማት ለዛሬው ዘመናዊ ትምህርት መሠረት ጣይ ነታቸው ከፍተኛ ድርሻ አላቸው::

### ለ በሀገሪቱ ክርስትና እንዲስፋፋ አድርገዋል

ገዳማት ለዛሬው የክርስትና በመላ ኢትዮጵያ መስበክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ይኸውም ለልዩ ልዩ ሰባክ ያን ወንጌል ምንጭነት በማገልገል ነው:: ዛሬ አንዳንዶች እንደሚሉት /ምና ልባት በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተቀየሩት ካል ሆኑ በስተቀር/ ትጉሃን አባቶች በዓቶቻ ቸውን እየለቀቁ ቃለወንጌል ያላዳ ረሱ በት የኢትዮጵያ ክፍል የለም::

### ሐ. ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ የሥነ ጥበብ ዕድገት

ሀገራችን የሥነ ሕንፃ፣የሥነ ሥዕ ል፣የሥነ ጽሕፈትና ፣የሥነ ዜማ ባለቤት እንድትሆን ያደረጓት እነዚሁ ጥንታ ውያን ገዳማት ናቸው:: በየዘመኑ በየገዳ ማቱ የነበሩ አባቶች የተለያዩ የሥነ ጥበ ባት ውጤቶችን አበርክተዋል:: በሥነ ሕ ንፃው ከላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲ ያናት ጀምሮ ልዩ ልዩ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ፣በሥነ ሥዕሉ የኢትዮጵያ የሚባለው አሣሣል ዘይቤ፣በሥነ ጽሕፈቱ ብቸኛውና የእኛ ብቻ የሆነው የቁም ጽሕፈት፣በሥነ ዜማው ጸዋትወ ዜማው፣ አቋቋሙ ወዘተ እንዲሁም ቅኔው የሚጠ ቀሱ ናቸው:: ለእነዚህ ሁሉ የሥነ ጥበባት ውጤቶች ምንጫቸው ገዳማት ናቸው::

### መ. በልማት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ገዳማት ባቀፏቸው መና ንያን ልዩ ልዩ ልማቶችን በማከናወን ከ ራሳቸውና ከአካባቢያቸው አልፎ ለሀ ገር ዕድገት አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ዋል ድባን /ጎንደር/ በመሰለ ጠፍ የበረሃ ቦታ የሚደረገውን ልማት፣በጋሥጫ በረሃ /ወሎ/ ጋሥጫ ገዳም ላይ የሚከናወነውን የከብት ርባታ፣በሰበታ ቤተ ደናግል የሴ ቶች ገዳም የሚከናወነውን ዘመናዊ የል ማት እንቅስቃሴ ▮ተመለከተ ይህንኑ አባ ባል በተጨባጭ ይረዳል:: ይሁንና አሁን አሁን በሀገራችን ፊቱን እያዞረ ያለው ተፈጥሮ ጥላውን በበርካታ ገዳ ማት ላይ በማሳረፍ መነኮሳቱ በረሃብ እያለቁ የተረፉትም ገዳሙን እየተዉ በመሰደድ ላይ ይገኛሉ::

ይህ የገዳማት የልማት እንቅ ስቃሴ ቁሳዊ ጥቅም ብቻ የለውም:: ሞ ራላዊ ጥቅምም አለው:: ይኸውም መነ ኮሳቱ በገዳማቸው የሚያደርጉት እንቅ ስቃሴ የሚመለከቱ የአካባቢው ነዋ ሪዎች ትምህርት በማግኘት ለልማት እነሱም ይነሣሣሉ:: ይህም በተለያዩ ገዳ ማትና አካባቢያቸው ታይቷል::

### ማጠቃለያ

ይህ ጽሑፍ ገዳማዊ ሕይወትንና ሥርዓቱን በሚመለከት ለአንባብያን መጠ ነኛ ግንዛቤ እንደሰጠ እናምናለን:: በረ ከታቸውና ትሩፋታቸው ለመላው ምእ መናንና በአጠቃላይ ለሀገር ለወገን ዐቢ ይ የሆነው የእነዚህ ገዳማት በሁሉም ባይሆን በውስጣቸው የሚኖ ረው ሕ ይወት እንዲሁም ሥርዓታቸው ዛሬ ዛሬ እንደጥንቱ አይደለም:: ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይች ላሉ:: ዋነኞቹ ግን ውስጣዊና ውጫዊ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ:: ውስጣዊ ከሚባሉት የብዙዎቹ መነኮሳት ዓላማን ያለመረዳት፣በብዙዎች ገዳማት መነኮ ሳት የአመክሮ ጊዜያቸውን መጨረስ ሳይሆን ሳይጀምሩ ቆብ መድፋት /ሥርዓቱ ስለሚፈጸምላቸው/፣ የየገዳ ማቱን የአስተዳደር ልልነት፣ የቤተ ክር ስቲያን ገዳማቷን በሚገባ ዐውቆ ያለ መቆጣጠር ችግር ሊጠቀሱ ይችላሉ::

ዛሬ ከየትኛው ገዳም እንደ መጡ የማይታወቁ በርካታ መነኮሳትና መነኮሳይያት በዓታቸው ትተው በየከተ ማው ሲዟዟሩ ይታያሉ:: የቀደሙት አባቶቻችን የደነገጉልን ሕግ «ማንም በዓቱን ለቆ በመንደርና በከተማ ሲ ወጣና ሲወርድ ቢገኝ ተመክሮ አልሰማ ካለ ከማኅበሩ ይለይ» እያለ በማይ ታወቅ የግል ጉዳያቸው ከተማ ገብተው ከቀናት አልፎ ወራት ሲያስቆጥሩ የገዳ ማቸው አስተዳደር በደንቡ መሠረት እርምጃ ሲወስድባቸው አይታይም:: ቤተክርስቲያንም ጉዳዩ በሚመለከተው ክፍሏ «ከየት መጣችሁ? የታለ መታ ወቂያችሁ» ብላ ስትጠይቃቸው አይታ ይም:: እኛም እንደምናየው ብዙ ሰዎ ችም እንደሚሉት ድሮ ድሮ በየት ባየናቸው ሲባሉ የነበሩ መነኮሳት ዛሬ በከተማው በዝቶ መገኘት የቤተ ክር ስቲያን አባቶች ለሕግ ለሥርዓት የማይ ገዙ እያስመሰላቸው ፣ትውልዱ የአባቶ ቹን በረከት እንዳያውቅ እያደረገ እን ዲሁም ለገዳም ሥርዓት ተገዝተው ንጽሕ ጠብቀው በዓታቸውን አጽንተው ያለፉ የቀደሙ አባቶቻችንን ታሪክ እያጠፉ ነው:: ዛሬ መነኩሴ ማለት አስ መሳይ፣ገንዘብ ወዳጅ፣ንጽሕ ያልጠበቀ እንደውም አልፎ አልፎ በሃይማኖት የሚጠረጠር ነው ብለው የደመደሙ ጥቂት ሰዎችን ዐውቃለሁ::

በእርግጥ ብዙዎች ገዳማት ዛሬ ዛሬ በሀገራችን የተከሰተው የተፈጥሮ መዛባት ቀጥተኛ ተጠቂዎች በመሆናቸው ረሃቡ ችግሩ አለ:: ይሁን እንጂ በገዳማት ሕይወት ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትና የቀደሙ አባቶች እንደ ሚነግሩን በንጽሕና በቅድስና ለሕግ ለሥርዓት ተገዥ ሆነው የአቅምን ያህል እየ ሠሩ የእግዚአብሔርን በረከት የጠበቁ አባቶ ቻችን በረከታቸው ከራሳቸው አልፎ ለአካ ባቢው አልፎ ሲልም ለሀገር ለወገን ሲተርፍ ያየንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም:: አሁንም እ᎐የናቸው ያሉ አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ አባ ቶቻችን ብዙዎች ናቸው::

ምንኩስና ራስን ለዓለም ፍቃድ ገድሎ ለሌሎች በሕይወት አርአያ እየሆኑ የሚኖሩበት ሕይወት ነው:: አርአያ ከሚ ኮንባቸው ነገሮች ውስጥ ደግሞ አንዱና ዋነ ኛው ለሥራ ነው:: በገዳማት ውስጥ የሚ ኖሩ አባቶቻችንና እናቶቻችን በዓታቸውን አጽንተው ሥራ እየተጉ ራሳቸውን ችግር በመታደግ ለአካባቢያቸው ማኅበረሰብም አብ ነት ሊሆኑ ይገባል:: በዚህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከጐናቸው መቆም ይኖር ባታል::

ውጫዊ ምክንያት ባልነው አንጻር ደግሞ በከተማም ሆነ በገጠር ያለን ምእ መናን በግንባር ቀደምትነት እንጠቀሳለን:: ከላይ ለገለጽነው የመነኮሳት በዓታቸውን ትተው በከተማና መንደር መበራከት ምክ ንያቱ በዚያ የሚኖሩ ምእመናን ጋባዥነትና ፈትፋችነት ነው:: መነኮሳት ምንም እን ኳን ዓለመ ምንኩስናን መርጠው ለዓለምና ዓ ለም ላፈራው ነገር ሁሉ የሞቱ ቢሆኑም በለ በሱት ሥጋ ሊፈተኑ ይችላሉ:: በመሆ ኑም የምእመናን ጋባዥነት ለመነኮሳቱ በከተማ አካባቢ መበራከት ዋናው ምክንያት ነው:: ዛሬ በአንዳንድ ባዕለ ጸጋ ቤት አንዳንድ መነኩሴ ተዘግቶበት «እንደሚቀለብ» እናያ ለን፣ እንሰማለን:: መነኩሴ «መቀለቡን» በመኪና ይዞ ከተማ ውስጥ መዟዟሩን እን ደጽድቅ ሥራ የሚቆጥሩ ምእመናን ብዙዎች ናቸው:: ይህ ግን ከእውነት የራቀ፣ተጽፎ ያላነበብነው አባቶችም ያላስተማሩን ምና ልባት ሞኝነት ነው::

እንደምናውቀው አንድ ምእመን ንስሐ ለመግባት የአባቶችንም በረከት ለ ማግኘት አቀበቱን ወጥቶ ቁልቁለቱን ወርዶ እሾህ ወግቶት እንቅፋት መትቶት አባቶቹና እናቶቹ ካሉበት ድረስ ይሄዳል:: ዛሬ ግን ያ የለም:: ምናልባት ገዳማውያኑ አንመጣም ብለዋቸው ወይም ለውጥ ፈልገው ገዳም ሲ ሄዱ እንኳን ጭነዋቸው የሚሄዱት ልዩ ልዩ ለሥጋ የሚስማሙ ምግቦች በዳቤ የሚኖሩ መነኮሳትን ልብ ያሸፍታሉ:: በጸሎቱም ሆነ በሌላው ለእኔ የሚሆን ልዩ ሥርዓት ይሠራ ልኝ ብለው ገዳማውያኑን ያስጨንቃሉ፣ ይረ ብሻሉ:: ስለዚህ ምእመናን ይህን ዓይነቱን ኢ -ክርስቲያናዊ ምግባር በያለንበት አርመን እኛ በረከት የምናገኝባቸው አባቶቻችንን በያሉበት ጸንተው ቢጸልዩልን ነውና እነሱን ወደ ከተማ የሚጋብዝ ነገር ከማድረግ መታቀብ አለብን:: የምናደርግላቸው ዕርዳታ የዕለት ጉርስ ብቻ የሚሆን ሳይሆን ሕይወታቸውን በቋሚነት የሚ ቀይር ቢሆን ይመረጣል:: የአባቶቻችንን ሕግና ሥርዓት ጠብቀን ከረድኤታቸውና በረከታ ቸው ተሳታፊዎች እንድንሆን የእግዚአብሔር ቸርነት የእመብርሃን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን:: አሜን::

# ከአንባብያን

## እንንቃ

መቼም በቅድስት ቤተ ክርቲያናችን ሰላም እንዳይኖር በጐቹ በፍቅር እንዳይኖሩ የቅድስናን ሥራ እንዳይሠሩ የሚያደርጉ በየጊዜው ዘዴያቸውን እየቀየሩ የሚመጡ ተኩላዎች እንዳሉ ግልጽ ነው:: ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ለዕረፍት ወደ ጉራጌ ዞን እዣ አካባቢ ሄድኩኝ:: በዓለ አስተርእዮን በአጥቢያችን በደማቅ ሁኔታ እያከበርን እያለ እነዚሁ ተኩላዎች ዓይናቸውን አፍጥጠው ቤተክርስተያናችን ቅጥር ግቢ ድረስ በመግባት የቅሰጣ ሥራቸውን መሥራት ጀመሩ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት በምእመናን ትጋት ይህ እኩይ ተግባራቸው ተጋለጠ:: ሊያዙ ሲሉም አመለጡ:: በዚሁ አካባቢ ሥራዎቻቸው በተደጋጋሚ እንደሚታዩ ሰምቼአለሁ:: «አንተ የምትተኛ ንቃ፣ ከሙታንም ተነሣ::» ኤፌ.5÷14:: እንደ ተባለ ምእምናን በያለበንበት ነቅተን ቤተክርስቲያናችንን ልንጠብቅ ይገባል::

ስለሺ ምራኒ
ጅማ ዩኒቨርስቲ

## እንድረስላቸው

ምንም እንኳን ከባሕር ማዶ በሚጐርፍላቸው ገንዘብ ተዋሕዶአዊት ቤተክርስቲያናችንን ለመሸርሸር ቢኳትኑም፣ ለጣያት አንሰግድም በማለታቸው ወደ እቶን እንዲወረወሩ የተደረጉትን ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጐን ፀጉራቸው እንኳን በወላፈኑ ሳይነካ ከእሳት ያወጣቸው፣ሳኦልን ከአልጋው አውርዶ ዳዊትን ከትቢያ አንሥቶ በትረ መንግሥት ለመጨበጥ የረዳው አምላክ ዛሬም ከእኛ ጋር ነውና አንሰጋም:: የሆነው ሆኖ በገጠር በተለይም በጠረፍ ያሉ አብያተክርስቲያናት በብዛት አስታዋሽ አጥተው በአሳባቢ ሁኔታ ላይ ናቸውና ምእመናን እና ስታውሳቸው:: በዚያ ያሉትም ወገኖቻችን ናቸውና::

*ዓለማየሁ ደረሰ ዲምቱ*

## የምሥራች

የማኅበረ ቅዱሳን
ቁጥር ፩
ያሬዳዊ የመዝሙር
ካሴት በቅርብ ቀን
በሥርጭት ላይ
ይውላል::

# ሥዕል ወይስ ምስል?

*ከኃ/ገብርኤል ዘሐና*

ሰብል ሲያዘረዝረ ጠላት ይበዛበታል የሚለውን የቄሱን ቃል እያሰላሰልኩ ከሩቅ ጉዞዬ እየተመለስኩ ነው:: ደብረ ብረሃን ከተማ ደርሻለሁ:: መሐል ከተማ ያለውን የቅድስት ሥላሴን ቤተክርስቲያን ልሳለም ጎራ አልኩ:: ገና ከቅጥሩ ስገባ ብዙ ገንዘብ ፈስሶበት የተሠራውን ምስል አየሁ:: የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና፣ሥነ ስቅለት የሚያሳይ መሆኑ ነው:: መንገደኛነቴን ዘንግቼው ቆሜ እመለከተው ጀመር:: ከኋላዬ አንድ የኔቢጤ መጥቶ ጋሼ ይሄ እኮ በየጊዜው ልብስ ይቀየርለታል፤ መጋረጃ ይጋረድለታል:: በተለይ በበዓል ወቅት የሚያማምር ልብስ ይጎናጸፋል አለኝ:: ቃል አልተነፈስኩም:: ምስልና ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መች ይሆን የተዋወቁት? ጠያቂው አእምሮዬ ጠየቀ:: ከግቢው ወጥቼ መንገዴን ቀጠልኩ::

አዲስ አበባ ብዙ ያዘረዘሩ ሰብሎች በፀረ ሰብል ተባዮችና እንስሳት እየተበላባት ያለች ሀገር ናት:: ጓደኛዬ ነው ይህን የነገረኝ:: ፈራሁ የፈሪዎቹም የጀግኖቹም መሸሸጊያ ወደሆነችው ቤተክርስቲያን ሮጥሁ:: የመጀመሪያውን ቀን አራት ኪሎ ካቴድራል ቅድስት ሥላሴ፣ሁለተኛውን ቀን ታዕካ ነገሥት ባኣታ ለማርያም ሄድሁ:: በሦስተኛው ቀን መቼስ አንዴ መንገደኛ ሆኛለሁ፤ ስዞር ነው የዋልኩት:: አራት ኪሎ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ፣ምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም፣ሽሮሜዳ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ፣አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል የሄድኩባቸው ናቸው:: ሁሉም ደስ ይላል:: እንደየዐቅማቸው ተልዕኮአቸውን ለመወጣት ደፋ ቀና ይላሉ:: አንዳንድ ያየኋቸው ምእመናን ድርጊት ግን ውጤን ረበሸው:: አሳዘኑኝ:: በግቢው ውስጥ ከቆሙት ምስሎች ሥር ተደፍቶ ይጸልያሉ:: ከመቅደሱ ገብቶ ከጽላቱ ፊት ተደፍቶ መጸለዩስ ሊቀር ነው? አልኩኝ::

እነዚያ ደብረ ብርሃን ያየሁአቸው ዓይነት ምስሎች በአንዳንድ የአዲስ አበባ አድባራት እና ገዳማት ተገጥግጠው መሠራት ጀምረዋል:: የ4 ወንጌላውያን ፣የመላእክት፣የእመቤታችን ምስል በጀሶ፣በተለያዩ ማዕድናት ተቀርጸዋል:: አሁንም አእምሮዬ ምስልና ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መች ይሆን የተዋወቀት? ብሎ ጠየቀኝ::

ቀኑን ሁሉ ስዞር ውዬ ደክሞኛል:: የጊዜ ንዋሙን ጸሎት አድርሼ ልተኛ ስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ:: ያኔ ልጅ ሳለሁ የሃይማኖት አባቴ ስለ ሥዕልና ስለ ምስል የነገሩኝ ነገር ታወሰኝ:: «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከምትጠቀምባቸው ንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ሥዕል ነው:: ሥዕል በተለያዩ ቀለማት በወረቀት፣በጨርቅ፣በብራና በግድግዳ ላይ የሚሳል ነው:: ሥዕል ለመንፈሳዊ አገልግሎት መዋል የጀመረው በፈቃደ እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን ሲሆን በመጀመሪያ የተሳለውም ሥዕለ ኪሩብ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል:: ዘጸ 37÷7 :: ቤተክርስቲያናችን ከጀሶ፣ከስሚንቶ፣ከእንጨት የሚሠሩ ምስሎችና ቅርፆችን አትቀበልም::»


**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ መሆን ከፈለጉ**

| | ሐመር መጽሔት | | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 ዕትም | የ12 ዕትም | የ6 ዕትም | የ12 ዕትም |
| ለአዲስ አበባ | 18.70 | 37.40 | 10.00 | 20.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 19.20 | 38.40 | 10.50 | 21.00 |
| ለውጭ ሀገር | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 9 ዶላር | 18 ዶላር |

አድራሻዎንና የከፈሉበትን ማስረጃ ለዲ.መስፍን ተ/ዮሐንስ ንግድ ባንክ 4 ኪሎ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 75282 አዲስ አበባ ከፍለው በመ.ሣ.ቁ 80078 ይላኩልን::

## በማኅበረ ቅዱሳን
## የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች

- ሐመር መጽሔት የተለያዩ ዕትሞች
- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ የተለያዩ ዕትሞች
- ሌሎች መንፈሳዊ መጽሔቶች
- የቪዲዮ ትምህርቶች
- መንፈሳዊ ፖስት ካርዶች
- የጸሎትና የትምህርት መጽሔት
- ቅዱሳት ሥዕላት
- የሥጦታ ዕቃዎች

### በተጨማሪ ምን አዲስ ነገር አለ? ቢሉን

- ኦርቶዶክሳዊ የልጆች አስተዳደግ በሚል አዲስ የቪዲዮ ትምህርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል
- ኢትዮጵያዊ የአሳሳል ዘይቤን የምታንጸባርቅ የ1993 ዓ.ም የትንሣኤ ፖስት ካርድ ተዘጋጅታ ቀርባለች።
- የማኅበረ ቅዱሳን ቁ 5 ያሬዳዊ መዝሙር በቅርብ ቀን በገበያ ላይ ይውላል።
- «<u>የንስሐ ሕይወት</u>» መጽሐፍ እንደገና ታትሞ እየተሠራጨ ነው።

ይህ መጽሐፍ የሚከተሉትንና ሌሎች ዝርዝር ነጥቦችን የያዘ ነው።

- ንስሐ ምንድነው ?
- ለንስሐ የሚያበረታቱ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?
- እንዴት ንስሐ ይገባል?
- ንስሐን ከፈተና እንዴት መከላከል ይቻላል? ወዘተ...

☛ ነገረ ድኅነት የሚል አዲስ መጽሐፍ በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል ተዘገጅቶ ቀርቧል

**ሁሉንም እንደፍላጎትዎ ከማከፋፈያዎቻችን ያገኟቸዋል።**

<u>አድራሻ</u> :-

<u>አዲስ አበባ</u>

<u>ቁ.1</u> መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን 5 ኪሎ አካባቢ ከሸዋ ዳቦ ቤት ፊት ለፊት፤

<u>ቁ.2</u> ገነተ ጽጌ /አራዳ/ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ የከተማ አውቶቡስ መጠበቂያው አጠገብ
ስልክ 565159 መ.ሣ.ቁ 80078

<u>ክፍለ ሀገር</u>

መቀሌ፣ጅማ፣አርባ ምንጭ፣ጎንደር፣አሶሳ፣ነቀምቴ፣ባሕር ዳር፣አዋሳ፣ድሬዳዋ

<u>አዲስ የተከፈቱ</u> 1/ ናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት
2/ ፍቼ
3/ ደሴ

### በማኅበረ ቅዱሳን የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ

- የካህናት አልባሳት
- የመዘምራን ልብስ
- ጧፍ፣ዕጣን፣ዘቢብ...
- ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች አልባሳት
- በተክሊል ለሚጋቡ ሙሽሮች የካባ ኪራይ
- ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት

የቤተክርስቲያናችንን ሥርዓት ጠብቀን ቀጠሮ አክብረን በተመጣጣኝ ዋጋ በጥራት እንድናዘጋጅልዎ ይጐብኙን።

<u>አድራሻ :-</u> አዲስ አበባ ከገነተ ጽጌ /አራዳ/ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደ 6 ኪሎ በሚወስደው መንገድ መቅደላ ሆቴል አጠገብ

ስልክ 128460 መ.ሣ.ቁ80078


ዋጋ ብር 3.00

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡